# ለምን አልሰለምሁም?

ከ(ቀሲስ) ግርማየሁ ሞገስ:

ከሁሉም ሁሉን ይወቅ ጸራሲ

<u>ክርስትናንና ስልምናን በማነጻጸር፣</u>

አዲስ አበባ
መጋቢት 1990 ዓ.ም.

ክርስትናና ስልምና በኢትዮጵያ ለብዙ ዘመናት አብረው፣ተባብረው የኖሩትን ሃይማኖቶች ለማቃቃር አንዳንድ እስላሞች ትክክል ያልሆኑ፣ በሐሰት ፕሮፖጋንዳ የተሞሉ ክታባት ስለበተኑ የተሰጠ መልስ።


የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።

## ማስገንዘቢያ፤

ለማንኛውም ውድና ክቡር አንባቢ የተሰጠ ማስገንዘቢያ፤

ይህ መጽሐፍ አንድ ጊዜ አንቦ የሚጥሉት ልብ ወለድ የተረት መጽሐፍ ስላልሆነ፣በፍጹም ለመረዳት ዳር እስከ ዳር ቢያንስ ሁለት ጊዜ፣አፍ ተልብ ሁኖ፣ከጫጫታ ርቆ መነበብ አለበት።

ከውሳኔና ከፍርድ በፊትም በደንብ መረዳት ያስፈልጋል። ያለዚያ ግን ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል። ይህ ቀርቷል፣እንዲህ ቢሆን የሚል ሂስም ከቀረበ በሚቀጥለው መጽሐፍ ለማስተናገድ ዝግጁ መሆናችንን በትሕትና እንገልጣለን። ብቻ በጽሞና ተነቦ ይሁን።



ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ፤ ብዙዎች እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ በስሜ ይመጣሉና፤ ብዙዎቹንም ያስታሉ። (ማቴ.24:4) ብዙ ሐሰተኞች ነብያትም ይነሳሉ፣ ብዙዎችንም ያስታሉ (:16)።

ሰላም የሚረታው አደለም በመጽሐፉ
ነው እንጂ በሰይፉ።
ድሉ በሰይፉ ካልሆነ
በመጽሐፍትስ እነሆ አለን።
መጸሕፍት ደግሞ ካልሞሉ ለሥጋ ጥቅም ስርብትና
አንድነት ሁነን እናጥናቸው ተሰብሰበን በጽሞና።
እውነትን ፈላጊ ከሆንህ፤የማታደላ ለጥቅም
ይህን መጽሐፍ አንብና እንነጋገር በሰላም።
ይህን ብናደርግ ለጽድቅ ብለን
አንዱ አምላካችን ይደሰታል።
በእኛ ድኀነት፣በእኛ ሥልጣን
እኛም መንግሥቱን እንወርሳለን
እንደ መላእከት ትጉሃን
ስሙን እየቀደስን በክብር
እኖራለን በደስታ በሰማያዊው ማኀደር
በሃይማኖት አመከኛተን
ለገንዘብ ለሹመት ብለን
ብንዋጋ፤ብንጋደል
ሰማያዊ ክብር አናገኝም
በምድርም ሰላም ፍጽም የለም።
በኦሪትና በወንጌል፤ ጌታ ያዘዘውን ቃል ኪዳን
ክርስቲያን ትቶ ወደጎን
ሰላምንም ይዞ ተረቱን
ሲፋጅ ይኖራል ዘለዓለም
ለሹመት፤ለገንዘብ፤ለጥቅም።
ጥቅም ካልፈለግህ የሰው ዘር
እውነትን ፈልግ በምርር
ለዚህም ይርዳህ እግዜር።

## የደራሲው ሥጋዊ ሂደት፤





አሳምሮ ፈጥሮ፣በእየጊዜው ከደረሰብኝ ፈተና ሁሉ እያሳለፈ ከዚህ ላደረሰኝ፣ፈጣሪዬ፣አምላኬዬ፣መድኀኒቴ፣ወልደ እግዚአብሔር፣ መድኀኔ ዓለም እየሱስ ክርስቶስ የተሰጠ ንኡስ ሰማዕታዊ (ምስክራዊ) ገጸ በረከት። ^

## አርእስት፤

ለምን አልሰለምሁም ወይንስ አልሰልምም? 1
1. የደራሲው ሥጋዊ ሂደት 3
2. ሰላም የሚረታው (በግጥም) 2
3. መቅደም 6
4. መግቢያ 9
5. ምዕራፍ: 1 11
   ምስጢረ ሥላሴ
6. ምዕራፍ: 2 16
   ምስጢረ ሥጋዌ
7. ምዕራፍ: 3 20
   የቅዱሳት መጻሕፍት ታማኝነት።
8. ምዕራፍ: 4 22
   ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ነው።
9. ምዕራፍ: 5 32
   ክርስቶስ ዐምደ ብርሃን
10. ምዕራፍ: 6 34
   ትንቢታትን ሁሉ የፈጸመ ክርስቶስ ብቻ ነው።
11. ምዕራፍ: 7 39
   ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ተነሥቷል።
12. ምዕራፍ: 8 48
   መንፈስ ቅዱስ እንጂ መሐመድ አይደለም።
13. ምዕራፍ: 9 51
   የሙሴና የኢየሱስ መመሳሰል
14. ምዕራፍ: 10 53
   ሙሴና መሐመድ ግን አይመሳሰሉም።
15. ምዕራፍ: 11 62
ክርስቶስ በኋላው ለሚመጡ ውሸታም ነቢያት ምን ይላል?
16. ምዕራፍ: 12 66
   ከክርስቶስ በኋላ ነቢይ የለም።
17. ምዕራፍ: 13 69
   የመሐመድ ታሪክና ስለምና።
18. ምዕራፍ: 14 75
   መሐመድ ያልሠራው ኀጢአት፤ያላደረገው በደል የለም።

19. ምዕራፍ: 15 — 84
መጽሐፍ ቅዱስ ስለመሐመድ
20. ምዕራፍ: 16 — 89
ክርስቶስ አዲስ ሕግ አላወጣም ብለዋል።
21. ምዕራፍ: 17 — 91
በቁርአን አዲስ ነገር የለም ከሰማይም አልወረደም።
22. ምዕራፍ: 18 — 94
ቁርአን በይዘቱም ሆነ በጽሕፈቱ ዝብርቅርቅ ነው።
23. ምዕራፍ: 19 — 103
ቁርአን ከክርስትና ምን ያምናል?
24. ምዕራፍ: 20 — 109
ስልምና የክርስቶስን መሰቀል ይክዳል።
25. ምዕራፍ: 21 — 111
ስልምና ወይም ቁራን የክርስቶስን ነብይነት ያምናል።
26. ምዕራፍ: 22 — 114
የጥናቱ ውጤት ባጭሩ።
27. ምዕራፍ 23 — 117
ከመሐመድ የሚያንስ ነቢይ የለም፣
28. ምዕራፍ 24 — 119
የጥንቱ ውጤት ባጭሩ፣
29. መፍትሔ ቃላት — 121
30. የተነበቡ መጻሕፍት — 123
31. የሚነበቡ መጻሕፍት
32. መወድስ — 125

**<u>ምስጋና፣</u>**

ለዚህ መጽሐፍ አተነባበር ብዙ ሊቃውንት በምክርም፣ መጻሐፍ በማቀበም ረድተዋል። በመቅድሙም ሐሳቡን ያመነጩት ሴሎች እንደሆኑ ተገልጧል። ስለዚህ እኔም በመጻሐፉ እንደሕጉ ስማችሁን በምስጋና ላስታውሥ ብላቸው መጽሐፉ የሚያመጣውን ተከታታይ ስለፈሩ ቢዘሉሉም ከእኔ ጋራ እግዚአብሔር ዋጋቸውን ይከፍላቸው እያልሁ እየጸለይሁ፣ቀና የሆነ አንባቢም እንዲጸልይላቸው አደራ እላለሁ።

## መቅድም፤

በገበሩ እንደ ተገለጠው ክርስትናና ስልምና መሐመድ ከተነሣበት ጊዜ ጀምሮ በኢትዮጵያ በኅብረት የኖሩ ሃይማኖቶች ናቸው። እንዲያውም የመሐመድን ተከታዮች ወገኖቹ ቢያሳደዷቸውም ኢትዮጵያ አስተናግዳለች። በዚህም ለስልምና ባለውለታ ናት። ኢትዮጵያዊው፡ኦርቶዶክስ ክርስቲያን በ16ኛው መቶ ዘመን በስሕተት በተደረገው የሃይማኖት ጦርነት ምክንያት ከወንድሞቻቸው ካቶሊክና ወንጌላውያን ይልቅ ስላምን ይመርጣሉ። ስለ ካቶሊክና ወንጌላውያን ሲያነሡባቸው፤ስላም ምን አለን? ከድሮ ጀምሮ አብረን አይደል የኖርን፤የእኛ ጠላቶች አሁን መጤዎች ሃይማኖቶች፤ካቶሊክ፤ፕሮቴስ ታንት፤ጴንጤ፤ወዘተ.እንጂ ይላሉ። ይህ ስሕተት መሆኑን ከተማረው በቀር ኅጋው (ተራው) ሕዝብ አያውቀውም። እኔም ክርስቲያኖች ወንድማማቹ በምስጢረ ሥላሴ፤በሥላሴ አንድነት ሦስትነት የሚያምኑ ሁሉ ለሹመት፤ለሥልጣን፤ለገንዘብ ብለው በፈጠሩት ጭቅጭቅ እንጂ በሃይማኖት እምብዛም ስለማይለያዩ በውይይት ልዩነታቸውን እንዲፈቱ በቃልም፤በትምህርትም በመጽሐፍም ስደክም ስለስልምና ትኩረት ሳልሰጥ እኖር ነበር።

በዚህ ላይ ሳለሁ፤በጊታ በመድኅኔ ዓለም በዓላት ብዙ ነገር አጋጥሞኛል። በዚሁ መሠረት የመ.ጋቢት መድኅኔ ዓለም ዋዜማ 1989 ዓ.ም. አንድ ሰው ደውሎ፤ "አያውቁኝም እኔ ግን ዩኒቨርስቲ ሲያስተ ምሩ አቅወታለሁ። ከጓደኞቼ ጋር እየሱስ እውን ፈጣሪ ነውን? የሚል መጽሐፍ አንብበን፤ለቤተ ክህነት ጉባኤ ሊቃውንት መልሱ ብለን ብንሰጣቸው፤እናት ሥራ አጣችኋል፤እኛ ለራሳችን አባታችን ተሰድበ ው ተጨንቀናል፤እናት ደግሞ ከጥንት የኖረውን የስላም ጥያቄ ይዛችሁልን መጣችሁ ብለው አመናጭቀው መለሱን፤እኛም አማራጭ ብንፈልግ እርስዎ ትዝ አሉንና ለእርስዎ ለመስጠት ወስነን፤ቤትዎን የሚያውቅ ሰው ፈልገን መጽሐፉን በነገ ጀምበር ልንልክልዎ ነው" አለኝ። "እኔም የማሳትምበት ገንዘብ የለኝም። በማስተማር የኖርሁ፤በት ንሽ የጡረታ አበል የምኖር፤ከዚህ በፊት በቅርቡ ሁሉም ሁሉን ይወቅንና አንድ እረኛ አንድ መንጋን ያሳተምኋቸውም ለከፈን ትሆናለች ብዬ ባስቀመጥኳት ነው። እነሱም ከ84000(ብር)በላይ ጨርሰውብኛል። ተሸጠው ዋጋቸውን እንዳይመልሱም በእየደብሩ ያሉ ያልተማሩ፤የማያነቡ የጠላቶቻችን የውስጥ አርበኞች ኅጋው አንብቦ እንዳይወጥራቸው ፈርተው አታንቡ ስላሉት ወጭው ስላልተመለሰ ሌላ መጽሐፍ የማሳትምበት አቅም የለኝም "ብዬ

ብመልስ፣እኛ መጻሕፉን አምጥተን ከአፕርዎ ውስጥ እንጥላለን ከዚያ በኋላ ያለው የራስዎ ኃላፊነት ነው" ብሎ በጆሬዬ ስላኩን ዘጋ። እንዳለውም በበነጋው የሚያውቀኝ ሰው እነእገሌ ናቸው ሰጣቸው ብለው የሰጡኝ ብሎ ሰጠኝ። እኔም ቅዳሚና እሑድ የማኅበራዊ ግዳጀን ትቼ አነበብሁና ባነበብሁ መጽሐፉ በብዙ ስሕተትና በድፍረት የተጻፈ በሐሰት የተሞላ ሆኖ አገኘሁት፣በዚህ ጊዜ ቋንቋ ስማር በዩኒቨርስቲ ለማግኘት ተብሎ ሁለት ሴሚስተር ዐረብኛ ተምሬ ነበርና፣ብዙ ጊዜ ትርጉም ስለማላምን፣ዐረብኛ የተማርሁባቸውን ደብተሮችና ምንባባት ማገላበጥ ጀመርሁ፣ወዲያውም መዝገበ ቃላት አስፈላጊዩ መሆኑን ተረዳሁና፣አንድ የኪስ መዝገበ ቃላት አለችን በዚያች ለመረዳት ብፈልግ ወደ 80 የሚገስግሰው ዐይኔ ናቃትና ተናንቀው አልተያይ ስላሉ ትልቅ መዝገበ ቃላት ፍለጋ ወደ አንዋር መስጊድ፣መርካቶ ሄድሁ። ከዚያ ግን የሚከተሉትን ክትባት ተደርድረው አገኘሁ። እነሱም በአርእስታቸው ፊደል ተራ ከዚህ በታች የተጻፉት ናቸው፤

1. መጽሐፍ ቅዱስ ስለመሐመድ ምን ይላል?በአሕመድ ዲዳት፤ይህ አንድም እውነት ወይም ፍሬ የለውም፣ሁሉም በዚህ መጽሐፍ በቂ መልስ አግኝቷል።
2. መሐመድ የታላቆች ታላቅ፣አሕመድ ዲዳት (ሰው በመፍጀት)
3. ሰብአዊ መብት በኢስላም (እንደ ሥርአታቸው)
4. የሴቶች ደረጃ በኢስላም (ዶ/ር ጀማል አልበዳዊ)
5. ስለ ኢየሱስ እውነተኛ መረጃ (ቁርአንን እንጂ ሌላ አልጠቀሰም) (ዶ/ር ማንሕ ሐምማድ አልጆሀይኒ)
6. ቁርአንን ለመረዳት (አቡል አዕለ መውዲድ። (ስለቁርአን መውተፍተፍ)
7. ኢየሱስ እውን ፈጣሪ ነው?(ዲዳት ባላወቀው ገብቶ የዳከረበት)
8. እስልምና ክርስትና (መሐመድ ዐሊ አልኹሊ) መጽሐፍ ቅዱስን አይቀበልም፣የራሱን ተረት ያወራል።
9. ክርስቲያን ሙስሊም ውይይት፣ ዶ/ር ሐሰን፣ኢም፣.........በዚህ መጽሐፍ ብዙ የእስላም ስሕተቶች ተጋልጠዋል።
10. ክርስቶስ በኢስላም (አሕመድ ዲዳት(ይህ የዲዳት መጽሐፍ ነው የመሰለውንና የሚመኘውን ያወራል)
11. ውድ ዐብደላ፤ጊርሃርድ ኔሀልስ(ለመግባባት ነው የተጻፈው)
12. የእምነት መሠረቶች ትንታኔ፤አርካትኤል፣(ይህ የሚሰብከው ሃይማኖቱን ነው፤ሁሉም እንደዚህ ቢሆን ኑሮ መልስ አያስፈል ግም ነበር።

13. <u>የናብ ዒሳ መልእክት</u>፤ጊርሃርድ ኔልስ
14. <u>የዳዕዋ ሰዎች ሥነ ምግባር</u>፤አቡል አዕለ አል መውደዲ፣ይህ
ም የአራሱን ሲሰብክ ክርስትናን በኢርቱዕ ይኅሰማል እንጂ
ስም ጠርቶ አይሳደብም።
15. <u>ግብጻዊቷ መነኩሲትና ፈረንጆች ሲቃውንት በእስልምና</u>
<u>ጎዳና</u>፤አብደላ መሐመድ ዐሊ (ይህ እውነት ቢሆን ኑሮ ያለምን
ም ጦርነት ዓለም ሁሉ በሰለመ ነበር)።
16. <u>የጽድቅ ጥያቄዬ፤</u> ሡልጣን መሐመድ ከሃን (ብዙ ሃይማኖት
ከመረመረ በኋላ እውነተኛው ክርስትና ነው ብሎ የመሠከረ) ከዚያም
ከመስጊድ በራፍ ላይ ክርስትናን የሚያጥላሉና የሚያረክክሱ ስድስት
ክታባት አገየሁና ትልቅ መዝገበ ቃላትና አንድ ለጀማሪ የሚሆን ዐረ
ብኛ መማሪያ ገዝቼ፣ወደ ቤቴ ተመልሼ ዐረብኛ መክለስና መማር
ጀመርሁ። ክታባቱንና መጻሕፍቱን አነበብሁ። ቁርአኑንም ዐረብኛዬን
ስለማላምናት በዐረብኛ ታንቱ እያሉ፣በእንግሊዘኛ፣በፈረንሳይኛ በአማ
ርኛ ትርጉም ሌት ተቀን ተያያዝሁት። ይህም በጠቅላላ ማኅበራዊ
ግዴታዬን ትቼ ሦስት ወር ወሰደብኝ።

እኔ የተነሣሁት ግን እውነትን ለመፈለግ እንጂ ስልምና?
ለማጥላላት ወይም ለመንቀፍ እንዳልሆነ ስላም ሁሉ እንዲያውቅልኝ
እፈልጋለሁ። የምመልሰውም በእኛ ላይ ለተሰነዘሩት ስድቦችና
ነቀፌታዎች ብቻ ነበር። በኋላ ግን የራሱን ሃይማኖት እንኳ አጣርቶ
ያላወቀ ስላም ሁሉ መማሪያ ስላደረገን ሥር ነቀል አጠቃላይ መልስ
ለመስጠት ተገድጃለሁ። የስላም መሪ መሐመድ በ19ኛው ሱሩህ
ስለሌሎች ሃይማኖቶች ያለውን ችላ ብለው ወይም ዘለው በክርስቲያን
ላይ ስለዋሹና ስለዘላበዱ ነው ይህ መልስ የተሰጠው። ሱራሁም ራሱ
ስላሙ እንብቦ እንዲፈርድ ከዚህ ይቀጥላል።
እናንተ ከሓዲዎች የምታመልኩትን አላመልክም። እናንተም እኔ
የማመልከውን አታምልኩም። እኔም እናንተ የምታመልኩትን አላመል
ክም።እናንተም እኔ የማመልከውን አታመልኩም። ለእናንተም ሃይማኖ
ታችሁ ለእኔም ሃይማኖቴ፤(በቁር አን መደጋገም ልማድ ነው) ይህን
ያለውም በእየሃይማኖታችን እንቁም ለማለት ነበር። እነ ዲዳት ግን ቁርአንንም
ሳያውቁ፣የስልምናን ሕግም ሳያከብሩ፣ምስጢሩንም ሳይረዱ ይጥሉታል።
ቅስውም አሁንም ከማያውቋቸው ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ገብተው
ይዘላብዳሉ። ስለዚህ ቀማጣን ቀማጣ ካላሉት ገብቶ ይፈተፍታል እንደ ተባለው
እንዳይሆን ይህ መጽሐፍ ከእኔ ከደካማው፣የተሻላ ሌላ ሊቅ ጥሩ መልስ እስኪ
ሰጣቸው ድረስ መቆያ ተሰጥቷቸዋል።
ይህን ላነበበ ሁሉ በልቶ በመድኅኔ ዓለም፣ዓለምን ያዳነ እግዚአብሔር ልቡና
በጥቶት እውነተኛውን መንገድ ተከትሎ መንግሥቱን እንዲወርስ፣በሙሉ
እንዲቀደስ ያደርግ ዘንድ በልጁ በእየሱስ ክርስቶስ ስምና መስቀል እንለምናለን።
አሜን

# መግቢያ፤

## ቋንቋ

ቋንቋህ ከባድ ነው ስለሚሉ ብዙ ሰዎች፣የሃይማኖት ሕጋጌ ካልሆነ በቀር በቀላል አማርኛ ለመጽሐፍ ተሞክሯል። የሃይማኖትና የፍልስፍና ቃል ሲሆንም መጀመሪያ በተገኘበት በቅንፍ ይተረጎማል፤በመጨረሻም በመፍትሔ ቃላት ይፈታል። አንቱና አንተ፣አርስዎ፣በሚከተሉት ምክንያቶች ሁሉም አንተ ነው።

ሀ. ከጳጳት በቀር ያውም ያሁኖቹ ሐዲሶቹ እንጂ ሁሉም አንተ ነው፤ቂርሎስ እንዲህ አለ፣ቆስጠንጢኖስ ነገሠ፣አትናቴዎስ ጸሎተ ሃይማኖትን አረቀቀ። ጳጳስም እንኳ ቢሆን ከግብጻውያን በስተቀር አንተ ሲባል ነው የኖረው። እግዚአብሔር የዚህ ዓለም ፈጣሪ አንተ፣ልጁም የዓለም መድኀኒት፣መንፈስቅዱስም የዓለም ሕይወት አንተ ነው የሚባሉ፣ማርያምም አንቺ፣በዚህ ሕግ መሠረት ከመሐመድ በቀር ሁሉን አንተ የሚለው አሕመድ ዲዳትም በሃይማኖትም፣በትውልድም፣በባህልም የውጭ ስለሆነ አንተ ይባላል። አንቱ ለዘመድ የሆነ እንደሆነ ፍቅርንና መላመድን ሲያሳይ፣አንቱ ደግሞ ለባዳ፣ለሩቅ፣ መራራቅን፣አለመላመድን ያሳያል።

አያ አሕመድ ዲዳትንና መሰሎቹን ወንድሞቼ እንዳልላቸው በዝምድና፣በባህል፣በሀገር፣በሃይማኖት ስለማንገናኝ ወንድሞቼ ማለት ቅጥፈት ስለሆነ በሀገር ቤቱ ማዕረግ አያ አሕመድ፣አያ እገሌ እያልሁ እጽፋለሁ።

እነዲዳት ለራሳቸው ክርክር እንዲመቻቸው እስራኤልን አይሁድ ብለው ጽፍው፣ አይሁድ የሚል ቃል የለም ብለው ጽፈዋል፤የአብርሃም ልጆች እስራኤል፣ዕብራውያን እንጂ አይሁድ ወይም ይሁዳ አይደሉም። ይሁዳ (ብዙው አይሁድ) ከዐሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል ከያዕቆብ ልጆች አንዱን፡ስለዚህ በዚህ መጽሐፍ ይሁዳ ከያዕቆብ ልጆች አንዱን፣አይሁድ ደግሞ የእሱን ልጆች ያሳያል፤ እስራኤል ደግሞ የያዕቆብን ልጆች፣በመላ፣ዕብራውያን ከእስማኤል በቀር የአብርሃምን ልጆች ያሳያል። አይሁዳውያን የሚሉ ግን አማርኛ የማያውቁ ሰዎች አሁን በቅርቡ የፈጠሩት ነው።

## ጥቅስ፤

የሚጠቀስ መጽሐፍ ሁሉ ከተጠቀሰ በኋላ እንዳለቀ ከዚያ መረጃው ምንጩ ተጠቅሶ ይቃለፋል።

<u>ቋንቋ</u> የሚጠቀሰው ሁሉ የሚጻፈው በአማርኛ ብቻ ነው፤ንጹሕ የክርስቲያን የዐረብኛ ማተሚያ ቤት በአዲስ አበባ ስለሌለ የማሳተም ችግር እንዳያመጣ። ትርጉሙም የሚሰጠው በቀጥታ ከዐረብኛ በንጹሕ አማርኛ ነው።

## ቅደም ተከተል፤

የአርእስቱ ቅደም ተከተል የተጠየቅን መንገድ ተከትሎ የቀረበ ነው።
በተቻለ መጠን የመጽሐፉ አቀራረብ ለአንባቢው ተጠየቅ እንዲመች ተሞክሯል።

የመጽሐፍ ስምና ምዕራፍ በተከታታይ ከተጠቀሰ ቁጥር እንጂ የመጽሐፍ ስማና ምዕራፍ አይደገምም።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ብዙ ድግግሞሽ አለ፤ምክንያቱም የክርክር መጽሐፍ ስለሆነ መረጃውን በእየእርስቱ ለመስጠትና አንባቢን ሌላ መጻሕፍት ከማገላበጥ ለማዳን።

ምሕጻረ ቃል፤ቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ተለመደው፤የተቀሩት ሊቃውንትና የስላም ክታባትና ቁራን ግን በዝርዝር ይጻፋሉ።

# ምዕራፍ:1፤

## ምስጢረ ሥላሴ፤

ምስጢረ ሥላሴንና ምስጢረ ሥጋዌን በስፊው የሚናገሩትን ሁለቱን መጻሕፍታችንን፤ሁሉም ሁሉን ይወቅንና አንድ እረኛ አንድ መንጋን እንዲያነብ አንባቢን ጠቁመን፣ክርስቶስ ምስጢረ ሥላሴን አላስተማረም፣ የአምላክ ልጅም አይደለም፣ አምላክ ነኝም አላለም እያሉ ዓለምን ለሚያወናብዱት ለነአሕመድ ዲዳት ማብራሪያ ደግሞ ይህን እንሰጣለን።

ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በአካል አንድ ብቻ አልነበረም። በአካል በስም፣ በግብር ሦስት፣በመለኮት፣በባሕርይ በህልውና አንድ ሁኖ አንድ አምላክ እየተባለ ዘለዓለም ሲቀደስ ኑሯል፤ ይኖራል።

ሥላሴ በስም አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ይባላሉ። በግብር አብ ይወልዳል፣ያሠርጻል፣ወልድ ይወለዳል፣መንፈስ ቅዱስ ይሠርጻል።፡በአ ካል አብም፣ ፍጹም አካል(ህልውና፣ገጽ) አለው፤እንደዚሁም ወልድና መንፈስ ቅዱስ ከአብ የተለየ ፍጹም አካላት አሏቸው። አካልንና ሰውነትን ከኛም ያልተማሩ ሰዎች ያደባልቃሉ፤አካል ሦስቱም፣ አብ፣ወልድ፣መንፈስ ቅዱስ ለእየራሳቸው አሏቸው፤ሰውነት ግን የሚ ጨበጥ የሚዳሰስ ያለው ወልድ ብቻ ነው። ይኸውም ሥጋ በመልበሱ። በምስጢረ ሥላሴ አካል ለቀዋሚ ነገር ለመንፈስ ነው የሚነገረው፣አ ይታይም አይዳሰስም፣መንፈስ ነው። አካል በምናውቃቸው በሌሎቹ ቋንቋዎች (ፕሮሶፓን ግሪክ፣ፔርሶና ላቲን፣ፔርሶን እንግሊዝ፣ጣልያን ፈረንሳይ ነው። ሰውነት (በአካል በሚዳሰስ ትርጉሙ)ሶማ ግሪክ፣ቦዲ እንግሊዝ፣ኮርፓ ጣልያን፣በፈረንሳይ በንባቡ ኮር በአጻጻፍ ኮርጥስ፣ላ ቲን ኮርፑስ ነው። ስለዚህ ነው ወልድ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ በተለየ ረቂቅ አካሉ ሥጋ ስለለበሰ፣ ሰውነት (የሚዳሰስ አካል) አለው የሚባለው። ባሕሪያቸው መለኮታቸው፣መንግሥታቸው፣ሥልጣናቸው ግን አንድ ነው።፡በአካል ሦስት ስለሆኑና በመለኮት፣በባሕርይ አንድ ስለሆኑ፣ እኔ እያለ በነቢያት በክርስቶስ፣በሐዋርያት፣እግዚአብሔር ሲያናግር ኑሯል።

1. (ዮሐ. 1:1-3) በመጀመሪያ ቃል ነበረ፤ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ። ይህ በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ። ሁሉም በእሱ ሆነ። ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለእሱ የሆነ የለም። ከዚህ ላይ ከመጀመ ሪያ ጀምሮ ከእግዚአብሔር አብ ጋራ ሌላ እግዚአብሔር ወልድ እንዳለና ያለእሱም ምንም እንዳልሆነ ይናገራል፤ በአካል የተለያዩ በመለኮት ግን አንድ የሆኑ፣ሁለት አካላት፣ አንድ እግዚአብሔር እንዳለ ወንጌላዊው ቁልጭ አድርጎ ገልጧል፣ከዚህ ላይ የተጠቀሱት ሁለቱ አካላት አብና ወልድ ናቸው፣ዝቅ ስንል ደግሞ ሦስት አካላት መሆናቸውን እናያለን።

2. (ማቴ.3:16-17) ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ከውኃ ወጣ፤እነሆም ሰማያት ተከፈቱ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንደ ርግብ ወርዶ ከእሱ ላይ ሲቀመጥ አየ። እነሆም ድምፅ ከሰማያት ወጥቶ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ። በዚህም በአምሳለ ርግብ የወረደው እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፣የምወደው ልጄ ያለ እግዚአብሔር አብ፣ተጠማቂው ሰው የሆነው እግዚአብሔር ወልድ በትስብእቱ ዐማኑኤል፣ኢየሱስ ክርስቶስ የተባለው፣በኋላ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ሥላሴ ብለው የሰየሟቸው አካላት፣አብ ወልድ ወመንፈስ ቅዱስ መሆናቸውን ቁልጭ አድርጎ ያሳያል። (ማር.1:911፤ ሉቃ.3:21-22)

3. ይኸው ታሪክ በደብረ ታቦርም ተደግሟል፣ያውም ከትእዛዝ ጋራ፣(ማቴ.17:1-6፤ማር.9:2-13፤ሉቃ.9.28-36) "እነሆም ከደመናው በእርሱ ደስ የሚለኝ ልጄ ይህ ነው እርሱን ስሙት።"

4. (ዮሐ.11:4) ኢየሱስም ሰምቶ፣ይህ ሕመም የእግዚአብሔር ልጅ በእርሱ ይከብር ዘንድ ስለ እግዚአብሔር ክብር ነው እንጂ ለሞት አይደለም አለ።

5. (-:27) አዎ! ጌታ ሆይ አንተ ወደ ዓለም የሚመጣው ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆንህ እኔ አምናለሁ አለችው። በዚህ ጊዜ ቁርአንና እስላሞች እንደሚሉት አምላክ ባይሆን ኖሮ፣አይደለም ተሳስተሻል፣እኔ አምላክ አይደለሁም ይላት ነበር።

6. (12:45) "እኔን ያየ የላከኝን አየ።" ከዚህም ላኪና ተላኪ ሁለት አካል መኖራቸውን ይናገራል።

7. (13:3) ኢየሱስ አብ ሁሉን በእጁ እንደ ሰጠው ከእግዚአብሔርም እንደመጣ ወደ እግዚአብሔርም እንደሚሄድ ዐውቆ ከእራት ተነሥቶ ልብሱን አኖረ።

8. (14:1) ልባችሁ አይታወክ በእግዚአብሔር እመኑ፣በኔም ደግሞ እመኑ። በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ———።

9. ኢየሱስም እኔ መንገድና እውነት፣ሕይወትም ነኝ፣በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም። እኔንስ ብታወቁኝ አባቴንም ደግሞ ባወቃችሁ ነበር።

10. (15-17) ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ። እኔም አብን እለምነዋለሁ፣ለዘለዓለም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላውን አጽናኝ (አማላጅ) እንዲሰጣችሁ። እሱም ዓለም የማያየውና የማያውቀው ስለሆነ ሊቀበለው የማይችል የእውነት መንፈስ ነው፤እናንተ ግን ከእናንተ ዘንድ በውስጣችሁም ስለሚኖር

ታውቁታላችሁ። በዚህም ሦስት መሆናቸውን ቁልጭ አድርጎ ተናግሯል። አብን አለምንኖሁ፣መንፈስ ቅዱስን ይልክላችኋል ብሉ፣ሦስቱንም፤ተለማኝ፣ለማኝ፣ተላኪ አድርጎ ሦስቱን አካላት ዘርዝሯል።
11. (23-24) ኢየሱስም መልሶ አለው፣የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል፣አባቴም ይወደዋል ወደ እርሱም እንመጣለን፣በእርሱም ዘንድ መኖሪያ እናደርጋለን። የማይወደኝም ቃሌን አይጠብቅም (እንደ አይሁድና እንደ አሕመድ ዲዳት ያለው)፡ የምትሰሙትም ቃል የላከኝ የአብ ነው እንጂ የኔ አይደለም።
12. (25) ከእናንተ ጋራ ስኖር ይህን ነገርኋችሁ፣አብ በእኔ ስም የሚልከው አጽናኝ (አማላጁ) መንፈስ ቅዱስ ግን ሁሉን ነገር ያስተምራችኋል፣እኔ የነገርኋችሁንም ሁሉ ያስታውሳችኋል።
13. (31) ነገር ግን እኔ አብን እንደምወደው ዓለም ያውቅ ዘንድ አብ ያዘዘኝን ሁሉ እፈጽማለሁ።
14. (15:9) አብ እኔን እንደ ወደደኝ እኔም እናንተን ወደድኋችሁ። (15) አገልጋይ ጌታው የሚያደርገውን ስለማያውቅ ከእንግዲህ ወዲህ አገልጋዮች አላላችሁም። ከአባቴ የሰማሁትን ሁሉ ስለነገርኋችሁ ወዳጆቼ ብያችኋለሁ።
15. (21)የላከኝን ስለማያውቁ በእኔ ምክንያት ይህን ሁሉ ያደርጉባችኋል።
16. (23) እኔን የጠላ አባቴንም ይጠላል። (26) ነገር ግን ከአብ የሚወጣና እኔም ከአብ የምልክላችሁ የእውነት መንፈስ፣አጽናኙ መንፈስ ቅዱስ ሲመጣ፣ስለኔ ይመሰክራል። እናንተም ከመጀመሪያ ጀምሮ ከኔ ጋራ አብራችሁ ስለነበራችሁ ትመሰክራላችሁ።
17. (16:1-3) ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ፣ይህን ሁሉ የነገርኋችሁ እምነታችሁ እንዳይናወጥ ብዬ ነው፤ከምኩራቦች ያስወጧችኋል፣እንዲያውም እናንተን የሚበድላችሁ ሁሉ፣እግዚአብሔርን የሚያገለግል የሚመስልበት ጊዜ ይመጣል። ይህንም የሚያደርጉት አብንም ሆነ እኔን ስለማያውቁ ነው።
18. (7-8) እኔ ግን እውነት እውነት እላችኋለሁ፣የኔ መሄድ ለእናንተ ይጠቅማችኋል፣ምክንያቱም እኔ ካልሄድሁ አጽናኙ (ጰራቅሊጦስ፣መንፈስ ቅዱስ) ወደእናንተ አይመጣም፣እኔ ከሄድሁ ግን ወደ እናንተ እልከዋለሁ። እርሱ በመጣ ጊዜ ስለ ኃጢአት፣ስለፍርድና ስለጽድቅም ሰዎችን ያስረዳል።
19. (12-15) ገና የምነግራችሁ ብዙ ነገር አለኝ፤ነገር ግን አሁን ይከብዳችኋል። የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል፤ምክንያቱም እሱ የሚናገረው የሰማውን እንጂ የራሱን አይደለምና ነው። እርሱ ወደ ፊት የሚሆኑትን ነገሮች ይነግራችኋል፤ የኔ ከሆነው ወስዶ ስለሚነግራችሁ፣እኔን ያከብረኛል።.........።

20. (28) ከአብ ዘንድ ወጥቼ ወደ ዓለም መጥቻለሁ፣እንደ ገናም ይህን ዓለም ትቼ ወደ አብ እሄዳለሁ።.........። (30) አንተ ሁሉን እንደ ምታውቅና ማንም ጥያቄ ሊያቀርብልህ እንደማትፈልግ አሁን ዐወቅን፣ስለዚህ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደ መጣህ እናምናለን።
21. (32:—፤) ነገር ግን አብ ከኔ ጋራ ስለሆነ ብቻዬን አይደለሁም።
22. በጠቅላላ አባትና ልጅ መሆናቸውን ለማወቅ የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ዐሥራ ሰባትን ያነቧል።
23. (19:7)አይሁድም እኛ ሕግ አለን፣ይህ ሰው ራሱን የእግዚአብሔር ልጅ ስላደረገ በሕጋችን መሠረት ሞት ይገባዋል አሉ።
24. (10:30) እኔና አብ አንድ ነን።
እነ አሕመድ ዲዳት ኢየሱስ አምላክ ነኝ፣የአምላክ ልጅ ነኝ አላለም፣እነ ጳውሎስ ለከኩበት ስላሉ፣ለመልስ ያህል የዚህ በላዩን ጠቀስን እንጂ መላ መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገር ስለአባትና ልጅ ነው። ዓለምም የሚድነው በእየቦታው እንደገለጥነው አሪትና ነቢያት ፍርጥርጥ አደርገው ተንቢተዋል፣እየሱስም አስተምሮአል፣ሐዋር ያትም ሰብከዋል። ገርብተዋል፣ ቀልብሰዋል፤ ርግጥ ነው፣ሥጋ በመልበሱ፣ሥጋ ለብሶ ዓለምን ለማዳን ከኀጢአት በቀረ ሰው የሠራውን ሁሉ ሠርቷል፣እህል በልቷል፣ውሃ ጠጥቷል፣ጥቂት በጥቂት አድጓል፤ተርቧል፣ተጠምቷል፣በሥጋው ሰው የሆነ አምላክ የማርያም ልጅነውና። አሁንም በሥጋው ሰው ስለሆነ፣ተገፏል፣ተሰቅሏል፣ሙቷል በመለኮቱ ሥጋውን ይዞ ያላንዳች ረዳት መቃብር ከፈቱልኝ፣መግነዝ ፍቱልኝ ሳይል ተነሥቷል፣ተነሥቶም ወደ ሰማይ በክብር ዐርጎ በአባቱ ቀኝ በሥልጣን በክብር ተቀምጧል።
እርግጥ ከመለኮቱ ከመዋሐዱ በፊት ሥጋውን የፈጠረ በመንፈስ ቅዱስ ወልድ እንዲዋሐደው ያደረገ፣ ያመቻቸ እግዚአብሔር አብ በሦስትነቱ ነው፤ስለዚህም አባቴም (በመለኮቱ) አምላኪየም በትስብ እቱ ይለዋል። አባቱም ልጄ ይለዋል፣መለኮቱን ሲያይ። ሐዋርያትም የኢየሱስ ክርስቶስ አባትና አምላክ እግዚአብሔር አብ እያሉ ያስተማሩ ስለዚህ ነው። (ዮሐ.20:17፤2ቆሮ.1:3፤ኤፌ.1:3፤1ጴጥ.1:3፤17) እሱም ራሱ እንደ መለኮት ሲያስብ አባቴ እንደ ሰውነቱ ሲያስብ አምላኪያ ሲል ኑሯል፣አስተምሯል።
ይህ ሁሉ ምስክር እያለ ነው እነዲዳት፣ኢየሱስ አምላክ ወይም የአምላክ ልጅ አይደለም የሚሉት።
እስከዚህ የአብን አባትነትና የወልድን ልጅነት፣የመንፈስ ቅዱስን እስትንፋስነት በሐዲስና በብሉይ ከገለጥን በቁርአን ደግሞ እንዴት እንደሆኑ እንይ።

## ሥላሴ በቁርአን

(ሱራህ 4: 171) እናንተ የመጽሐፍ ሰዎች ሆይ!በሃይማኖታችሁ ወሰንን አትለፉ፣በአላህም ላይ ከእውነት ሌላ አትናገሩ የማርያም ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር መልእክተኛና ቃሉም ነው፣ከእሱ የሆነ መንፈስም ብቻ ነው።

እኛስ ምን እንላለን? ቃለ እግዚአብሔር የእግዚአብሔር ቃል ከማለት በቀር። ለእነ ዲዳት የእግዚአብሔር ልጅ ስንል በወሲብ የወለደው ነው የምንል ይመስላችዋል። ከዚህ ላይ በቁርአኑ እንደተገለጠው በእንደበቱ የሚወጣ ቃሉ እንጂ ከማርያም በወሲብ የወለደው የሚል ጤነኛ ክርስቲያን የለም። ለምን? ቢሉ እግዚአብሔር አብ መለኮት መንፈስ እንጂ ሥጋዊ አይደለምና። ሥጋ የለውምና፣ትስብእትን የተጎናጸፈ ሰው አይደለምና፣ ቀጥሎም እሱም ወደ ማርያም አንድ መንፈስ አምጥቷል አለ፤ይህም የእግዚአብሔር መንፈስ፤በዚህም መንፈስ ቅዱስ ለእንጽሖ በክርሠ ድንግል ማደሩን ይናገራል። (ሱራህ:19:34) የማርያም ልጅ ኢየሱስ በእሱ የሚጠራጠሩበት እውነተኛ ቃሉ ነው። ማስተዋል የለ፣የነአሕመድ ነገር፣እኛስ እውነተኛ ቃለ እግዚአብሔር ነው እንላለን እንጂ ምን እንላለን? ከዚህ አስቀድሞም በሉቃስ ወንጌል(4:18-20)የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ላይ ነው፤መልካም ዜናን ለድኆች እንዳበስር ሹሞኛል፤ለታሰሩት መፈታተን፣ ለታወሩት ማየትን እንዳውጅና የተጨቁኑትንም ነጻ እንዳወጣ ልኮኛል፤እንዲሁም እግዚአብሔር ሕዝቡን የሚያድንበትን የጸጋ ዓመት እንዳስታውቅ ልኮኛል። ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ምዕራፍ :19:30: ሕፃኑም አለ፣እኔ የእግዚአብሔር ባርያ ነኝ (በሥጋው) መጽሐፍን ሰጥቶኛል፣ነቢይም አድርጎኛል። በየትም ሰፍራ ቢሆን ቡሩክ አድርጎኛል። ለእናቴም ታዛዥ አድረጎኛል፤ትዕቢተኛና እምቢተኛም አላደረገኝም።——።

በመንፈስ እነዚህ ሁለቱ ጥቅሶች በምን ይለያያሉ? ዓለምን ለማዳን በትሕትና የመጣው የወልደ እግዚአብሔር ቃላት ናቸው። ምስጢረ ሥላሴን ወስኖ አስተምሮት የዐረገ ክርስቶስ ነው። እነ ዲዳት ግን በአራተኛው መቶ ዘመን በ325 በኒቅያ ነው የተወሰነው ይላሉ፤ተሳስተዋል፣ለምን ቢሉ? ከጴራቅሊጦስ እንሥቶ እስከ ዘመነ ቆስጠንጢኖስ ያለው ዘመን ለክርሲታያን ዘመነ ሰማዕት፣ዘመነ ሰደት ይባላል፤በዚህ ዘመን ክርስቲያኖች እንደልባቸው ለመገናኘትና ተገናኝተውም እንደልባቸው ለመናገር ስላልቻሉ፣በቀላሉ በኢየሱስ ክርስቶስ ያመነ ሁሉ ክርስቲያን ይባል ነበር፤ቆስጠንጢኖስ በነገሠ ጊዜ ግን መጻሕፍት ተጠንተው፣ምስጢራት በቅዱሳት መጽሕፍት ተመርምረው ተወስኑ፤መናፍቃንም ተወገዙ፣ኢምሁራንም ተማሩ።

# ምዕራፍ 2፤

## ምስጢረ ሥጋዌ

ምሥጢረ ሥጋዌ በሰፊው ለክርስቲያን በአንድ እረኛ አንድ መንጋ ምዕራፍ አንድ ተጽፎል። ከዚህ ደግሞ ለነዲዳትና ለመሰሎቹ በመልስና በመረጃ መልክ በአጭሩ ቀገልጧል። እሱም በመጀመሪያ የኦሪትን ከዚያ የቁርአንን ስለአዳም መውደቅ ታሪክ መነሻ አድርጎ ታትቷል።

(ዘፀ 2:7) ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር አምላክ ከመሬት አፈር ወስዶ፣ሰውን ከአፈር አበጀው፣በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስ እፍ አለበት። ሰውም ሕይወት ያለው ፍጡር ሆነ።

(15) ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር አምላክ ሰውን በኤደን የአትክልት ቦታ አኖረው፤ይህንም ያደረገው ሰው የአትክልቱን ቦታ እንዲያለማ ውና እንዲኩተኩተው ነው፤እግዚአብሔር አምላክ ሰውን በአትክልቱ ቦታ ከሚገኙት ዛፎች ሁሉ ፍሬ ብላ፤ነገር ግን ደጉን ከክፉ ለመለየት የሚያስችል ዕውቀት ከሚሰጠው ዛፍ ፍሬ አትብላ፤ምክንያቱም ከዚህ ፍሬ በበላህበት ቀን በርግጥ ትሞታለህ ብሎ አዘዘው።

(18) እግዚአብሔር አምላክም አለ፣ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም። የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት።

(20)......፤እግዚአብሔር አምላክም በአዳም ከባድ እንቅልፍን ጣለበት እንቀላፋም፣ከጎድኑም አንዲት አጥንት ወስዶ ስፍራውን በሥጋ ሞላው፤እግዚአብሔር አምላክም ከአዳም የወሰዳትን አጥንት ሴት አድርጎ ሠራት፤ወደ አዳምም አመጣት፣አዳምም ይህች አጥንት ካጥንቴ፣ሥጋም ከሥጋዬ ናት እርስዋ ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባል። ስለዚህ ሰው አባትና እናቱን ይተዋል፣ ከምሽቱም ይጣበቃል፤ሁሉም አንድ ሥጋ ይሆናሉ። አዳምና ምሽቱ ሁለቱም ዕራቁታቸውን ነበሩ። አይተፋፈሩምም ነበር።

(3:1......፣) አዳምና ሔዋንም በዚህ ሁኔታ በገነት መካከል የፍጥረታት ሁሉ ገዥዎች ሁነው ሲኖሩ ሰይጣን ቀናና በእባብ ተመስሎ የተከለከለችውን ዕፅ እንዲበሉ በማድረጉ የአምላካቸውን ትእዛዝ በመተላለፋቸ ው ተረግመው ከገነት ወጡ። ይህ ታሪክ በቁርአን ደግሞ እንዲህ ነው፤ (ላሟ ምዕራፍ :2:34-38) መላእከትንም ለአዳም ስገዱ ባልን ጊዜ ከዲያብሎስ በቀር ሁሉም ሰገዱ፣እሱ ግን እምቢ አለ፣ኮራም በዚህም ከከሐዲዎች ተቆጠረ አዳም ሆይ !አንተ ከነምሽትህ በገነት ተቀመጥ፤ ከርሷም በፈለጋችሁት ስፍራ በሰፊው ተመገቡ፣ግን ይህችን ዛፍ አትቅረቡ፣ከበደለኞች ትሆናላችሁና አላነም። ከርሷም ሰይጣን አዳለጠ (አሳሰቶ) በውስጡ ከነበሩበት ድሎት አወጣቸው። አንዱ ለሌላው ጠላት ሁናችሁ ውረዱ፣ለእናንተም በምድር ላይ እስከ ጊዜያችሁ ድረስ

መጠሊያና ሥንቅ አለላችሁ። በአራትም ሆነ በቁርአን እግዚአብሔር ትእዛዙ በመጣ_ሉ ተናዶ አዳምና ሔዋንን ከገነት እንዳስወጣቸው ቁልጭ ተደርጎ ተጽፏል። ቁርአን ከዚህ በኋላ ስለመታረቅና ድኅነት የሚናገረው የለም፤ከአሕዛብ ልማድ ከመጣው መሥዋዕተ እንስሳ በቀር። ኦሪትና ወንጌል ግን በትንቢትና በፍጻሜ አምላክ ዓለምን የታረቀው በልጁ ደም መሆኑን አብራርተው፤ ነገረው ደምድመዋል አዳም የፈጣሪውን ትእዛዝ በመተላለፉ ከገነት ወጥቶ፤እሱ ብቻ ሳይሆን በመላ ዘሩም በምድረ ፍዳ ሲኖር በሦስት አካላት ሲመሰገን የሚኖር እግዚአብሔር በዳዩን አዳምን ይቅር ለማለት ወሰነ። (ዘፍ. 3:1-4) ለዚህም መታረቂያ መሥዋዕት አስፈለገ። በደሉም ግዙፍ ስለሆነ ለመሥዋዕቱ የሰውና የእንስሳ ደም የማይበቃ ሆነ። የስላሙ የመሐመዱ፤የቁርአኑ አምላክ ቢሆን ኑሮ ያለፍርድ እንደ ዐጤ ከለሚሰራ ምሬሃለሁ ቢል ይበቃ ነበር። የአብርሃም አምላክ ግን እውነተኛ ዳኛም መሐሪም ስለሆነ፤ተቀዳሚና ተከታይ የሌለው ልጁ ሥጋ ለብሶ እንዲሠዋ ወሰነና ላከው። (ዘፍ.3:15) በአንተና በሴቲቱ መካከል፤በዘርህና በዘርዋ መካከል ጠላትነትን አኖራለሁ፤እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል አንተም ሰኮናውን ትቀጠቅጣለህ ባለው መሠረት፤በዳይም ተበዳይም ልጅ ልጃቸውን አዋጡና የአምላክ ልጅ እግዚአብሔር ወልድ፤ኢየሱስ ክርስቶስ ዐማኑኤል በሚባሉ አስማት፤ ሥጋ ለብሶ፤ትስብእትን ተዋሕዶ፤የሰውን ልጅ ጠላት ሰይጣንን ድል ነሥቶ፤ከዲያብሎስ ባርነት ከሲኦልና ከገሃነም ሥቃይና ኩነኔ አዳነ። የተበዳይና የበዳይ ልጅ (ዘር) በተዋሕዶ ተሰቅሎ ዓለምን አዳነ። ከሦስቱ ሥላሴ፤ከሠለስቱ አካላት አንዱ በተለየ አካሉ እግዚአብሔር ወልድ ሥጋ ለብሶ፤ተሠቃይቶ፤ተገፎ፤ተገርፎ፤ተሰቅሎ ዓለምን እንዲያ ድንና ከአባቱም ከራሱም ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ እንዲያስታርቅ እንዴት እንደ ተወሰነ በሥሉስነት ሲመሰገን ከሚኖረው ከገናናውና ከረቂቁ አምላክ አንዱ እግዚአብሔር በቀር ማንም አያውቅ። ተበዳዩ አምላክ በዳዩን ሰውን ይቅር የሚልበት ጊዜ ሲደርስ፤በመበሥሩ በቅዱስ ገብርኤል አማካይነት፤የቅድስት ድንግል ማርያምን ፈቃድ እንዳገኘ፤እንድያ፤ተቀዳሚ፤ተከታይ የሌለው ልጁን ሥጋ እንዲለብስ ወደ ማርያም ላከ።

በልደት ሦስቱም፤አብ፤ወልድ፤መንፈስ ቅዱስ ተስማምተዋል፤ተባብ ረዋል። አብ መርጧል፤አጽንቷል፤መንፈስ ቅዱስ በላያዋ ላይ አድሮ ወላዲተ አምላክ ማኅደረ መለኮት እንድትሆን አመቻችቷል፤አዘጋጅቷ ታል። እግዚአብሔር ወልድም ከነፍሷ ነፍስ ከሥጋዋ ሥጋ ነሥቶ ፍጹም ሰው ሁኗል። ስለዚህም በአንድ አካል የተዋሐደ ሰውና አምላክ ይባላል። ስለዚህም በአንድ አረኛ አንድ መንጋ በተሰጠው ውሳኔ

አንድ መለትስ ይባላል፤(መለትስም ሰውና አምላክ ወይም መለክትና
ተሰብእት ማለት ነው) በመለኮቱ የአብ ልጅ፣በትሰብእቱ(ሥጋው)
የማርያም ልጅ ይሉሃል ይህ ነው። በግዕዙም ወልደ አብ በመለኮቱ
ወልደ ማርያም በትሰብእቱ ይላል ውሳኔው። ሰው አምላክ፣አምላክ
ሰው ሆነ የሚያሰኘውም ይህ ነው። በመለኮቱ አምላክ አማልክት፣ፈጣ
ሬ ዓለማት ሲሆን፣በትሰብእቱ ደግሞ ንጉሠ ነገሥት፣ሊቀ ካህናት፣ሊ
ቀ ሰማዕት፣ ሊቀ ነቢያት ነው። እንደ ሰውነቱ፣ሰው መሆኑን
ለማጠየቅ ትንሽ በትነሽ አድጓል፣እንደ ሕፃናት አልቅሷል፣ደክሟል፣ተ
ርቧል፣ተጠምቷል፣ምራቅ፣ደም ወጥቶታል፣ሙቷል። አምላክ እነደ
መሆኑ፣አምላክነቱን ለማጠየቅ(ለማስረዳት)በድንግልና ተወልዷል፣በተ
ዘጋ ቤት ገብቷል፣በባሕር ላይ ያለ ጀልባ ሂዷል፤ከሞተና ከተቀበረ
በኋላ መቃብር ክፈቱልኝ መግነዝ ፍቱልኝ ሳይል ተነሥቷል፤በዚህም
አንድ መለትስነቱን እነረዳለን። መለትስ መሆኑን ያልተረዱ ብዙ
ሰዎች ትሰብእትን ሲያይ የተነገሩትን ቃላት፣ጥቅሶች፣ዐረፍተ
ነገሮች፣ባነበቡ ቁጥር ለማረም ወይንም ለማጣመም ይሞክራሉ። ይህ
ግን ካለማወቅ የመጣ ነው፤ልኩ መለኮቱን ሲያዩ የተነገሩትን
ለመለኮቱ ሰጥቶ በመለኮት ባሕርይ መተርጎም፣በትሰብእት፣ለትሰብእት
የተነገ ሩትን ደግሞ ለትሰብእት ሰጥቶ ካነበቡ በኋላ አንድ አካል
አንድ መለትስ ብሎ አስታርቆ አስማምቶ መፍታት ነው። ኢየሱስ
ክርስቶስ እግዚአብሔር ወልድ የአብና የማርያም ልጅ፣በአንድ
መለትስ መሆኑን ለመረዳት በሰፊው የሚፈልግ ሁሉ ከሁሉም ሁሉን
ይወቅ 47-67 ያለውን መግለጫ ከጥቅሶቹ ጋራ እያዛመደ እንዲያነብ
ይጠቆማል። ከዚህ ግን ፍጹም አምላክ እና ፍጹም ሰው በአንድ አካል
አንድመለትስ መሆኑን ለማስረዳት የሚከተሉት ተጠቅሰዋል፤(ዮሐ.1:1-
14)3:1618፤መዝ.2:68፤109:4፤ሉቃ.23:34፤ዮሐ.10:30፤14:6፤20:1
7፤ኢሳ.61:13፤ሉቃ.4:18-19፤53:11-12፤ዮሐ.14:28፤31፤መዝ.
21:1፤ማቴ.27:46፤ሉቃ.13:32፤2ቆሮ.1:3፤11:31፤ኤፌ.1ኢሳ.3፤
17፤ፊል. 2:6፣10፤ 1ጴጥ.1:3፤ 2ጴጥ 1:17-18፤ግብ. 2:24፤ራእ.
1:6፤ 3:12፤ዮሐ. 6:37-39፤ 7:29፤ 1:36፤ 8:42፤ 9:4፤ሉቃ.4:43፤
ገላ.4:4፤ ዮሐ.4:9) ከቅዱሳት መጻሕፍት አምላክና ሰው መሆኑን
ለመግለጥ የተጻፉ ለቁጥር የሚያዳግቱ ብዙ ጥቅሶች አሉ።
ቁርአንም የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ያምናል፤ይህንም በምስጢረ
ሥላሴ ከዚህ በፊት አስረድተናል። ከዚህ ደግሞ ሀ. (ሉቃ.19:17-
22፤)ማርያምን ከቤተሰብዋ ወደ ምሥራቃዊው ክፍል በተነሣች ጊዜ
በተገለለች ጊዜ አውሣ። መንፈሳችንንም ወደ እሷ ላክን፤እሱም ፍጹም
ሰው መስሎ ታያት። እስዋም እኔ ከአንተ በጌታ እጠበቃለሁ፣ጌታህን

ፈሪ እንድሆን አለችው። እሱም እኔ ንጹሕን ልጅ ለአንቺ ልሰጥሽ ከጌታሽ የተላክሁ ነኝ አላት። እሷም ወንድ ሳይነካኝ አመንዝራም ሳልሆን እንዴት እወልዳለሁ አለችው። እሱም ጌታሽ ይህ ለኔ ቀላል ነው፤እኛ ለሰው አስተርእዮና የኛንም ምሕረት መግለጫ እናደርገዋለን፣ይህም የተወሰነ ነው ይላል። እስዋም ፀነሰችው ወደ ሩቅ ቦታም ሸሸች።

ሊ, (ሱራህ: 2: 253) ከእነዚህ መልእክተኞቻችን ግማሹን ከሌሎች በላይ አበለጥን። እኩሎቹን አላህ አነጋገራቸው፣ሌሎችን ደግሞ በደረጃ ሱራህ:19:) አበለጣቸው። ለማርያም ልጅ ኢየሱስ ግን የአምላክነቱን ግልጽ ምልክት (ተአምር) ሰጠነው፤በመንፈስ ቅዱስም አበረታነው።

ሐ, (ሱራህ: 3: 45-48) መላእክት ያሉትን አስታውሥ፤ማርያም ሆይ! አላህ ከርሱ በሆነው ቃል፣ስሙም ኢየሱስ ክርስቶስ የማርያም! ልጅ የሚባል፣በዚህ ዓለምና በመጭው ዓለም ከባለሟሎቹ ሁሉ የከበረ ልጅ ሲሰጥሽ የምሥራች ይልሻል (ያበሥርሻል) እሷም ጌታዬ ሆይ!ሰው ሳይነካኝ ለኔ እንዴት ልጅ ይኖረኛል? አለች። ነገሩ እንደዚህ ነው፣አላህ የሚሻውን ያደርጋል፤አንዳችን ነገር በሻ ጊዜ፣ሁን ይለዋል ወዲያውም ይሆናል። ብራና ባይወደድ ኑር ቁርአን መደጋገም ልማዱ ስለሆነ ብዙ መጥቀስ ይቻላል።

ከዚህ የተረፈውን ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው ነው በሚሉት እርእስት ይመለከቷል።

# ምዕራፍ 3፣

## የቅዱሳት መጻሕፍት ታማኝነት፤

ምስጢረ ሥላሴና ምስጢረ ሥጋዌ
ያለፉት ሁለት ምዕራፎች ምስጢረ ሥላሴና ምስጢረ ሥጋዌ የቅዱሳት መጻሕፍትን
የተረጋገጡት በቅዱሳት መጻሕፍት ነው። የቅዱሳት መጻሕፍትን ታማኝነት ለማበተባበል እነዲዳት ሞክረዋል፤ቁርአን ግን ያረጋግጣል። ሁሉንም እናስከትላለን። (2 ጢሞ.3 :16-17) ቅዱስ መጽሐፍ በሙሉ በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት የተጻፈ ነው፤እርሱ እውነትን ለማስተማር፤የተሳሳቱትን ለመገሠጽ፤ስሕተትን ለማረምና ለትክክለኛ ኑሮ የሚበጀውን መምሪያ ለመስጠት ይጠቅማል። የሚጠቅመውም የእግዚአብሔር ሰው ፍጹም እንዲሆንና ማንኛውንም መልካም ሥራ ለመሥራት ብቁ እነዲሆን ነው።

በዚህ መሠረት የቅዱሳት መጻሕፍት ደራስያን ሁለት ሁለት መንፈስ እግዚአብ
ናቸው፤አንድኛው የሃይማኖትን ሂደት የሚመራው
ሔር መንፈስ ቅዱስ፤ሁለተኛው የእያንዳንዱ መጽሐፍ አዘጋጅ ራሱ ደራሲው። ለሁለቱም ድርሻ ድርሻ አላቸው፤መንፈስ ቅዱስ በሰውር በደራሲው መንፈስ አድሮ ይመራል፤ደራሲው ደግሞ ብራና ፍቆ፣ቀ ምጾ፣ቀለም በጥብጦ፣የሚጽፍበትን ቋንቋ አጥንቶ፣በተቻለ ዐቅም ተዘጋጅቶ ይቀርባል። እንደዚህ ያለውን በፍጹም አእምሮው ያለውን ሰው መንፈስ እግዚአብሔር ይመራዋል እንጂ ዕፀ ፈርስ ጠጥቶ እንደ አበደ፤አብዶም እንደሚለፈልፍ አያስቀባጥረውም፤ወይም አብሾ ጠጥቶ እንደ ሰከረ አያስቀባጥረውም፤ያለዚያም ዛር እንደ ያዘው አያስጎራውም።

ስለዚህ ቅዱስ መጽሐፍ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ስለተጻፈው በይዘቱ አይጠላም፣አይፋለስም፣አይጋጭም፣ግን ደራሲው ሰው በመሆኑ በአር ስሕተ ሱ ድርሻ፤የቃላት ግድፈት፤የአገባብ (የአሰካክ) የጸታ የግሥ ጊዜ ስሕተ ት ይገኙበታል፤ሩቅና ቅርብ፤አይጠብቅም፣ ሴትና ወንድ (ጾታ) አይለይም። በትርጉምም የዘሩን ቋንቋ ስልት ወደ ሚገለበጥበት ቃል ለቃል ይመልስና፣ብዙ ጊዜ በተቀባዩ ቋንቋ ግጭት ያጋጥመዋል። ከዚህ በቀር እነአሕመድ ዲዳት እንደሚሉት ግጭት የለም፤እንደ ቁርአንም አይፋለስም። እንደ ቁርአን የያዘውን ርእስ ሳይጨርስ፣ርእስ መከተል በአንድ እንዳልተማረ ከአምስተኛ ክፍል በታች እንዳለ ሕፃን ተማሪም ርእስ ዐሥራ አምስት ሐሳብ አይናገርም። የያዘውን ሐሳብ ሳይጨርስም ሌላ ሐሳብ ትዝ አለኝ ብሎ አይዘፈንቅም። መጽሐፍ ቅዱስ ተሰብስቦ ከተጠረዘ እንኳንስ በአመራርና በይዘት ይቅርና በአንድ ቀለም ወይም ቃል እንኳ ቢሆን ብዙ ያናግራል፤ሲያናግር ሲያጩቃጭ ቅ ኑሮአል።ይታረማል ቢባልስ መጽሐፍ ቅዱስን ያህል የእግዚአብሔር ቃል፤ከእግዚአብሔር ጋራ የተነጋገሩ ነቢያት፤ሐዋርያት፣የተማሩ

ሊቃውንት የጻፏት፣ራሱ ወልደ አምላክ ያስተማረው፣እንዴት ጤና በሌለው፣ባልተማረ፣ፊደል ባልቆጠረ ሰው በእየጊዜው በተለፈለፈ፣ከእሱ በፊት የነበረ አዋልድና የባልቴት ተረት ተይዞ፣አንድ አዲስ ነገር ያልያዘ ዝብርቅርቅ እርስ በእርሱ የሚፋለስ መጽሐፍ ይዞ ይነቅፋል? ከዚህ ላይ ደርግ በመጣ ጊዜ የደ ረሰ አንድ ቀልድ መሳይ ታሪክ ትዝ ይለኛል። ሁለት የለውጥ ሐዋረያት ፍኖተ ሰላም ሂደው ስለለውጡ የመሰላቸውን ካወሩ በኋላ፣ለተሰብሳቢው የጥያቄ መብት ይፈቅዳሉ፣ከተሰብሳቢዎች አንዱ እጁን ያወጣና ጌታው! ለምን ነው? ጃንሆይን ያወረዳችኋቸው? ብሎ ይጠይቃል፣የለውጥ ሐዋርያም ሌባ ስለሆኑ ነው ብሎ ይመልሳል፤ጠያቂም ታዲያ አንድ ሌባ በመቶ ሃያ (120) ነው ወይ የሚለውጥ? ብሎ ቁጭ አለ። ይዘቱ፣አመራሩ፣ሂደቱ የተዝረጠረጠ መጽሐፍ ይዞ፣ሆኄና ቀለም መጽሐፍ ቅዱስ ጎደለው ብሎ ይወቅሳል። ለምን ቢሉ የራሱን ጉድለት ሰው እንዳያይበት።

<u>ምሳሌያት፤</u>

ሀ. አላህ አንድ ነው ይላል፤ ራሱ በነጠላም በብዙም ይናገራል፤(ሱራህ:4:164.) ከዚህ በፊት ያነጋልህን ያላነጋገልህም ካለ በኋላ፣አላህ በቀጥታ ለሙሴ ተናገረ ብሏል። እኛና ነጠላ አላህ በአንድ ዐረፍተ ነገር አይሄድም።

ለ. (5 :14) ስለዚህ በመካከላቸው ጠላትነትና ጠብ አላህ የእጃቸውን ሥራ እስከ ሚነግራቸው እስከ ትንሣኤ ድረስ አንሥተናል። አሁንም ነጠላና ብዙ። ቅዱሳት መጻሕፍት ግን ልክ እንደሆኑ ራሱ ቁርአን ከ40 ጊዜ በላይ እየመሰከረ ጽፎአል፤ለምሳሌ፤

ሀ, (ሱራህ. 5:46)በውስጧ መመሪያና ብርሃን ያለባት እሪትን አወረድን፤ትእዛዝን የተቀበሉት ነቢያትም በአይሁድ ላይ በእሷ ይፈርዱሉ።..........። በነቢያት ፈለግም ላይ ለማርያም ልጅ ኢየሱስ እሪትን የምታረጋግጥ ወንጌልን ሰጠነው። እስዋም በውስጧ ቀትታና ብርሃን አለባት።...... የወንጌል ባለቤቶችም እግዚአብሔር ባወረደው በወንጌል ይፍረዱ። እግዚአብሔር ባወረደው። የማይፈርድ ዐመፀኛ ነው። (ራሱ መሐመድም)

ቢ, ወደ ቀኝ እንድትመሩ ለሙሴ የጽድቅንና የኀጢአትን መስፈርት መጽሐፍ ሰጠን። (ሱራህ 2:53 87፤)

ሐ, በእርገጥ ለሙሴ መጽሐፍ ሰጥተን በኋላውም አእላፍ ልኡካን (ነቢያት)እንዲከተሉት አደረግን። ለማርያም ልጅ ኢየሱስም የአምላክ ሥልጣን እንዳለው ግልጥ መረጃ ሰጥተን በመንፈስ ቅዱስ አጠናነው። ከዚህም በላይ የቅዱሳትን መጻሕፍት ታማኝነትና እውነተኛነት የሚከተሉት የቁርአን ጥቅሶች ያረጋግጣሉ። (ሱራህ: 121፤ 144፤ 174፤ 176፤ 213፤ 285፤ ሱራህ 111:7፤ 20፤ 23፤ 48፤78፤ 81፤100፤ ሱራህ 4: 46፤ 51፤105፤ ሱራህ:6:155፤ ሱራህ 119: 47፤

ከዚህም በላይ ይህን ያህል መጥቀስ ይቻላል። ይህ ሁሉ ምስክር እያለ ነው እንዲዳት መጽሐፍ ቅዱስ ተቆነጽሏል የሚሉት፣ክኪሳቸው አውጥተው። ምክንያቱም አመዛዝና መረዳት አነጻጽሮ ማንበብ አያውቁምና ነው።

# ምዕራፍ :4፤

## ኢየሱስ ፍጹም አምላክ ነው፤የአምላክም ልጅ ነው፤

ብለዋል፤በቁርአን ሳይቀር እነ ዲዳት ኢየሱስ አምላክ አይደለም ብለዋል፤በቁርአን ሳይቀር እውነተኛነታቸውና፣ታማኝነታቸው በተረጋገጠላቸው ቅዱሳት መጻሕ ፍት፣ብሉይና ሐዲሳት መሠረት ኢየሱስ ፍጹም አምላክ፣በመለትስ ፍጹም ሰው ነው:: (ከገጽ: 4.17: ኢየሱስ እውን ፈጣሪ ነውን?) ይህንም የሚሉት ምስጢረ ሥጋዌን ባለማወቃቸው ነው::ቃለእግዚአብ ሔር፣ ወልደ እግዚአብሔር፣በመለኮቱ ወልደ አምላክ (የአምላክ ልጅ) በትስብእቱ (በሥጋው) የማርያም ልጅ፣ፍጹም ሰው፣ከኀጢአት በቀር፤ወልደ አብ በመለኮቱ ወልደ ማርያም በትስብእቱ የሚያሰኘው ም ይህ ነው:: ይህም ማለት መለኮትና ትስብእት ተዋሕደው በክርስቶስ አንድ አካል ሁነዋል:: በመለኮት ባሕርዩ አብ ልጅ ይለዋል፤በትስብእት ባሕርዩ ደግሞ፣ከነፍሷ ነፍስ፣ከሥጋዋ ሥጋ ነሥቶ አንድ አካል ሁኖ ስለተወለደ ማርያም ልጄ ትለዋለች:: ስለዚህ በመለኮቱ የአምላክነት ቅጽል፣ግብር፣ቅድመ ዓለማዊነት፣ዘላለማዊነት አለው፣ነው፣በሥጋው ደግሞ ከኀጢአት በቀር ሥጋዊ ሰው የሚያደርገውን ሁሉ ፈጽሟል፣ከ ዚህ በፊት እንዳየነው በጥቂት በጥቂት አድጓል፣ደክሟል፣ተርቧል፣ተ ገርፏል፣ተሰቅሏል፣ሙቷል፣በሞተ በሦስተኛው ቀን ሥጋን የተዋሐደ መለኮት ነውና፣መግነዝ ፍቱልን፣መቃብር ክፈቱልኝ ሳይል ተነሥቶ፣ለአርባ ቀን ትንሣኤውን ለሐዋርያትና ደቀ መዛሙርቱ እያዩት፣መንፈስ ሲገልጥ ስንብቶ፣በአርባኛው ቀን ደቀ መዛሙርቱ እያዩት፣መንፈስ ቅዱሳን በጥቂት ቀን ውስጥ የሚልክላቸው መሆኑን ገልጦ፣ ተሰፋ ቅዱሳን በጥቂት ቀን ውስጥ የሚልክላቸው መሆኑን ገልጦ፣ ተሰፋ ቅዱሳን በጥቂት ቀን ውስጥ የሚልክላቸው መሆኑን ገልጦ፣

ስጥቶ ወደ ሰማይ ዐርጎ በአባቱ ቀኝ በክብር ተቀምጧል::

ፍጹም አምላክ ወልደ አምላክ ለመሆኑ ከነቢያት ጀምሮ የተነገሩትን የሚከተሉትን ጥቅስ እናቀርባለን፤

1. (ኢሳ.9:6-9) ሕፃን ተወልዶልናልና ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፣አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፣ስሙም ድንቅ መካር፣ኃያል አምላክ፣የዘለዓለም አባት፣የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል:: ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘለዓለም ድረስ በፍርድና በጽድቅ ያጸናው ይደገፈው ዘንድ በዳዊት ዙፋንና በመንግሥቱ ላይ አለቅነቱ ይበዛል፤ለሰላሙም ፍጻሜ የለውም የእግዚአብሔር ቅንዓት ይህን ያደርጋል:: የሚወለደውም ሕፃን ኃያል አምላክ እንደሆነ በዚህ ጥቅስ ቁልጭ ብሎ ተገልጧል::

2. (ኢሳ. 7:14) ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል፤እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም ዐማኑኤል ብላ ትጠራዋለች:: ዐማኑኤል ማለትም እግዚአብሔር ከእኛ ጋራ ነው ማለት ነው:: እግዚአብሔር በዓለም ሁሉ ሙሉ ነው፤እግዚአብሔር

ከእኛ ጋራ ነው ማለት ግን እንደኛ ሥጋ ለብሶ በመካከላችን ሲመላለስ ይታያል ማለት ነው።

<u>አምላክ አይደለም የአምላክ ልጅ አይደለም ብለዋል፤ለዚህ ምስክር፣</u>

3. <u>መጀመሪያ አባቱ እግዚአብሔር አብ፤</u>

(መዝ.2: 6-9) እኔ ግን ንጉሤን ሾምሁ፣በተቀደሰው ተራራዬ በጽዮን ላይ፣ትዛዙን እናገራለሁ፤እግዚአብሔር አለኝ አንተ ልጄ ነህ፣ እኔ ዛሬ ወለድሁህ፣ለምነኝ አሕዛብን ለርስትህ፣የምድርንም ዳርቻ ለግዛትህ እሰጥሃለሁ፤በብረት ብትር ትጠብቃቸዋለህ፣እንደሸክላሠሪ ዕቃም ትቀጠቅጣቸዋለህ። በዚህም የራሱን አባትነት የልጁንም ልጅነትና ባለ ሥልጣን መሆን እኔ ዛሬ ወለድሁህ———። ብሎ (መዝ.109:1) አረጋግጧል።

4. እግዚአብሔር ጌታዬን:-ጠላቶችህን ለእግርህ መቀመጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው።.በዚህም በቀኜ ተቀመጥ ሲል እኩያው መሆኑን ይገልጣል።

5. (ማቴ.3: 16-17) ኢየሱስ ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ከውኃው ወጣ፣እነሆም ሰማያት ተከፈቱ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንደ ርግብ ወርዶ በእርሱ ላይ ሲመጣ አየ፣እነሆም ድምፅ ከሰማያት መጥቶ፣በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ። እነ አሕመድ ዲዳት ልጅ የለውም ይላሉ፣እግዚአብሔር ግን እንዲህ እያለ ይመሰክራል። (ማቴ. 17: 5፤ማር.1: 11) የሚከተሉት ጥቅሶች ደግሞ የዚህተመሳሳዮች ናቸው፤(ማቴ.12:18፤ማር.1:11፤ኤፌ.1:6፤ቆላ.1:13፤ ዕብ.5:5፤ 2ጴጥ.1:17)

6. <u>ኢየሱስ ክርስቶስ ስለራሱ፤</u>

እነ ዲዳት ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ አምላክ ወልደ አምላክ ነኝ አላለም ይላሉ፤ለዚህ ስሕተት ማቃኛም የሚከተሉትን ጥቅሶች እነሆ! (ሉቃ.2: 48-49) ባዩትም ጊዜ ተገረሙ፤እናቱም ልጄ ሆይ! ለምን እንዲህ አደረግህብን? እነሆ አባትህና (አሳዳጊህ ለማለት) እኔ እየተጨነቅን ስንፈልግህ ነበርን አለችው፤እርሱም ስለምን ፈለጋችሁኝ? በአባቴ ቤት እሆን ዘንድ እንዲገባኝ አላወቃችሁምን? አላቸው። ቤተ መቅደሱን ነው ያባቴ ቤት ያለው።

7. (ዮሐ.3: 14-18) ሙሴ በምድረ በዳ እባብን እንደ ሰቀለ፣እንዲህ በእሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይ ጠፋ የሰው ልጅ ይሰቀል ዘንድ ይገባዋል። በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና። ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ

ዓለም አላከውምና፣በእርሱ በሚያምን አይፈረድበትም፣በማያምን ግን
በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁኑኑ ተፈርዶበታል።
ይህን የተናገረው ስለራሱ የአምላክ ልጅነት አልተናገረም የተባለው
ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።
8. (4:25-26) ክርስቶስ የሚባል መሲሕ እንዲመጣ አውቃለሁ፣እሱ
ሲመጣ ሁሉን ይነግረናል አለችው። ኢየሱስም የማናግርሽ እኔ እሱ
ነኝ አላት።
9. (5: 15——:)——፣ሰውየውም ሂዶ ያዳነው ኢየሱስ እንደሆነ
ለአይሁድ ነገረ። ስለዚህም በሰንበት ይህን ስላደረገ አይሁድ ኢየሱስን
ያሳደዱት ነበር፣ሊገሉትም ይፈልጉ ነበር፣ኢየሱስ ግን አባቴ እስከ
ዛሬ ይሠራል፣እኔም ደግሞ እሠራለሁ ብሎ መለሰላቸው። እንግዲህ
ሰንበትን ስለሻረ ብቻ አይደለም፣ነገርግን ደግሞ ራሱን ከእግዚአብሔ
ር ጋር አስተካክሎ እግዚአብሔር አባቴ ነው ስላለ፣ስለዚህ አይሁድ
ሊገድሉት በጣም ይፈልጉ ነበር።
ስለዚህ ኢየሱስ መለሰ እንዲህም አላቸው፣እውነት እውነት
እላችኋለሁ፣አብ ሲያደርግ ያየውን ነው እንጂ ወልድ ከራሱ ሊያደርግ
ምንም አይችልም። ያ የሚያደርገውን ሁሉ ወልድ ደግሞ እንዲሁ
ያደርጋልና። አብ ወልድን ይወደዋልና የሚያደርገውን ሁሉ ያሳየዋል
እናንተም ታደንቁ ዘንድ ከዚህ የሚበልጥ ሥራ ያሳየዋል። አብ
ሙታንን እንደሚያስነሣ ሕይወትም እንደ ሚሰጣቸው፣እንዲሁም
ወልድ ደግሞ ለሚወዳቸው ሕይወትን ይሰጣቸዋል። ሰዎች ሁሉ አብን
እንደሚያከብሩት ወልድን ያከብሩት ዘንድ፣ፍርዱን ሁሉ ለወልድ
ሰጠው እንጂ አብ በአንድ ሰው እንኳ አይፈርድም። ወልድን
የማያከብር የላከውን አብን አያከብርም። እውነት እውነት እላችኋለሁ፣
ቃሌን የሚሰማ፣በላከኝም የሚያምን የዘለዓለም ሕይወት አለው፣ ከሞት
ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ፣ወደ ፍርድ አይመጣም። እውነት እውነት
እላችኋለሁ ሙታን የእግዚአብሔርን ልጅ ድምፅ የሚሰሙበት ሰዓት
ይመጣል፣እርሱም አሁን ነው፣የሚሰሙትም በሕይወት ይኖራሉ።
አብ በራሱ ሕይወት እንዳለው እንዲሁ ደግሞ ለወልድ በራሱ ሕይወ
ት እንዲኖረው ሰጥቶታልና የሰው ልጅም ስለሆነ ይፈርድ ዘንድ፣ሥል
ጣንን ሰጠው፣የእግዚአብሔር ልጅ የሰው ልጅ ነውና፤በመቃብር
ያሉት ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል። መልካምም
ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ፣ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይመጣሉ
ና በዚህ አታድንቁ። እኔ ራሴ አንዳች ላደርግ አልችልም፤እንደ ሰማሁ
እፈርዳለሁ ፍርዴም ቅን ነው፣የላከኝን ፈቃድ እንጂ ፈቃዴን
አልሻምና። እኔ ስለኔ ስለራሴ ብመሰክር ምስክሬ እውነት አይሆንም፣

ስለኔ የሚመሰክር ሌላ ነው፤ እርሱም ስለኔ የሚመሰክረው ምስክር እውነት እንደሆነ አውቃለሁ። እናንተ ወደ ዮሐንስ ልካችኋል እርሱም ለእውነት መስክሯል።እኔ ግን ከሰው ምስክር አልቀበልም፣ እናንተ እንድትድኑ ይህን እላለሁ እንጂ፤እርሱ የሚነድና የሚያበራ መብራት ነበር፣እናንተም ጥቂት ዘመን በብርሃኑ ደስ ሊላችሁ ወደዳችሁ። እኔ ግን ከዮሐንስ የሚበልጥ ምስክር አለኝ፣አብ ልፈጽመው የሰጠኝ ሥራ፣ይህ የማደርገው ሥራ አብ እንደላከኝ ስለ እኔ ይመሰክራልና። የላከኝ አብም እርሱ ስለኔ መስክሯል። ድምፁን ከቶ አልሰማችሁትም መልኩንም አላያችሁትም፣እርሱም የላከውን እናንተ አታምኑምና በእናንተ ዘንድ የሚኖር ቃሉ የላችሁም። እናንተ በመጻሕፍት የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ይመስላችኋልና እነርሱን ትመረምራላችሁ እነሱም ስለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው፣ነገር ግን ሕይወት እንዲሆንላችሁ ወደኔ ልትመጡ አትወዱም።——። እኔ በአባቴ ስም መጥቻለሁ አልተቀበላችሁኝምም ሌላው በራሱ ስም ሲመጣ እርሱን ትቀበላላችሁ። እናንተ እርስ በእርሳችሁ ክብር የምትቀባበሉ፣ከአንዱ ከእግዚአብሔር ያለውን ክብር የማትፈልጉ፣እንዴት ልታምኑ ትችላላችሁ? እኔ በአብ ዘንድ የምከሳችሁ አይምሰላችሁ፤የሚከሳችሁ አለ፣እርሱም ተስፋ የምታደርጉት ሙሴ ነው። ሙሴንስ ብታምኑት እኔንም ባመናችሁኝ ነበር። እርሱ ስለኔ ጽፏልና። መጻሕፍትን ካላመናችሁ ግን ቃሌን እንዴት ታምናላችሁ?

በዚህ ምዕራፍ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር አብ ልጅ መሆኑን፣የላከውም ለትስብእቱ ሥልጣን የሰጠውም እሱ እንደሆነ ሙሴም በዳግም 18:18 እግዚአብሔር እንደኔ ያለ ነቢይ ያስነሣላችኋል እሱን ስሙት ያለው እሱን ራሱን እንደሆነ እንጂ ሌላ ከሱ በፊት ወይም በኋላ የሚነሣ አወናባጅ ነቢይ ነኝ ባይ እንዳልሆነ ፍርጥ እርግጥ፣ግልጥ ግልጥልጥ አድርጎ ተናግሯል። ይህን በጥሞና አንቦ እውነተኛውን በመከተል ጽድቅን የሚፈልግ ያስተዋይ አንባቢ ፈንታ ነው።

10. (8:12) ደግሞም ኢየሱስ፣እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ፣የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም ብሎ ተናገራቸው።——————።

(9:35) ኢየሱስም ወደ ውጭ እንዳስወጡት ሰማ፣በአገኘውም ጊዜ አንተ በእግዚአብሔር ልጅ ታምናለህን? አለው። እርሱም መልሶ ጌታ ሆይ!በእርሱ አምን ዘንድ ማነው? አለ። ኢየሱስም አይተኸዋልም፣ከአንተ ጋርም የሚናገረው እሱ ነው አለው። እርሱም ጌታ ሆይ አምናለሁ አለ። ሰገደለትም። ስጊዱን ዝም ብሎ መቀበሉም አምላክነቱን ያረጋግ

ጣል። (10፥—27—33) በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ እኔም እውቃቸዋለሁ፤ይከተሉኝማል፤እኔም የዘለዓለም ሕይወት እሰጣቸዋለሁ፤ ለዘለዓለምም አይጠፉም። ከእጄም ማንም አይነጥቃቸውም፤የሰጠኝ አባቴ ከሁሉ ይበልጣል፤ከአባቴም እጅሊነጥቃቸው ማንም አይችልም። እኔና አብ አንድ ነን።
አይሁድ ሊወግሩት ደግመው ደንጊያ አነሡ። ኢየሱስም ከአባቴ ብዙ መልካም ሥራ አሳየኋችሁ፤ከእነሱ ስለማናቸው ሥራ ትወግሩኛላችሁ? ብሎ መለሰላቸው። አይሁድም ስለ መልካም ሥራ አንወግርህም፤ስለስ ድብህ፤አንተ ሰው ስትሆን ራስህን አምላክ ስለማድረግህ ነው እንጂ ብለው መለሱለት። በዚህ ጥቅስም ራሱ አምላክ መሆኑን ገልጧል፤አይ ሁድም ስድብ ነው ብለው ሊወግሩት ደንጊያ አንሥተዋል።
11. (36-39፤) የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ስላልሁ አብ የቀደሰውን ወደ እናንተም የላከውን (የላከኝን) ትሳደባለህ ትሉታላችሁ? እኔ የአባቴን ሥራ ባላደርግ አትመኑኝ፤ባደርገው ግን እኔን ስንኳ ባታምኑ፤አብ በእኔ እንደሆነ እኔም በአብ እንደሆንሁ ታውቁና ታስተውሉ ዘንድ ሥራውን እመኑ፤አሁን ደግሞ ደግመው ሊይዙት ፈለጉ።
12. (11: 25-27) ኢየሱስም ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፤የሚያምንብኝ ቢሞትም እንኳ ሕያው ይሆናል፤ሕያው የሆነ የሚያምንብኝም ሁሉ ለዘለዓለም አይሞትም፤ይህን ታምኛለሽ? አላት።
13. (ማር. 14:61-62) ሊቀ ካህናቱ ደግሞ ጠየቀውና የቡሩክ ልጅ ክርስቶስ አንተ ነህ? አለው። ኢየሱስም እኔ ነኝ፤የሰው ልጅም በኀይል ቀኝ ሲቀመጥ፤በሰማይም ደመና ሲመጣ ታያላችሁ አለ። ሊቀ ካህናቱ ም ልብሱን ቀደደና ከእንግዲህ ወዲህ ምስክሮችን ምን ያስፈልገናል? ስድቡን ሰማችሁ፤ምን ይመስላችኋል? አለ። እነርሱም ሁሉ ሞት ይገበዋል ብለው ፈረዱበት። አንዳንዶችም ይተፉበት፤ፊቱንም ሸፍነ ው ይጎስሙትና ትንቢት ተናገር ይሉት ጀመር። (ማቴ.25:65-67፤ ሉቃ.22: 66- 71)
14. ለቅዱስ ጳውሎስና ዮሐንስም ከሞተ በኋላ ተገልጦ እንዲህ ብሏል፤(ግብሐ.9: 3-6) ሲሄድም ደማስቆ በደረሰ ጊዜ ድንገት በእሱ ዙሪያ ከሰማይ ብርሃን እንደባረቀ ከምድርም ላይ ወድቆ ሳለ ስለ ምን ታሳድደኛለህ? የሚለውን ድምፅ ሰማ። ጌታ ሆይ! ማንነህ? አለው። እርሱም አንተ የምታሳድደኝ እኔ ኢየሱስ ነኝ፤ችንካር ብትረግጥ ላንተ ይብስሃል አለው። እየተንቀጠቀጠና እየተደነቀ፤ጌታ ሆይ! ምን አደርግ ዘንድ ትወዳለህ? አለው። ጌታም ተነሥተህ ወደ ከተማ ግባና ታደርገው ዘንድ የሚያስፈልግህን ይነግሩሃል አለው።

15. ለዮሐንስም (ራእ.1:8) ያለውና የነበረውም ሁሉን የሚገዛ ጌታ አምላክ አልፋ ና ዖሜጋ እኔ ነኝ ይላል።————። ባየሁትም ጊዜ እንደ ሞተ ሰው ሁኜ ከእግሩ በታች ወደቅሁ፤ቀኝ እጁንም ጫነብኝ እንዲህም አለኝ፣አትፍራ፤ፊተኛውና መጨረሻው ሕያውም ነኝ፣ሙቼም ነበርሁ፤እነሆም ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ ሕያው ነኝ፤የሞትና የሲኦልም መክፈቻ አለኝ። እንግዲህ ያየኸውን አሁንም ያለውን ከዚህም በኋላ ይሆን ዘንድ ያለውን ጻፍ።

16. (2 :18) በትያጥሮስም ወዳለው ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ፤ እንደ እሳት ነበልባል የሆኑ ዐይኖች ያሉት በእቶንም የነጠ ረ የጋለ ናስ የሚመስሉ እግሮች ያሉት የእግዚአብሔር ልጅ እንዲህ ይላል። ሁሉንም በደንብ ለመረዳት (ም.2 :3) በመላ ማንበብ ያሻል።

ስለ አምላክነቱ የመሰከሩ ሌሎች ነቢያት ሐዋርያት፤መላእክት፣ መናፍስት፤

17. የእነ ኢሳኢያስን ከዚህ በፊት ተናግረናል (9 :6 -7)

18. ዮሐንስ (ዮሐ.1:29) በበነጋው ዮሐንስ ኢየሱስን ወደ እሱ ሲመጣ ዐይቶ እንዲህ አለ—እነሆ! ያለምን ኀጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብ ሔር በግ፣ አንድ ሰው ከኔ በኋላ ይመጣል፣ከእኔም በፊት ነበረና ከእኔ ይልቅ የከበረ ነው ብዬ ሸለ እርሱ ያልሁት ይህ ነው። እኔም አላውቀውም ነበር ፣ዳሩ ግን ለእስራኤል ይገለጥ ዘንድ በውሃ እያጠመቅሁ እኔ መጣሁ። ዮሐንስም እንዲህ ብሎ መስከረ፣መንፈስ ከሰማይ እንደ ርግብ ሲወርድ አየሁ፤በእርሱ ላይም ተቀመጠ። እኔም አላውቀውም ነበር፤ዳሩ ግን በውሃ አጠምቅ ዘንድ የላከኝ እርሱ መንፈስ ሲወርድበትና ሲቀመጥበት የምታየው በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቅ እሱ ነው አለኝ። እኔም አይቻለሁ እሱም የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ መስክሬአለሁ።——37፤

19. (6:14) ከዚህ የተነሣ ሰዎች ኢየሱስ ያደረገውን ምልክት ባዩ ጊዜ ይህ በእውነት ወደ ዓለም የሚመጣው ነቢይ ነው አሉ።

20. (11:27) አዎን ጌታዬ ሆይ! አንተ ወደ ዓለም የሚመጣው ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆንህ እኔ አምናለሁ አለችው።

21. (12:42-43) ከዚህም ጋራ ካለቆች ደግሞ ብዙዎች በእሱ አመኑ፤ነገር ግን ከምኩራብ እንዳያስወጧቸው በፈሪሳውያን ምክንያ ት አልመሰከሩለትም፣ ከእግዚአብሔር ክብር ይልቅ የሰውን ክብር ወደዋልና።

22. (13:3)ኢየሱስም አብ ሁሉን በእጁ እንደሰጠው ከእግዚአብሔ ርም እንደ መጣ ወደ እግዚአብሔርም እንዲሄድ ዐውቆ ከራት ተነሣ።

23. (ማቴ.16:15-18) እናንተስ እኔ ማን እንደሆንሁ ትላላችሁ? አላቸው። ስምዖን ጴጥሮስም መለሰ፣አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ አለ። ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው፣የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ! በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ አለው። አምላክ ባይሆን ኖሮ የለም እኔ የአምላክ ልጅ፣አምላክ አይደለሁም ብሎ ያስተባብለው ነበር እንጂ ምስክርነቱን ተቀብሎ አያመሰግነውም ነበር። ከዚህም በላይ ጴጥሮስ እስከ ዕለተ ሞቱ ሲያስተምረው የኖረ ይህን ነው። (ግብሐ.2:36) እንግዲህ ይህን እናንተ የሰቀላችሁትን ኢየሱስን እግዚአብሔር ጌታም ክርስቶስም እንዳደረገው የእስራኤል ወገን ሁሉ በእርግጥ ይወቅ። (1ጴጥ.1:3፤30፤2ጴጥ.1:1)የእሱን ግርማ አይተንበብልሃት የተፈጠረ ውን ተረት ሳንከተል የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ኀይልና መምጣ ት አስታወቅናችሁ። ከገናናው ክብር በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጂ ይህ ነው የሚል ያ ድምፅ በመጣለት ጊዜ ከእግዚአብሔር አብ ክብርና ምስጋና ተቀብሏልና፤እኛም በቀደሰው ተራራ ከእሱ ጋራ ሳለን ይህን ድምፅ ከሰማይ ሲወርድ ሰማን።

24. ከቅዱስ ጴጥሮስ ጋራ የነበረ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ ወንጌላዊ ደግሞ እንደ ሚከተለው መስክራል፤(ዮሐ.1:1-5) በመጀመሪያ ቃል ነበረ፣ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፣ቃልም እግዚአብሔር ነበረ። ይህ በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ። ሁሉም በእርሱ ሆነ፣ከሆነውም አንዳች እንኳ ያለ እርሱ የሆነ የለም። (አልሆነም) በእርሱ ሕይወት ነበረች፤ሕይወትም የሰው ብርሃን ነበረች።——፤

25. (20 :30 -31) ኢየሱስም በዚህ መጽሐፍ ያልተጻፈ ብዙ ምልክት በደቀ መዛሙርቱ ፊት አደረገ፣ነገር ግን ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ታምኑ ዘንድ፣አምናችሁም በስሙ ሕይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ ተጽፏል።

26. (1ዮሐ.1:1-4) ስለ ሕይወት ቃል፣ከመጀመሪያ የነበረውንና የሰማነውን በዐይናችንም ያየነውን የተመለከትነውንም፣እጆቻችንም የዳሰሱትን እናወራለን፤ሕይወትም ተገለጠ፣አይተንማል፣እንመሰክራ ለን፣ከአብ ዘንድ የነበረውንም ለእኛም የተገለጠውን፣የዘለዓለምን ሕይወት እናወራችኋለን፤እናንተ ደግሞ ከእኛ ጋራ ኅብረት እንዲኖራ ችሁ፣ያየነውንና የሰማነውን ለእናንተ ደግሞ እናወራላችኋለን። ኅብረታችንም ከአብ ጋራ ከልጁም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋራ ነው።

27. (7) ነገር ግን እርሱ በብርሃን እንዳለ በብርሃን ብንመላለስ ለእያንዳንዳችን ኅብረት አለን፣የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኀጢአት ሁሉ ያነጻናል።

28. (3:23) ትእዛዚቱም ይህች ናት፣በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ እናምን ዘንድ።

29. (4:9-10) በዚህ የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ዘንድ ተገለጠ፣በእርሱ በኩል በሕይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኮታልና። ፍቅርም እንደዚህ ነው። እግዚአብሔር እርሱ ራሱ እንደ ወደደን ስለ ኀጢአታችንም ማስተሰሪያ፣ይሆን ዘንድ ልጁን እንደ ላከ እንጂ እኛ እግዚአብሔርን እንደ ወደድነው አይደለም።

30. (4:14) እኛም አይተናል አብም ልጁን የዓለም መድኀኒት እንዲሆን እንደ ላከው እንመሰክራለን።

31. (5: 5) ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ከሚያምን በቀር ዓለምን የሚያሸንፍ ማን ነው?

32. (13) የዘለዓለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ለምታምኑ ይህን ጽፌላችኋለሁ።

33. (20) የእግዚአብሔርም ልጅ እንደመጣ፣እውነተኛም የሆነውን እናውቅ ዘንድ ልቡናን እንደ ሰጠን እናውቃለን፣እውነተኛም በሆነው በእርሱ አለን፤እርሱም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘለዓለም ሕይወት ነው።

34. በተአምራት ክርስትናን ከማሳደድ የተመለሰው የአሕዛብ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስም ለቁጥር የሚያስቸግር፣ለጥቅስ የሚያዳግት ብዙ ማስረጃ በመንፈስ ቅዱስ እየተመራ ሰጥቷል።

35. (ሮሜ :8 :29፤32) ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኩር ይሆን ዘንድ አስቀድሞ ያወ ቃቸውን የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ወሰነ።

36. (32) ለገዛ ልጁ ያልራሩለት ነገር ግን ስለ ሁሉችን አሳልፎ የሰጠው (9:5) አባቶችም ለእነርሱ ናቸውና ከእነርሱም ክርስቶስ በሥጋ መጣ፣እርሱም ከሁሉ በላይ ሁኖ ለዘለዓለም የተባረከ አምላክ ነው።

37. (14:9) ስለዚህ ነገር ሙታንንም ሕያዋንንም ይገዛ ዘንድ ክርስቶስ ሙቷልና፣ሕያውም ሁኗልና።

38. (1ቆሮ.1: 9)ወደ ልጁ ወደ ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ ኅብረት የጠራችሁ እግዚአብሔር የታመነ ነው።

39. (ገላ.4:4) ነገር ግን የተወሰነ ዘመን በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ልጁን ላከልን። እርሱ ከሴት ተወለደ፣ለሕግም ታዛዥ ሆነ።

40. (1ጢሞ.2:5-7) አንድ እግዚአብሔር አለና፣በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለው መካከለኛ ደግሞ አንድ አለ፣እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፣ራሱንም ለሁሉ ቤዛ ሰጠ። ይህም ትክክለኛው

ጊዜ ሲደርስ የእግዚአብሔርን የማዳን ፍላጎት የሚያስረዳ ምስክርነት ነው። እኔም ለዚህ ነገር ዐዋጅ ነጋሪና ሐዋርያ በእምነትና በእውነትም የአሕዛብ አስተማሪ ለመሆን ተሾምሁ፤እውነትን እናገራለሁ፤አልዋሽ ም። ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ሁሉ ለምሳሌ ያህል ነው። መላ ሐዋርያት ያስተማሩትና እንደ ጳውሎስ ያሉት የጻፉት ሐዲስ ኪዳን የሚያስተም ረው የኢየሱስን ክርስቶስነትና የአምላክ ልጅነት፤አምላክነት ነው።

41. <u>መላእክት፤</u>

<u>ሊቀ መላእክት ታላቁ መልአክ ቅዱስ ገብርኤል፤</u>

(ሉቃ.1:29-33) እርስዋም ባየችው ጊዜ ከንግግሩ በጣም ደነገጠችና ይህ እንዴት ያለ ሰላምታ ነው? ብላ አሰበች። መልአኩም እንዲህ አላት፤ማርያም ሆይ! በእግዚአብሔር ፊት ጸጋ አግኝተሻልና አትፍሪ እነሆም ትፀንሻለሽ፤ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፤ስሙንም ኢየሱስ ትይ ቀለሽ፤እርሱ ታላቅ ነው፤የልዑል ልጅም ይባላል፤ጌታ አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል፤በያዕቆብ ቤት ለዘለዓለም ይነግሣ ል፤ለመንግሥቱም መጨረሻ የለውም።

42. (2:8-14) በዚያም ሀገር መንጋቸውን ሲጠብቁ ከሜዳ የሚያድሩ እረኞች ነበሩ። እነሆም፤የጌታ መልአክ ወደ እነሱ ቀረበ፤የጌታ ክብርም በዙሪያቸው አበራ። ታላቅ ፍርሃትም ፈሩ። መልአኩም እንዲህ አላቸው-እነሆ! ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ፤ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኀኒት፤እሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋልና። ይህም ምልክት ይሆንላችኋል፤ ሕፃን ተጠቅልሎ፤በግርግም ተኝቶ ታገኛላችሁ። ድንገትም ብዙ የሰማይ መላእክት ከመልአኩ ጋራ ነበሩ። እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ፤ክብር (ስብሐት) ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ አሉ።

43. (ማቴ.28:2-8) እነሆም የጌታ መልአክ ከሰማይ ስለወረደ ታላቅ የምድር መናወጥ ሆነ፤ቀርቦም ድንጋዩን አንከባሎ በላዩም ተቀመጠ። መልኩም እንደ መብረቅ፤ልብሱም እንደ በረዶ ነጭ ነበረ። ጠባቆቹም እርሱን ከመፍራት የተነሣ ተናወጡ እንደ ሞቱም ሆኑ። መልአኩም መልሶ ሴቶቹን አላቸው፤ እናንተስ አትፍሩ የተሰቀለውን ኢየሱስን እንድትሹ አውቃለሁና እንደ ተናገረ ተነሥቷልና በዚህ የለም የተኛበትን ስፍራ ኑ እዩ። ፈጥናችሁም ሂዱና ከሙታን ተነሣ እነሆም ወደ ገሊላ ይቀድማችኋል፤በዚያም ታዩታላችሁ ብላችሁ ለደቀ መዛሙርቱ ንገሯቸው አላቸው። (ማር.16:2-8፤(ሉቃ.24:4-8የሐ. 20:11-14)

<u>ርኩሳን መናፍስት፣</u>

44. (ማር. 1:23-24) በዚያን ጊዜም በምኩሩባቸው ርኩስ መንፈስ የያዘው ሰው ነበረ፣እርሱም የናዝሬቱ ኢየሱስ ሆይ! ካንተ ጋር ምን አለን?ልታጠፋህ መጣህን? ማን እንደሆንህ ኣውቅሃለሁ፣የእግዚአብ ሔር ቅዱሱ ብሎ ጮኸ: (ሉቃ.4: 33፤)

45.(ማር.5:2-14)——፣ኢየሱስንም ከሩቅ ባየ ጊዜ ሩጦ ሰገደለት፣በታላቅ ድምፅም እየጮኸ፣የልዑል እግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ሆይ! ከአንተ ጋር ምን አለኝ? እንዳታሠቃየኝ፣በእግዚአብሔር አምልሃለሁ አለ።

46. (ማር.3: 16) ርኩሳን መናፍስትም ባዩት ጊዜ በፊቱ ተደፍተው አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ እያሉ ጮኹ። እንዳይገልጡትም በጣም አዘዛቸው።(ማር.1:24፤5:7፤15:39፤ማቴ.8:29፤ሉቃ.4:41፤ዮሐ1: 50፤)

47. (ግብሐ.19: 11-18) እግዚአብሔርም በጳውሎስ እጅ የሚያስገርም ታምራት ያደርግ ነበር፣ስለዚህም አካሉ ከነካው ጨርቅእየወሰዱ ከድውያን ላይ ይጥሉ ነበር፣ደዌያቸውም ይለቃቸው ነበር፣ክፉዎች መናፍስትም ይወጡ ነበር፤አጋንንትንም እያወጡ ይዞሩ ከነበሩት አይሁድ አንዳንዶቹ ጳውሎስ በሚሰብከው በኢየሱስ ስም እናምናችኋለን እያሉ ክፉዎች መናፍት ባሉባቸው ላይ የጌታን የኢየሱስን ስም ይጠሩባቸው ዘንድ ሞከሩ። የካህናቱም አለቃ አስቄዋ ለሚሉት አንድ አይሁዳዊ ይህን የሚያደርጉ ሰባት ልጆች ነበሩት። ክፉው መንፈስ ግን መልሶ፣ኢየሱስንስ ኣውቀዋለሁ፣ጳውሎስንም ኣውቀዋለሁ እናንተሳ እነማን ናችሁ? አላቸው። ክፉው መንፈስም ያለበት ሰው ዘለለባቸው፣ቆስለውም ከዚያ ቤት ዕራቁታቸውን እስኪሸሹ ድረስ በረታባቸው፣አሸነፋቸውም። ይህም በኤፌሶን በሚኖሩት ሁሉ በአይሁድና በግሪክ ሰዎች ዘንድ የታወቀ ሆነ፣በሁሉ ቸውም ላይ ፍርሃት ወደቀባቸው ፣የጌታም ኢየሱስ ስም ተከበረ።——።

ስለ ክርስቶስ አምላክነትና ሰውነት (ወልደ አብ በመለኮቱ፣ወልደ ማርያም በትስብእቱ) በዚህ ዕጥፍ መረጃ ማቅረብ ይቻላል። ባጭሩ ያስቀረው የማሳተሚያው ወረቀት ነው። የራሱ የእግዚአብሔር አብ፣የኢየሱስ ክርስቶስ፣የነቢያት፣የሐዋርያት የመላእክት ፣ምስክርነት እያለ ይህን ሁሉ አሽቀንጥረው ጥለው እነ ዲዳት ክርስቶስ አምላክ አይደለም ይላሉ። ሌላው ይቅርና የባልንጀሮቹን የርኩሳን መናፍስትን ምስክርነት እንኳ ትቶ ኢየሱስ አምላክ ወልደ አምላክ አይደለም የሚል ከ600 ዘመን በኋላ የተነሣ ሐሳዊ መሲሕ ሁሉ ከመናፍስት ርኩሳን ያንሳል።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ጥቅሶች እነ ዲዳት አብ አባቴ ነው የሚለው እንደ ሌላው የጸጋ ልጅ ነው የሚሉትን የሐሰት ስርብትና ብትንትኑን ያወጣዋል። በመለኮት የባሕርይ አባትና ልጅ መሆናቸው ንም አብራርቶ ያስረዳል፤ለዚህም አባት ልጁ !ልጄ! ልጅም ወልድም አባቴ! አባቴ ! እያሉ ተማምነዋል፣ተመሰጋግነዋል።

# ምዕራፍ፡ 5፤

## ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰውም ነው።

ፍጹም አምላክነቱን በአለፈው ምዕራፍ አይተናል፤በዚህ ደግሞ ፍጹም ሰውነቱን እናስረዳለን። ለአምላክነቱና ለሰውነቱ ማስረጃ የሚሰጠው የቤተ ክርስቲያን ዐዋጅም ወልደ አብ በመለኮቱ፣ ወልደ ማርያም በትስብእቱ ሁለት ልደት በተዋሕዶ ከበረ ይላል፤ይኸውም በመለኮቱ የአብ፣በሥጋው የማርያም ልጅ ሁለት ልደት በተዋሕዶ ከበረ ማለት ነው።

በመለኮቱ እምቅድመ ዓለም ከአብ በመወለዱ አምላክ፣ ወልደ አምላክ እንደሆነ በሥጋው (በትስብእቱ) ደግሞ ከቅድስት ድንግል ማርያም ስለተወለደ ፍጹም ሰው ነው። ከኀጢአት በቀር ሥጋዊ ደማዊ ሰው የሚያደርገውን ሁሉ ፈጽሟል፤ያለ ወንድ ዘር ከድንግል ማርያም በግብረ መንፈስ ቅዱስ፣በኀይለ እግዚአብሔር ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነሥቶ፤እንደ ሌላው ጤነኛ ሰው ዘጠኝ ወር ካምስት ቀን በማሕፀን ቆይቶ ተወለደ። እንደ ሕፃናት ጥቂት በጥቂት አደገ፤ተራበ፤ ተጠማ ደከመ፤በላ፤ጠጣ፤ተኛ፤ነቃ፤በእግሩ ተጓዘ፤በእጁ ጨበጠ፤ዳሰሰ ወደ አባቱ ጸለየ፤ለአባቱ ሰገደ፤ከዲያብሎስ ተፈተነ፤ታሰረ፤ተገረፈ፤ተ ገፈፈ፤ተሰቀለ፤ሞተ። በለበሰው ሥጋ ይህ ሁሉ ደረሰበት። በመለኮቱ ከሞተ በኋላ የሞትን አሽክላ ሰብሮ፤መግነዝ ፍቱልኝ መቃብር ክፈቱ ልኝ ሳይል ተነሣ። ሥጋ መልበሱና ለሰው ብሎ ሰው መሆኑን(ማስረዳ ት ብዙ ጊዜ ራሱን የሰው ልጅ እያለ ደጋግሞ ይጠራ ነበር፤ በዚህ ስም ነቢዩ ሕዝቅኤል ይጠራበት ነበር፤ይህም በትንቢት መነገሩ ነው። (12:1——:)የእግዚአብሔር ቃልም ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ፤"የሰው ልጅ ሆይ! በዐመፀኛ ቤት መካከል ተቀምጠሃል፤ያዩ ዘንድ ዐይን አላቸው፤እነርሱም አያዩም፤ይሰሙ ዘንድ ጆሮ አላቸው እነሱም አይሰ ሙም፤እነርሱ ዐመፀኛ ቤት ናቸውና። አንተም የሰው ልጅ ሆይ፡——። ዳንኤልም ዐይቶታል (7:13) በሌሊት ራእይ አየሁ፤እነሆም የሰው ልጅ የሚመስል ከሰማይ ደመናት ጋር መጣ፤ወደ ሽመገለውም ሰው ደረሰ። ወደ ፊቱም አቀረቡት። ወገኖችና አሕዛብ በልዩ ልዩ ቋንቋም የሚናገ ሩ ሁሉ ይገዙለት ዘንድ ግዛትና ክብር መንግሥትም ተሰጠው ግዛቱ ም የማያልፍ የዘለዓለም ግዛት ነው፤መንግሥቱም የማይጠፋ ነው።

በእናቱ ፍጹም የሰው ልጅ መሆኑን ለማስረዳት ጌታ ብዙ ጊዜ መላልሶ ተናግሯል፤እኛም ከብዙ ጥቂቱን ከዚህ እናስከትላለን።

**የሰው ልጅ፤**

(ማቴ.8:20፤9:6፤11:19፤16:13፤20:28፤24:27፤ማር.8 38፤ሉቃ.18: 8፤ ዮሐ.1: 51፤ 5: 27፤ 6: 53፤ 12: 23፤ 13: 31፤ ግብ. 7: 56፤ ራዕ. 1: 13)።

ይህ ሁሉ እያለ ሥጋ ለብሶ ለሰው ሲል የተቀበለውን መከራ፣ የሆነውን ሁኔታ፣የተሠቃየውን ሥቃይና ሕማም እንዲያው በድካም የደረሰበት አስመስለው እና ዲዳት አቅርበውታል። ይህን ያደረገውም ዲያብሎስ አዳምን በሥጋ ከይሲ ተሰውሮ እንዳሳተው እሱም በሥጋ ሰብእ ተሰውሮ ሰይጣንን ድል ለመድረግ መሆኑን ቢያውቁ ኑሮ ባላወቁት፣ ባልገባቸው ነገር አይዘላብዱም ነበር። ውርደትን ሁሉ ሥጋ ለብሶ በሥጋው ፈጽሞ ዲያብሎስን ድል ነሥቶ፣የበድል መሥዋዕት ራሱን አድርጎ ለአባቱ አቅርቦ ፣ዓለምን አድና ከአባቱ ጋር አስታርቋል ። ይህንም ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በግልጥ አስተምሮታል፣በግብርም አሳይቷል፣ነቢያት በትንቢት ተናግረውታል፣በመጨረሻም ሐዋርያት ሰብከውታል፣ቀጥሎም ቤተ ክርስቲያን ታስተምረዋለች፣ትሰብከዋለች።

# ምዕራፍ 6

## ክርስቶስ ዐምደ ብርሃን ነው፤

ክርስቶስ የፒራሚድ ጉልላት ወይም ዐምደ ብርሃን ስለሆነ ብሉይ ኪዳን ይመጣል እያለች፣ሐዋርያት ደግሞ መጥቶ ሄደ፣ሄዷል እያሉ ያመለክታሉ፣ይናገራሉ። ወደ ጉልላቱ የማያሳይ ማዕዘን ወይም ጠርዝ የለም። ብሉያት፣ ክርስቶስ ይመጣል ብለው ትንቢት ይናገሩ፣ ነቢያት ደግሞ ልጅህን ቀኝ እጅህን ላክልን እያሉ ይጸልዩ ነበረ።

ለሁሉም ከሁሉም ሁሉን ይወቅ ገጽ129 የተጻፈውን ያነቧል። ያን መጽሐፍ ለማያገኝ ከዚህ ቀጥለን ባጭሩ እንጽፋለን። በሌላም አነጋገር ነቢያት ክርስቶስ ይመጣል፣ዓለምን ያድናል እያሉ ከዚህ በፊት በንጽጽ ር እንዳየነው ትንቢት በእየጊዜው ተናግረዋል፤እራሱም እኔ ነኝ እያለ ድውይ እየፈሰ፣ሙት እያስነሣ፣ታምራት እያሳየ በርግጥ የአምላክ ልጅ መሆኑን በግቢር አስረድቷል። ከእሱ በኋላ ደግሞ ደቀ መዛሙር ቱ ሐዋርያት፣አርድእት፣ሊቃውንት፣አበውም ትንቢት የተነገረለት፣ዘ መን የተቈጠረለት መሲሕ፣ነቢይ ኢየሱስ ነው፣እሱም መጥቶ ስለ እሱ የተነገረውን ትንቢት ሁሉ ፈጽሞ፣ዓለምን አድኖ ወደ ሰማይ ተመልሶ ዐርጎ በአባቱ ቀኝ በክብር ተቀምጧል እያሉ ዓለምን አስተማሩ፣አስተ ምረዋል። ስለዚህም በሰማዕትነት በዐላውያን ነገሥታት፣በመናፍቃን ጳ ጳሳት አደባባይ ተሰቃይተዋል፣አልቀዋል፤ያሉትም የእነሱን ዱካ እየተ ከተሉ ናቸው፣መከራም እየደረሰባቸው ነው።

ከዚህ ቀጥለን በሙሴና በሌሎች ነቢያት የተነገሩት ትንቢቶች በክርስ ቶስ መምጣት እንዴት እንደተገረቡ (ተመለሱ) እናያለን። በሙሴ የተነገረው ትንቢት በክርስቶስ መምጣት መፈጸሙን ለማጠየቅ ቅዱስ ጴጥሮስ እንዲህ ብሎ መልሶታል (ገርብቶታል) እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ በቅዱሳን ነቢያት አፍ የተናገረው ነገር ሁሉ እስከሚከናወንበት ድረስ ሰሚ ይቀበለው ዘንድ ይገባልና ሙሴም ለአባቶች አለቆች ጌታ አምላክ እኔን እንዳስነሣኝ ነቢይ ከወንድሞቻችሁ ያስነሣላችኋል።የሚነግ ራችሁንሁሉ ስሙት ያን ነቢይ የማትሰማ ነፍስ ሁሉ ከሕዝብ ተለይታ ትጠፋለች። ይህን ቃል ጥብቅ መሆኑን ለማስረዳት ሁለት ጊዜ ተናግሮ ታል። ከፍ ብሎ ቁጥር 15 ላይ"ከአንተ መካከል ከወንድሞችህ እግዚ አብሔር አምላክ እንደኔ ያለ ነቢይ ያስነሣልሃል። እሱን ስማው። (በዚህ ትንቢት መሠረት፤

1ኛ ያስነሣልሃል እንጂ ያስነሣብሃል ስላለ፣

2ኛ የእስማኤልና የኤሳው ዘሮች ለያዕቆብ ልጆች ለነገደ እስራኤል ጠላት፣ ደመኛ እንጂ ወንድም አይደሉምና እንዲያውም መሐመድስ አይሁድ፣በቁርአን እንደ ተጻፈው በገቡበት ገብቶ ሲያሳድዳቸው ነው የኖረና፣ይህ ትንቢት ለመሐመድ ሊጠቀስ በምንም አይቻልም። (2ኛ ሱራህ: 120፤4ኛ ሱራህ:46፤153፤157፤ 5ኛ. ሱራህ:41፣64) ዕይ።

ምክንያቱም መሐመድና ተከታዮቹ የአይሁድ ጠላት እንጂ ወዳጅ ወይም ወገን አይደሉምና።
ሦስተኛም ከሳሙኤል ጀምሮ የተነሡት ነቢያት ሁሉ ስለዚህ ወራት ተነበዩ። እናንተ የነቢያት ልጆችና እግዚአብሔር ለአብርሃም በዘርህ የምድር ወገኖች ሁሉ ይባረካሉ ብሎ ከአባቶቻችንም ጋራ ያደረገው የኪዳን ልጆች ናችሁ። ለእናንተ አስቀድሞ እግዚአብሔር ብላቴናውን (ልጁን) አስነሥቶ፣እያንዳንዳችሁን ከክፋታችሁ እየመለሰ ይባርካችሁ ዘንድ ሰደደው። (ግብሐ.3:21-26) ዲያቢሎስ አዳምን በእባብ አድሮ ስላሳተው፣ጌታ እግዚአብሔር ዲያብሎስን በሥጋ ገብቶ የሚያሸንፈው፣ከዘሩ የሚወለደው ክርስቶስ እንደሆን ተናግሯል። ከይስ ይቀጠቅጣል ተብሏል። እግዚአብሔር አምላክም እባቡን አለው፣ይህን ስላደረግህ ከእንስሳት፣ከምድር አራዊትም ሁሉ ተለይተህ አንተ የተረገምህ ትሆናለህ፣በሆድህ ትሄዳለህ፣አፈርንም በሕይወትህ ዘመን ሁሉ በላለህ፤በአንተና በሴቲቱ መካከል፣በዘርህና በዘርዋ መካከል ጠላትነትን አኖራለሁ። እርሱ ራስህን ይቀጠቅጥሃል፣አንተም ሰኮናውን ትቀጠቅጠዋለህ (ዘፍ.3:14-15)

ይህም ከአዳም ተወልዶ፣ሥጋ ለብሶ፣በመስቀል ተሰቅሎ ዲያብሎስን ድል መንሣቱን ይናገራል። ይህንም ዮሐንስ ወንጌላዊው፣መልዕክታል (ቀለብሰታል፣ገርብቶታል) ልጆቼ ሆይ! ማንም አያስታችሁ፣እሱ ጻድቅ እንደሆነ ጽድቅን የሚያደርግ ሁሉ ጻድቅ ነው። ኀጢአትን የሚያደርግ ሁሉ ደግሞ ከዲያብሎስ ነው፤በመጀመሪያ ዲያብሎስ ኀጢአትን አድርግዋልና፡ስለዚህ የዲያብሎስንሥራ ለማፍረስ ልጁ ተገለጠ። (1ዮሐ.3:6-8)

ከድንግል ይወለዳል፤እናንተ የዳዊት ቤት ሆይ!ስሙ፣በውኑ ሰውን ማድከማችሁ ቀላል ነውን? አምላኪየን ደግሞ የምታደክሙ? ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል፣እነሆ! ድንግል ትፀንሳለች፣ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም ዐማኑኤል ትለዋለች። (ኢሳ.7: 14) በድንግልና ተፀንሶ በድንግልና በመወለዱ ተፈጽሟል፤የኢየሱስ ክርስቶስ ልደትም እንዲህ ነበረ። እናቱ ማርያም ለዮሴፍ ታጭታ ሳለ፣ሳይገናኙ በመንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ተገኘች። (ማቴ.1:18-24) እንዲህ ብሎ ማቴዎስ መፈጸሙን ይናገራል፣ነግሮናል።

ዓለሙን ሁሉ የሚያስተው ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እሱም የቀድሞው እባብ ተጣለ። ወደ ምድር ተጣለ፣መላእክትም ከእርሱ ጋራ ተጣሉ። ታላቅም ድምፅ ከሰማይ ሰማሁ፤እንዲህ ሲል "አሁን የአምላካችን ማዳንና ኀይል መንግሥትም የክርስቶስ ሥልጣን ሆነ፣ቀንና ሌሊትም የሚከሳቸው የወንድሞቻችን ከሳሽ ተጥሏልና፣

እነሱም ከበጉ ደም የተነሣ፣ከምስክራቸውም ቃል የተነሣ ድል ነሡት (ራእ.12:9-12) ይህም ዘፍ.3:15: የተጻፈውን በትክል ያጥፋል፣ስለዚህ መሆኑንም ያስረዳል። ጳውሎስም "የሰላምም አምላክ ሰይጣንን ከእግራችሁ በታች ፈጥኖ ይቀጠቅጠዋል "ብሎ ደግሞታል። (ሮሜ.16:20) አብርሃምም እግዚአብሔርን "እስማኤል በፊትህ ቢኖር በወደድሁ ነበር" አለው። እግዚአብሔርም "በእውነት ምሽትህ ሣራ ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች፤ስሙንም ይሥሐቅ ብለህ ትጠራዋለህ። በእርሱ፣በዘሩ የዘለዓለም ቃሌ ኪዳን አቆማለሁ። (ዘፍ.14:19) ይህም መፈጸሙን ቅዱስ ጳውሎስ በዕብራውያን መልእክቱ ምዕራፍ 7 ቁልጭ አድርጎ በሙሉ ገልጦታል። "እንደ መልከ ጼዴቅ ሥርዓት አንተ ለዘለዓለም ካህን ነህ" ብሎ፣ እግዚአብሔር ማለ፣አይጸጸትምም፤ (መዝ.109:4) ይህም ከላይ በተጠቀሰው ምዕራፍ ተመልሷል (ተገርብቷል)

እግዚአብሔር ጌታዬን "ጠላቶችህን በእግርህ ዱካ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው።መዝ.110:1)ይህም(ማቴ.22:44፤ማር.12:36፤ሉቃ.20:42፤ግብ.2:34፤1ቆሮ.(5:25) ላይ ተመልሷል።

<u>ነቢይ</u> ነው፤በዘዳግም ከ18:15-20: የተነገረው ነቢይ እሱ መሆኑን ራሱና ደቀ መዛሙርቱ አረጋግጠዋል፡(ማቴ.13:57፤ማር.6:4፤ሉቃ.4:24፤ዮሐ.1:21፤7:40)ግብ.3:22:23)ኢየሱስ ግን "ነቢይ የሚናቀው በገዛ ሀገሩና በገዛ ቤተሰቡ ነው እንጂ በሌላ ቦታስ ይከበራል" አላቸው። (21:10-11) ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም በገባ ጊዜ፣የከተማው ሰዎች በሙሉ ይህ ማነው? በማለት ታወኩ። ሕዝቡም ይህ "ከገሊላ ክፍለ ሀገር ከምትገኝ ከናዝሬት ከተማ የመጣ ነቢይ ኢየሱስ ነው" አሉ።

<u>ንጉሠ ነገሥት ነው፤</u> (መዝ.2:6)እኔ ግን ንጉሤን በተቀደሰው ተራራዬ በጽዮን ላይ ሾምሁ። (መዝ.23:6-10) እናንተ መኳንንቱ በሮችን ከፈቱ፣የዘለዓለም ደጆችም ይከፈቱ የክብር ንጉሥ ይግባ፤የክብር ንጉሥ ማነው? እግዚአብሔር ነው፣ብርቱና ኃያል እግዚአብሔር ነው በሰልፍ ኃያል፡(መዝ.43:4)አምላኪዬና ንጉሤ አንተ ነህ፣ለያዕቆብ መድኃኒትን አዝዝ። (71:1)አቤቱ ፍርድህን ለንጉሥ ስጥ፣ጽድቅህንም ለንጉሡ ልጅ(149:2)እስራኤል በፈጠረው ደስ ይበለው፣የጽዮንም ልጆች በንጉሣቸው ሐሤትን ያድርጉ። (ኢሳ.32:1፤9:6-7)እነሆ! ንጉሥ በጽድቅ ይነግሣል፣መሳፍንትም በፍርድ ይገዛሉ። (ዳን.7:13-14)በሌሊት ራእይ አየሁ፣እነሆም የሰው ልጅ የሚመስል ከሰማይ ከደመናት ጋራ መጣ፣በዘመናት ወደ ሸመገለውም ደረሰ፣ወደ ፊትም አቀረቡት ወገኖችና አሕዛብ በልዩ ልዩ ቋንቋ የሚናገሩ ሁሉ ይገዙለት ዘንድ ግዛትና ክብር መንግሥትም ተሰጠው፣ግዛቱም የማይጠፋ የዘለዓለም ግዛት ነው።

<u>ንጉሠ ሰላም ነው፣</u>

ለዚህም ኢሳያስ ምዕራፍ ዐሥራ ሐንድን ያነቧል፤ ዘካርያስም እንዲህ ብሏል፤አንቺ የጽዮን ልጅ ሆይ! እጅግ ደስ ይበልሽ፣አንቺ የኢየሩሳሌም ልጅ ሆይ! እልል በይ፣እነሆ ንጉሥሽ ጻድቅና አዛኝ ነው። ትሑትም ሁኖ በአህያም፣በአህየይቱ ግልገል በውርንጭላይቱ ላይ ተቀምጦ ወዳ ንቺ ይመጣል (ዘካ.9.9) ይህ ሁሉ በሚከተሉት ጥቅሶች ተገርብቷል (ማቴ.21:2-12፤25:34፤ ማር.11:1-11፤ ሉቃ.19:28፤ ዮሐ.12:1219፤ 1ጢሞ.1:17)

ስለዚህ ዘለዓለማዊ ንጉሥ ለሆነው፣ለማይሞተው፣ለማይታየው ለአንዱ አምላክ ክብርና ምስጋና ለዘለዓለም ይሁን። (ራእ.19:16)በልብሱና በጭኑም የነገሥታት ንጉሥ የጌቶች ጌታ የሚል የተጻፈ ስም አለው።

<u>የመከራ ሰው ነው፣</u>

ሲወለድ ጀምሮ ከሙታን ተለይቶ እስኪነሣ ድረስ የዚህን ዓለም ሠላሳ ሦስት ዓመቱን ያሳለፈው በመከራ ነው፤እንደ ተወለደ ከግርግም ተወልዶ ከእንስሳት ጋር ከጋጥ ሰነበተ። የኢየሩሳሌምን ንጉሥ ሄሮድ ስን ፈርቶ ለሦስት ዓመት በግብፅ በረሃ ተሰደደ፤ኋላም ለራሱ ማሳረፊያ ሳይኖረው ለሦስት ዓመት ሀገር ላገር እየተዘዋወረ አስተማ ረ፣ይህም ኑሮ ሆነና አይሁድ ቀንተው አሰሩት፣አዳፉት፣ገረፉት፣ተፉ በት፤በመጨረሻውም ከሌቦች ጋራ ሰቅለው ገደሉት። ይህ ሁሉ ከዚህ በፊት እንዳየ ነው በትንቢት ተነግሯል። የሰማነውን ነገር ማን አምኖ ናል? የእግዚአብሔርስ ክንድ ለማን ተገለጠል? በሥሩ እንደቡቃያ ከደረቀም መሬት እንደ ሥር አድጓል፣መልክና ውበት የለውም፣የተና ቀ፣ከሰውም የተጠላ——። (ኢሳ.53፤መዝ.22:1-31፤ ማቴ.27:27-35፤ ዮሐ.1:29፤ 1ጴጥ.1:19፤2: 21-25)

<u>ስግዕት ሊቀ ስግዕት፣ቀዳሚ ስግዕት ነው፤</u>

ስለ አባቱ በመመስከሩ፣አባቱን አባቴ ነው በማለቱ በዐውደ ጲላጦስ ተገርፎ በአይሁድ እጅ ተሰቅሏል።

<u>ኀጢአተ ዓለምን የሚያስተሰርይ መሥዋዕት ነው፣</u>

(ዮሐ.1:29፤1ጢሞ.2:5-6፤ራእ.1:5-6)በማግሥቱም ኢየሱስ ወደ ዮሐ ንስ ሲመጣ አይቶ እንዲህ አለ፣እነሆ! የዓለምን ኀጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ ይህ ነው፣ከኔ በኋላ የሚመጣው ከኔ ይበልጣል፣ም ክንያቱም ከኔ በፊት ነበረ ያልኋችሁ ይህ ነው፣እኔም እራሴ አላውቀ ውም ነበር፣ነገር ግን እሱ ለእስራኤል ሕዝብ እንዲገለጥ እኔ በውኃ እያጠመቅሁ መጣሁ። (1ጢሞ.2:5-6) እግዚአብሔር አንድ ነው፣

በመካከል ሆኖ እግዚአብሔርንና ሰውን የሚያስታርቀውም አንድ ነው። እሱም ሰው የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ሰዎቹን ሁሉ ከኀጢአት ለመዋጀት ራሱን ቤዛ አድርጎ የሰጠ እርሱ ነው፤——።
(ራእ.1: 5-6)ከዮሐንስ ለሰባቱ በእስያ ላሉት አብያተ ክርስታያን የተላከ ሰላምታ፤ከአለው፤ከነበረው ከሚመጣውና በመንበሩ ፊት ካሉት ከሰባቱ መናፍስት ታማኝ ምስክር ከሆነው፤ከሞት በመነሣት በኵር ከሆነ ነው የምድር ነገሥታትም ገዥ ከሆነው፤ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን። አስተውሎ ያነበበ ከዚህ በላይ በሦስቱ ምዕራፋት የተነገሩት ትንቢታትና ተፍጻሚታት የተነገሩት ለኢየሱስ ክርስቶስ እንጂ ለሌላ እንዳልሆኑ ይረዳል። ስለዚህ ለአያ ዲዳትና ለመሰሎቻቸው ይህ መንገድ ግለፊያ አይደለም፤አያሳልፋም፤አይሰድም። በመሆኑም መጽሐፍ ቅዱስ ስለመሐመድ ብለው ሳይገባቸው የወሸከቱትን በሚቀጥለው ምዕራፍ እንመልሳለን።

# ምዕራፍ 7፣

## ትንቢታትን የፈጸመ ክርስቶስ ነው።

### ስለ ክርስቶስ ዳግም ምጣት የተነገሩ ትንቢቶች።

የክርስቶስ መምጣት እነ አሕመድ ዲዳት እንደ ሚሉት በሙሴ ብቻ ሳይሆን፣ከአዳም መውደቅ ጀምሮ እስከ ዮሐንስ መጥምቅ ሲነገር ኑሯል። እናም እውነትን ለማወቅ ለሚፈልግ ከዚህ በታች በቅደም ተከተል ቀርበዋል።

1. ለሴቲቱ ለሔዋን የተነገረ ትንቢት፤

(ዘፍ.3:15)በአንተና በሴቲት መካከል በዘርህና በዘርዋ መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ፣እሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፣አንተም ሰኮናውን ትቀጠቅጣለህ።

ፍጻሜ፤ (ገላ.4:4)ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግ በታች የተወለደውን ልጁን ላከ። (ሉቃ.2:7) በዚያ ሳሉ የመውለጃዋ ወራት ደረሰ የበኩር ልጇንም ወለደች——። (ራእ.12: 5)አሕዛብንም ሁሉ በብረት በትር ይገዛቸው ዘንድ ያለውን ልጅ ወንድ ልጅ ወለደች። ልጅዋም ወደ እግዚአብሔርና ወደ ዙፋኑ ተነጠቀ።

2. ለአብርሃም ዘር የተሰጠ የተስፋ ትንቢት፤ (ዘፍ.18:17-18) እኔ የማደርገውን ከአብርሃም እሰውራለሁን? አብርሃም በእውነት ታላቅና ብርቱ ሕዝብ ይሆናልና በምድር አሕዛብ ሁሉ በእሱ ይባረካሉና። ከዚህ በፊትም 12:2-3 ላይ፣ታላቅ ሕዝብም አደርግሃለሁ፣እባርክሃለሁ ስምህንም አከብረዋለሁ፤ለበረከትም ሁን፤የሚባርኩህን እባርካለሁ፤ የሚረግሙህን እረግማለሁ፤የምድር ነገዶች ሁሉ በአንተ ይባርካሉ ብሏል።

ፍጻሜው፣(ግብሐ.3:25)እናንተ የነቢያት ልጆችና እግዚአብሔር ለአብርሃም በዘርህ የምድር ወገኖች ሁሉ ይባርካሉ ብሎ ከአባቶቻችሁ ጋራ ያደረገው የኪዳን ልጆች ናችሁ።

3. ለይሥሐቅ ዘር የተሰጠ ተስፋ፤ (ዘፍ.17: 19)እግዚአብሔርም አለ በእውነት ምሽትህ ሣራ ወንድ ልጅን ትወልድልሃለች፣ስሙንም ይሥሐቅ ብለህ ትጠራዋለህ፣ከርሱ በኋላ ለዘሩ ቃል ኪዳን እንዲሆን፣ቃል ኪዳኔን ከእሱ ጋራ አቆማለሁ።

ፍጻሜ፤ አብርሃም ይሥሐቅን ወለደ፣ይሥሐቅም ያዕቆብን ወለደ፣ ያዕቆብም ይሁዳንና ወንድሞቹን ወለደ (ማቴ.1: 2:16)

4. ለያዕቆብ ዘር የተሰጠ የተስፋ ትንቢት፤

?4:1‾ ነየዋለሁ አሁን ግን አይደለም፣እመለከተዋለሁ በቅርብ
ከያቆብ ኮከብ ይወጣል፤ከእስራኤል በትር ይነሣል፣

የምዓብን ማዕዘኖች ይመታል። የሤትንም ልጆች ያጠፋል፤ኤዶምያስም ርስቱ ይሆናል፣እስራኤልም በኀይል ያደርጋል፤ከያቆብ የሚመጣ ገዥ ይሆናል።——።

ፍጻሜ፣ (ሉቃ.3:34) የያዕቆብ የይሥሐቅ፣የአብርሃም የታራ፣የናሆር ልጅ (ማቴ.1:2 ፤ሉቃ.1:30-33)

5. ከይሁዳ ነገድ መወለዱን የሚነገር ትንቢት፣

(ዘፍ.49:10)በትረ መንግሥት ከይሁዳ አይጠፋም፣የገዥም ዘንግ ከእግሮቹ መካከል ገዥ የሆነው እስኪመጣ ድረስ። የአሕዛብ መታዘዝም ለእርሱ ይሆናል።

ፍጻሜ፤ (ሉቃ.3:33)—የኤስሮም ልጅ የያሁዳ ልጅ የያዕቆብ ልጅ——።

6. የዳዊት አልጋ ወራሽነቱን የሚነገር ትንቢት፣

(ኢሳ.9:7፤11:5፤)ሕፃን ተወልዶልናልና፣ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፣ አለቅነቱም በጫንቃው ላይ ይሆናል፣ስሙም ድንቅ/መካር፣ኀያልአምላክ፣የዘለዓለም አባት፣የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል። ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘለዓለም ድረስ በፍርድና በጽድቅ ያጸናውና ይደግፈው ዘንድ በዳዊት ዙፋንና በመንግሥቱ ላይ አለቅነቱ ይበዛል፣ለሰላሙም ፍጻሜ የለውም

ፍጻሜ፣(ማቴ.1:7) የዳዊት ልጅ የአብርሃም ልጅ፣ የኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ መጽሐፍ።

7. የሚወለድበትን ቦታ የሚናገር ትንቢት፣

(ሚክ.5:2) አንችም ቤተ ልሔም ኤፍራታ ሆይ!አንቺ በይሁዳ አእላፋት መካከል ትሆኚ ዘንድ ታናሽ ነሽ፣ከአንቺ ግን አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘለዓለም የሆነ በእስራኤል ላይ ገዥ የሚሆን ይወ ጣልኛል።—።

ፍጻሜ፣ (ማቴ.2:1) ኢየሱስም በይሁዳ ቤተ ልሔም በንጉሡ በሄሮድስ ዘመን በተወለደ ጊዜ——። (ሉቃ.2:4-7)

8. የሚወለድበትን ጊዜ የተናገረ ትንቢት፤

(ዳን.9:25) ስለዚህ ዕወቅ አስተውልም፣ኢየሩሳሌምን ለመጠገንና ለመሥራት ትእዛዙ ከሚወጣበት ጀምሮ እስከ አለቃው እስከ መሲሕ ድረስ ሰባት ሱባኤና ስድሳ ሁለት ሱባኤ ይሆናል፤እስዋም በጭንቀት ዘመን ከኀዳናና ከቅጥር ጋራ ትሠራለች። ከስባ ሁለት ጊዜ ሰባትም በኋላ መሲሕ ይገደላል፣በእርሱም ዘንድ ምንም የለም፣የሚመጣውም አለቃ ሕዝብ ከተማይቱንና መቅደሱን ያጠፋል።——።

ፍጻሜ፣(ሉቃ.2:1-5)በዚያም ወራት ዓለሙ ሁሉ እንዲጻፍ ከአውግስጦስ ቄሳር ትእዛዝ ወጣች።——።

9. ከድንግል ስለመወለዱ የሚናገር ትንቢት፤

(ኢሳ.7:14)ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል፣እነሆ!ድንግል ትፀንሳለች፤ወንድ ልጅም ትወልዳለች፣ስሙንም ዐማኑኤል ብላ ትጠራዋለች (ትለዋለች)።

ፍጻሜ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደበት ሁኔታ እንዲህ ነው፤እናቱ ማርያም ለዮሴፍ ታጭታ ሳለች፣ሳይገናኙ፣በመንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ተገኘች። እጮኛዋ ዮሴፍም ደግ ሰው ስለነበረ ማርያምን በሰው ፊት ሊያጋልጣት አልፈለገም። ስለዚህ በስውር ሊተዋት አሰበ። ይህን ነገር ሲያስብ ሳለ የእግዚአብሔር መልአክ በሕልም ተገልጦለት እንዲህ አለው። "የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ!እጮኛህ ማርያም የፀነሰችው በመንፈስ ቅዱስ ስለሆነ እርስዋን ወደ ቤትህ ለመውሰድ አትፍራ። እርስዋ ወንድ ልጅ ትወልዳለች። እርሱም ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ስለሚያድናቸው ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ። "ይህም ሁሉ የሆነው እግዚአብሔር በነቢዩ እንዲህ ሲል የተናገረው እንዲፈጸም ነው። "እነሆ! ድንግል ትፀንሳለች፣ወንድ ልጅም ትወልዳለች፣ስሙም ዐማኑኤል ተብሎ ይጠራል።" ዐማኑኤል ማለትም እግዚአብሔር ከእኛ ጋራ ነው ማለት ነው።

10. <u>እናቱም ዘለዓለም ድንግል ስለመሆንዋ አሁንም ትንቢት፤</u>

በድግልና ለመውለድዋ ከላይ የተጠቀሰውን መልሶ ማስተዋል ይበቃል ዘለዓለም ድንግል ለመሆንዋ ግን የሚከተሉትን ጥቅሶች እነሆ! (ሕዝ.44:1)ወደ ምሥራቅም ወደ ሚመለከተው ወደ መቅደሱ በር አወጣኝ፣ተዘግቶም ነበር፤እግዚአብሔርም እንዲህ አለኝ፣ይህ በር እንደ ተዘጋ ይኖራል እንጂ ከቶ አይከፍትም፣የእስራኤል አምላክ የሆንሁ እኔ እግዚአብሔር የገባሁበት ስለሆነ የሰው ዘር የሆነ ሁሉ በዚህ በር መጠቀም አይችልም። ስለዚህ እንደ ተዘጋ ይኖራል። (መሐ.4:12) እኅቴ ሙሽሪት የተቆለፈ ገነት (የአትክልት ቦታ፥ተጋን)የተዘጋ ምንጭ (የታተመ ነቅዕ)። በዚህም መግቢያ የሌለው ተጋን (ገነት)፣አፍ የሌለው ምንጭ በማለቱ ዘለዓለማዊ ድንግልናዋን ያሳያል።

<u>ለፍጻሜ፤</u> (ማቴ.1:18 ፤ሉቃ.11:27:) ይመለከቷል።

11. <u>የሕፃናት መታረድ ትንቢት፤</u>

(ኤር.31:15) እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣"የለቅሶና የብዙ ዋይታ ድምፅ በራማ ተሰማ፣ራሔል ስለልጆችዋ አለቀሰች።"

<u>ፍጻሜ፤</u> ይህ በሐዲስ ቃል ለቃል ተፈጽሟል። (ማቴ.2:17)።

12. <u>የወደ ግብጽ መሰደድ ትንቢት፤</u>

(ሆሴ.11:1) እግዚአብሔርም እንዲህ ይላል፣"እስራኤል ሕፃን በነበረ ጊዜ ወደድሁት የምወደውንም ልጄን ከግብጽ እንዲወጣ ጠራሁት።

<u>ፍጻሜ፤</u> (ማቴ.2:14) ዮሴፍም በሌሊት ተነሣና ሕፃኑን ከእናቱ ጋራ ይዞ ወደ ግብጽ ሄደ። ከዚያም ሄሮድስ እስኪሞት ድረስ ቆየ፤ይህም የሆነው እግዚአብሔር በነቢዩ"ልጄን ከግብጽ ጠራሁት" ያለው ቃል እንዲፈጸም ነው።

**13. <u>ትንቢት ስለገሊላ ስብከት፤</u>**

(ኢሳ.9:1-2)ነገር ግን ተጨንቃ ትኖር ለነበረችው ጽዮን ከእንግዲህ ወዲያ ትካዜ አይገጥማትም። በቀድሞ ዘመን የዛብሎንና የንፍታሌም ምድር ተዋርዳ ትኖር ነበር፤በኋለኛው ዘመን ግን ከሚድተራንያን ባሕር ምሥራቅ ጀምሮ እስከ የርዳኖስ ማዶ ያለው፤በተለይም አረማውያን ሰፍረውበት የነበረው የገሊላ ባሕር ክብርን ይጎናጸፋል። በጨለማ ይኖር የነበረ ሕዝብ እነሆ!ታላቅ ብርሃን አየ። በሞት ጥላ አገር ውስጥ ለሚኖሩትም ሁሉ፤ብርሃን ወጣላቸው።

<u>ፍጻሜ፤</u> ኢየሱስ የማስተማር ሥራውን በገሊላ በጀመረ ጊዜ ይህ ትንቢት ቃል በቃል ተደግሟል፤ተፈጽሟል። (ማቴ.4:12-17 ፤ማር. 1: 14-15 ፤ሉቃ. 4:14-15)

**14. <u>የነቢዩ መምጣት ትንቢት፤</u>**

(ዘጸ.18:15)እግዚአብሔር ከወገኖቻችሁ መካከል እንደኔ ያለ ነቢይ መርጦ ያስነሣላችኋል፤እርሱ የሚላችሁን ሁሉ በመስማት ታዛዥ ሆኑ።

<u>ፍጻሜ፤</u> (ማር.9:7)የምወደው ልጄ ይህ ነው፤እሱን ስሙት የሚል ድምፅ መጣ።

**15. <u>ካህን ከመ መልከጼዴቅ፤</u>**

(መዝ.110:4) እግዚአብሔር በመልከ ጼዴቅ ሹመት ለዘለዓለም ካህን ትሆናለህ ብሎ ማለ። መሐላውም የማይሻር ነው።

<u>ፍጻሜ፤</u> (ዕብ.6:20) ወደዚህም መቅደስ ኢየሱስ እንደ መልከ ጼዴቅ የክህነት ሹመት ለዘለዓለም ሊቀ ካህናት ሆኖ፤ስለኛ ቀድሞ ገብቷል።

**16. <u>ከአይሁድ እንደ ሚገፉ የሚናገር ትንቢት፤</u>**

(ኢሳ.53:3)------። እኛም ንቀን ገለል አደረግነው፤እርሱ ከመከራና ከሕማም የማይለይ የሐዘን ሰው ሆነ፤ወደ እሱ የሚመለከት አንድም ሰው አልነበረም። እኛም በንቀት እንደ ኢምንት አየነው።

<u>ፍጻሜ፤</u>(ዮሐ.1:11) ወደ ወገኖቹ መጣ ፤ወገኖቹ ግን አልተቀበሉትም።

**17. <u>ስለ ክርስቶስ መለያ ስጦታዎች ትንቢት፤</u>**

(ኢሳ.11:2)የእግዚአብሔር መንፈስ በእሱ ላይ ይኖራል፤የጥበብና የማስተዋል መንፈስ የምክርና የኀይል መንፈስ፤የዕውቀትና የእግዚአብሔርን መፍራት መንፈስ ያርፍበታል፤------።

<u>ፍጻሜ፤</u> (ሉቃ.2:52)ኢየሱስም በእግዚአብሔርና በሰው ዘንድ የተወደደ ሆኖ በጥበብና በቁመት እያደገ ይሄድ ነበር። (ሉቃ.4:16-19)።

**18. <u>በድባቤ ኢየሩሳሌም መግባቱን የሚገልጥ ትንቢት፤</u>**

(ዘካር.9: 9)ጽዮን ሆይ! ደስ ይበልሽ፤ኢየሩሳሌም ሆይ! በደስታ እልል በይ፤እነሆ! ንጉሥሽ ትሑት ሆኖ፤ በአህያይቱ ግልገልም በውርንጭላ ይቱ ላይ ተቀምጦ በድል አድራጊነት ወደ አንቺ ይመጣል።------።

ፍጻሜ፣ (ማቴ.21:1-11፤ማር.11:1-11፤ሉቃ.19:28-40፤ዮሐ.12:13-14፤) ስለዚህ የዘንባባ ቅርንጫፍ ይዘው ሊቀበሉት ወጡ። "ሆሳዕና! በጌታ ስም የሚመጣ የእስራኤል ንጉሥ የተባረከ ነው! "እያሉ ጮሁ።

19. በወዳጁ ስለመካዱ ትንቢት፣

(መዝ. 41: 9) እንጀራዬን ከኔ ጋር አብሮ የበላ ክሌብ የምተማመንበት ወዳጄ እንኳ በእኔ ላይ በጠላትነት ተነሥቷል።

ፍጻሜ፤ (ማር.14:10)ከዐሥራ ሁለቱ አንዱ አስቆሮታዊው ይሁዳ ኢየሱስን አሳልፎ ለመስጠት ወደ ካህናት አለቆች ሄደ። እነሱም ይህን ባወቁ ጊዜ ደስ አላቸው። ገንዘብም ሊሰጡት ቃል ገቡለት፡――።

20. በ30 ብር መሼጡን የሚናገር ትንቢት፣

(ዘካ.11:12)እኔም "ብትፈቅዱ ደመወዜን ስጡኝ፣ባትፈቅዱ ተውት" አልኳቸው፤እነርሱም የአገልግሎቴን ዋጋ ሠላሳ ብር ስጡኝ።እግዚአብ ሔርም ከቤተ መቅደሱ የገንዘብ መቀበያ ሣጥን ጣለው" አለኝ። ስለ ዚህም "ለኔ በቂ ደመወዝ ነው" ብለው የሰጡኝን ሠላሳ ብር ወስጄ ከቤተ መቅደሱ ገንዘብ መቀበያ ሣጥን ውስጥ ጣልሁት።

ፍጻሜ፣ (ማቴ.26:15፤ማር.14:10-11፤ሉቃ.22:36) "ኢየሱስን አሳልፌ ብሰጣችሁ ምን ትሰጡኛላችሁ" አላቸው፣እነሱም ሠላሳ ጥሬ ብር ሰጡት፡――፡(27:3-5)ኢየሱስን አሳልፎ የሰጠው ይሁዳ፣ኢየሱስ እን ደ ተፈረደበት ባየ ጊዜ ተጸጸተ፣ሠላሳውንም ጥሬ ብር ለካህናት አለቆችና ሽማግሎች እንዲህ ብሎ መልሶ ሰጣቸው፤"ንጹሑን ሰው ለሞት አሳልፌ በመስጠቴ በድያለሁ። "እነሱ ግን" ታዲያ እኛ ምን ቸገረን? የራስህ ጉዳይ ነው አሉት። እሱም ሠላሳውን ጥሬ ብር በቤተ መቅደስ ውስጥ በትኖ ትቶላቸው ወጣ።

21. ለሸክላ ሠሪ ስለ ተሰጠ ገንዘብ ትንቢት፣

(ዘካ.11:13) እግዚአብሔርም የተስማሙበትን የከበረውን ዋጋዬን ወደ ሸክላ ሠሪው አኑረው አለኝ። ሠላሳውንም ብር ወስጄሁ በእግዚአብሔ ርም ቤት ወደ ሸክላ ሠሪው አኖርሁት።

ፍጻሜ፤ (ማቴ.26:6-7፤27:3-4፤ማር.15:1፤ሉቃ.23:1-3፤ዮሐ.18:28-32)ለንባቡ ቁጥር 20ን ይመለከቷል።

22. ስለውሸታም የሐሰት ምስክሮች ትንቢት፣

(መዝ.27: 12፤ 35:11፤)ለጠላቶቼ ፈቃድ አትስጠኝ፣የሐሰት ምስክሮች ተነሥተውብኛልና፣በዐመፃም የምላቸው።ተግፍ ምስክሮች ይነሣሉ፣የማ ላውቀውንም ይለክሱብኛል።

ፍጻሜ፣(ማቴ.26:57-62፤ ማር.14:53-65፤ ሉቃ.22:5455፤6371፤ ዮሐ.18:13-14፤19-24)የካህናት አለቆችና የሸንጎውም አባሎች ሁሉ

በኢየሱስ ላይ የሞት ፍርድ ለማስፈረድ የሐሰት ምስክር ይፈልጉ ነበር።————።

## 23. <u>ሲከሰስ ዝም ስለማለቱ ትንቢት፣</u>

(ኢሳ.53:7) "እርሱ ብዙ ግፍ ሲደርስበት መከራን ታግሦ ተቀበለ እንጂ አንድ ቃል እንኳ አልተናገረም። እርሱ ለመታረድ እንደ ሚወሰድ ጥቦትና እንደሚሸለትም በግ ዝም አለ። አንድም ቃል አልተናገረም። እርሱ በግፍ ተይዞ ተፈረደበት፣ወደ ሚገደልበትም ቦታ ተወሰደ፣ወገን እንደሌለውም ተቆጠረ፣ስለሕዝባችንም ኀጢአት ሞት ተፈርዶበት ከሕያዋን ምድር ተወገደ። ምንም ወንጀል ሳይፈጽም፣በአንደበቱም ሐሰት ሳይገኝበት፣በሞቱ ከክፉ አድራጊዎች ጋራ ተቆጠረ፣በባለጸጋም መቃብር ተቀበረ። "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ "ይህን ሁሉ መከራ እንዲቀበል የእኔ ፈቃድ ነበር፤የእርሱም ሞት የኀጢአትን ይቅርታ የሚያስገኝ መሥዋዕት ነበር። ስለዚህ እሱ ትውልዱን ያያል፣ረዥም ዘመንም ይኖራል፣በርሱም አማካኝነት የእኔ ዓላማ ይፈጸማል። ሕይወትን ከሚያሠቃይ ከብዙ መከራ በኋላ የሕይወትን ብርሃን በማየት እንደ ገና ደስ ይለዋል። ያን ሁሉ መከራ የተቀበለውም በከንቱ አለመሆኑን ይገነዘባል። በእርሱ ደስ የሚለኝ የእኔ ፍጹም አገልጋይ ብዙዎች ሊቀበሉት የሚገባውን ቅጣት ተሸክሞ እነሱን ከኀጢአት ነጻ ያደርጋል። ስለዚህም ለእርሱ የክብር ቦታ እሰጠዋለሁ። በኃያላንና በታላቆች መካከል የከበረ ይሆናል። ምክንያቱ ም እርሱ ሕይወቱን በፈቃዱ ለሞት አሳልፎ ስጥቷልና፣ከክፉ አድራጊ ዎች ጋራም ተቆጥሯል። የብዙዎቹን በደል ተሸክሟል፤የኀጢአትንም ይቅርታ ያገኙ ዘንድ ማልዶላቸዋል (ጸልዮአል)።

ክቡር አንባቢ ሆይ!ክርሲቲያንም ሆንህ ሰላም!ይህን ትንቢት ክርስቶስ የፈጸመው ቃል በቃል ነው፣ከዚህ ሌላ ወንጌልም አትናገር፣ሐዋርያት ም አላስተማሩ፣እርቶዶክስ ክርስቲያንም ሌላ አያምን። ለፍጻሜውም የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንቧል፤(ማቴ.26:62-67 ፤27:12-14) ከዚህ ቀጥለህ ወንጌሉ እስኪያልቅ አንብ። (ማር.15:6-15፤ሉቃ.23:13-25 ፤ዮሐ.18:39-40፤ 19:1-16)

## 24. <u>ተመታ፣ተጸፋ፣ምራቅ ተተፋበት፣</u>

(ኢሳ.50:6) ለሚገርፉኝ ጀርባዬን ስጠኋቸው፣ሲሰድቡኝና ጽሕሜን ሲነጩ፣እየተፉም ሲያፌዙብኝ ፊቴን ከእነሱ በማዞር አልሸሸግሁም።
<u>ፍጻሜ፣</u> (ማር.14:65፤15:17፤ዮሐ.19:1-3፤18:22)አንዳንዶችም ምራቃቸውን እንትፍ ይሉበት ጀመር፣ዐይኑንም በጨርቅ ሸፍነው፣ "አ ንተ ነቢይ ሆይ! እስቲ ማን እንደመታህ ዕወቅ "እያሉ በቡጢ ይመቱት ነበር። ሌሎችም በጥፊ እየመቱ ወሰዱት።

25. <u>ያለ ምክንያት ለመጠላቱ ትንቢት፣</u>
(መዝ.69:4፤109:3-5) ያለ ምክንያት የሚጠሉኝ ከራሴ ፀጉር ይልቅ በዝተዋል፤ጠላቶቼ በእኔ ላይ ሐሰት ይናገራሉ።
<u>ፍጻሜ፤</u> (ዮሐ.15:23-25) እኔን የሚጠላ አባቴንም ይጠላል፤ሌላ ሰው ያላደረገውን ሥራ በመካከላቸው ባላደርግ ኖሮ ኀጢአት ባልሆነባቸ ውም ነበር። አሁን ግን ይህን ሁሉ ካዩ በኋላ እኔንም አባቴንም ጠል ተዋል። ይህም የሆነው ያለ ምክንያት ጠሉኝ ተብሎ በሕጋቸው የተጻ ፈው ቃል እንዲፈጸም ነው።
26. <u>ዓለምን ለማዳን ተሰቃየ፤</u>
(ኢሳ.53:4-5፤6:12)እኛ ልንሸከመው የሚገባንን መከራና ሕመም እሱ ተሸከመ፣ይህም በእርሱ ላይ የደረሰበት ግርፋትና መከራ ሁሉ ከእግዚ አብሔር የተላከ ቅጣት እንደሆነ አድርገን አሰብን።
<u>ፍጻሜ</u>፣(ማቴ.8:1-17፣ሮሜ.4:25 ፤1ቆሮ.15:3) ይህንም በማድረጉ በነቢዩ ኢሳይያስ "እርሱ ደዌያችንን ተቀበለ፣ሕማማችንንም ተሸከመ" የተባለው ትንቢት ተፈጸመ።
27. <u>ዓለምን ለማዳን ከኀጢአተኞች ጋራ ተሰቀለ፣</u>
ከዚህ በፊት በቁጥር 22 የተጸፈውን ኢሳ.53 ን ያነቧል።
<u>ለፍጻሜ</u>፣ (ማቴ.27:38፤ማር.15:27-28፤ሉቃ.23:33) በዚያን ጊዜ ሁለ ት ወምበዴዎች አንዱ በቀኝ አንዱ በግራ ከኢየሱስ ጋራ ተሰቀሉ።
28. <u>እጁና እግሩን ለመቸንከሩ ትንቢት፣</u>
(መዝ.22:16፤ዘካር.12:16)ክፉ ሰዎች እንደ ውሻ መንጋ ከበቡኝ፣እጆ ቼንና እግሮቼን ቸነከሩኝ።
<u>ፍጻሜ</u>፣(ዮሐ.20:27፤ 19:37፤ 20:25-26)ከዚህ በኋላ ቶማስን "ጣትህን ወዲህ አምጣና እጆቼን እይ እጅህንም አምጣና በጎኔ ውስጥ አግባው እመን እንጂ እምነተ ቢስ አትሁን" አለው።
28. <u>ይሰደባል፣ይቀለድበታል፤</u>
(መዝ.22:7-8) የሚያዩኝ ሁሉ ይዘባበቱብኛል፣በንቀት ራሳቸውን እየነ ቀነቁ ከንፈራቸውን ያጣምሙብኛል። ደግሞ በእግዚአብሔ ተማምነህ አልነበረምን? ታዲያ ለምን አያድንህም? እግዚአብሔር የሚወድህ ከሆነ ለምን አይረዳህም? ይሉኛል።
<u>ፍጻሜ፤</u> (ማቴ.27:39-40፤41-44፤ማር.15:29-32) በአጠገቡ ያልፉ የነበሩትም ሰዎች በንቀት ራሳቸውን እየነቀነቁ፣"አንተ ቤተ መቅደስን የምታፈርስና በሦስት ቀን የምትሠራው፣እስቲ ራስህን አድን፣የእግዚ አብሔር ልጅ ከሆንህ፣እስቲ ከመስቀል ውረድ" እያሉ ያላግጡበት ነበር። በዚህ ዐይነት የካህናት አለቆች ከሙሴ ሕግ መምህራንና

ኸማግሎች ጋራ እንዲህ እያሉ ያፌዙበት ነበር። ሌሎቹን አዳነ፤ራሱን ግን ማዳን አይችልም፤እርሱ የእስራኤል ንጉሥ ከሆነ እስቲ አሁን ከመስቀል ይውረድ፤እኛም እንመንበት። እሱ በእግዚአብሔር ታምኗል የእግዚአብሔርም ልጅ ነኝ ብሏል፤ስለዚህ እግዚአብሔር የሚወደው ከሆነ እስኪ አሁን ያድነው.....።

30. <u>መጣጣና ሖሞት ለመሰጠቱ የተነገረ ትንቢት፤</u>

(መዝ.68-21)በምግቤ ውስጥ መራራ ነገር ቀላቀሉ፤በጠማኝም ጊዜ በውኃ ፈንታ ሆምጣጤ ሰጡኝ።

<u>ፍጻሜ፤</u>(ማቴ.27:34፡48፤ዮሐ.19:29)ከዚያ ሆምጣጤ የሞላበት ዕቃ ተቀምጦ ነበር፤ስለዚህ ከዚያ የነበሩ ሰዎች ሆምጣጤውን በእስፖንጅ ሞሉና በሂሶጥ እንጨት አንጠልጥለው ወደ አፉ አቀረቡለት። ኢየሱስም ሆምጣ ውን ከቀመሰ በኋላ "ተፈጸመ" አለ።

31. <u>ለጠላቶቹ ስለ መጸለዩ ትንቢት፤</u>

(መዝ.109:4)ምንም እንኳ እኔ የምወዳቸውና የምጸልይላቸው ቢሆንም እነሱ ይቃወሙኛል።

<u>ፍጻሜ፤</u> (ሉቃ.23:34)ከዚህ በኋላ ኢየሱስ "አባቴ ሆይ! የሚያደርጉትን ስለማያውቁ ይቅር በላቸው" አለ።

32. <u>ጎድኑ የሚወጋ ስለመሆኑ ትንቢት፤</u>

(ዘካ.12:10)የዳዊትን ዝርያዎችና የቀሩትን የኢየሩሳሌም ሕዝብ በምሕረት መንፈስና በጸሎት መንፈስ እሞላቸዋለሁ፤ስለዚህ ያንን የወጉትን ያዩታል፤አንድ ልጁንም እንዳጣ ሰው በመረረ ሁኔታ ያዝኑለታል።

<u>ፍጻሜ፤</u>(ዮሐ.19:34)ነገር ግን ከወታደሮቹ አንዱ ጎኑን በጦር ወጋው ወዲያውም ከጎኑ ደምና ውኃ ወጣ።

33. <u>ከአጥንቱ አንዱም አትሰበርም፤ይህም በትንቢት፤</u>

(መዝ.34:20)እግዚአብሔርም በጥንቃቄ ስለሚጠብቀው፤ከአጥንቶቹ አንዱ እንኳ አይሰበርም።

<u>ፍጻሜ፤</u> (ዮሐ.19:33)ወደ ኢየሱስ በሄዱ ጊዜ ግን ቀደም ብሎ እንደ ሞተ አይተው ጭኑን አልሰበሩም።

34. <u>ከወንበዶች ጋራ ይቀበራል የሚል ትንቢት፤</u>

(ኢሳ.53:9)ምንም ወንጀል ሳይሠራ፤በአንደበቱም ሐሰት ሳይገኝበት፤በሞቱ ከክፉ አድራጊዎች ጋራ ተቆጠረ። በባለጸጋም መቃብር ተቀበረ።

<u>ፍጻሜ፤</u>(ማቴ.27:57-60)በመሸ ጊዜ የአርማትያስ ሰው የሆነ ዮሴፍ የሚባል አንድ ሀብታም ወደዚያ መጣ። እርሱም የኢየሱስ ደቀ መዝሙር ነበር። ይህ ሰው ወደ ጲላጦስ ሄደና የኢየሱስን አስከሬን ለመነ፤

ጲላጦስም አስከሬኑ እንዲሰጠው አዘዘ። ስለዚህ ዮሴፍ አስከሬኑን አውርዶ በንጹሕ ጨርቅ ሸፍኖ ከአለት ተወቅሮ በተዘጋጀው በራሱ መቃብር ቀበረው።

35. <u>ትንቢት ስለ ትንሣኤው የተነገረ፤</u>

(መዝ.16:10)ነፍሴን በሲኦል አትተዋትም፤ቅዱስህንም መበስበስ እን ዲደርስበት አታድርገውም።

<u>ፍጻሜ፤</u> (ማቴ.28:16-20፤ማር.16:14-18፤ሉቃ.24:36-49)በዚያኑ ቀን እሑድ ማታ ደቀ መዛሙርቱ የአይሁድን ባለሥልጣኖች በመፍራት በራፎቹን ዘግተው ተሰብስበው ነበር፤በሮቹ ተዘግተው ሳለ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ ወደ ተሰበሰቡበት ቤት ገባ። በመካከላቸውም ቆሞ ሰላም ለእናንተ ይሁን አላቸው። እንደዚህም ብሎ እጆቹንና ጎኑን አሳያቸው።———።

36. (መዝ.68:18)ምርኮን ማርከህ ወደ ላይ ወጣህ ከሰዎቹም ስጦታን ተቀብለህ።

<u>ተፍጻሜት፤</u> (ሉቃ.24:50-51)ከዚህ በኋላ ኢየሱስ እነርሱን ከኢየሩሳሌም አውጥቶ እስከ ቢታንያ ወሰዳቸው፤በዚያም እጆቹን ዘርግቶ ባረካቸው፤ሲባርካቸውም ሳለ ከነርሱ ተለይቶ ወደ ሰማይ ዐረገ።

37. <u>እንኳንስ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስና ስለአስቆሮቱ ይሁዳም ትንቢት ተነግሯል</u>። (መዝ.109:7-8)ጸሎቱ እንደ ኀጢአት ይቆጠርበት፤ዕድሜውም በቶሎ ይቀጭ፤ሥራውንም ሌላ ሰው ይውሰደበት።

<u>ተፍጻሜት፤</u> (ግብሐ.1,18-20)ይህም የሆነበት ምክያት በመዝሙር መጽሐፍ፤"መኖሪያው ባዶ ይሁን፤ማንም አይኑርበት፤ደግሞ ሹመቱን ሌላ ሰው ይውሰድበት" የሚል ተጽፎ ስለነበረ ነው። እውነትን ፈላጊ ሰው ቅዱሳት መጻሕፍትን ቢያነብ ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ሌላ ትንቢታትና ተፍጻሜታት እንደሚያገኝ የታመነ ነው። እንደዚህ ብዙ ትንቢት ተነግሮለት የፈጸመ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። ከእሱ በፊትም የተነሡት ነቢያትም ሆነ በኋላው የተነሡ ሐሰውተ ነቢያት (ነቢያትን የሚያስተባብሉ ውሼታም ነቢይ ነን ባዮች)ከዚህ በላይ ከተነገሩት ትንቢቶች አራቱን አልፈጸሙም። እንዲያውም በኋላው የተነሡትማ ሐሰት እያቀናበሩ ጎጋውን ከማደናገር በቀር የፈጸሙት ትንቢት የለም።

# ምዕራፍ 8፤

## ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ተነሥቷል።

ቁርአንና ስላም እንደሚሉት ሳይሆን፣ክርስቶስ በብሉይ ኪዳን በነቢያት ትንቢት፣እንደ ተነገረ፣በሐዲስ ኪዳኑ እሱ ራሱ አስቀድሞ እንደ ተነባ፣ሐዋርያትም ተቀብለው እንደ ሰበኩ፣ተገፎ፣ረገርፎ፣ተሰቅሎ ሙቶ፣በሞተ በሦስተኛው ቀን በገዛ ኀይሉ መግነዝ ፍቱልኝ፣መቃብር ክፈቱልኝ ሳይል ተነሥቶ፣በተነሣ በአርባኛው ቀን ወደ ሰማት ዐርጎ በአባቱ ቀኝ በክብር ተቀምጧል። ለዚህም መረጃ ,ከብዙ በጥቂቱ ከነቢያትም ከወንጌልም ከዐይን ምስክሮች ሐዋርያትም ከዚህ ቀጥለን እንጠቅሳለን።

ኢሳያስ 53 ምዕራፉን በጠቅላላ ያነቧል።

1. "የሰማነውንስ ነገር ማን አምኖናል? የእግዚአብሔርስ ክንድ ለማን ተገልጧል? በፊቱ እንደ ቡቃያ ከደረቅም መሬት እንደ ሥር አድጓል መልክና ውበት የለውም፤ባየነውም ጊዜ እንወደው ዘንድ መልክና ውበት የለውም። የተናቀ ከሰውም የተጠላ፣የሕመም ሰው ደዌንም የሚያውቅ ነው፤ሰውም ፊቱን እንደ ሚሰውሩበት የተናተ ነው፣እኛም አላከበርነውም፡፡በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ፣ሕመማችንንም ተሸክሟል፤እኛ ግን እንደ ተመታ በእግዚአብሔርም እንደ ተቀሠፈ እንደ ተቸገረም ቆጠርነው። እሱ ግን ስለመተላለፋችን ቆሰለ፣ስለ በደላችንም ደቀቀ፣የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእሱ ላይ ነበረ። በእሱም ቁስል እኛ ተፈወስን። እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን፤ከኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ፤እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ።ተጨነቀ፣ተሠቃየም አፉንም አልከፈተም፣ለመታረድ እንደ ሚነዳ ጠቦት፣በሸላቹም ፊት ዝም እንደሚል በግ፣አፉን አልከፈተም። በማስጨነቅና በፍርድ ተወሰደ፣ስለ ሕዝቤ ኀጢአት ተመቶ ከሕያዋን ምድር እንደ ተወገደ ከትውልዱ ማን አስተዋለ? ከክፉዎችም ጋር መቃብሩን አደረጉ፣ከባለጠጎችም ጋር በሞቱ፣ሁኖም ግፍን አላደረገም ነበር። በአፉም ተንኮል አልተገኘበትም ነበር። እግዚአብሔርም በደዌ ያደቀው ዘንድ፤ነፍሱን ስለ ኀጢአት መሥዋዕት ካደረገ በኋላ ዘሩን ያያል፣ዕድሜውም ይረዝማል፤የእግዚአብሔርም ፈቃድ በእጁ ይከናወናል። ከነፍሱ ድካም ብርሃን ያያል፤ደስም ይለዋል፤ጻድቅ ባሪያየም በእውነቱ ብዙ ሰዎችን ያጸድቃል፣ኀጢአታቸውንም ይሸከማል። ስለዚህም እርሱ ብዙዎቹን ይወርሳል፣ከኀያላንም ጋር ምርኮን ይካፈላል፣ነፍሱን ለሞት አሳልፎ ሰጥቷልና፣ከዐመፀኞችም ጋራ ተቆጥሯልና፣እሱ ግን የብዙ ሰዎችን ኀጢአት ተሸከመ፣ስለ ዐመፀኞችም ማለደ።

በዚህ ምዕራፍ ነቢዩ ኢሳያስ ከክርስቶስ ልደት በፊት ስምንት መቶ ዘመን አስቀድሞ የክርስቶስን ሞትና ትንሣኤ ቁልጭ አድርጎ ተንትኗል። ይህ ትንቢት ከእሱም በፊት እንደ ሚከተለው ተነግሯል።

2. (መዝ.9-10) ስለዚህ ልቤን ደስ አለው፣ምላሴም ሐሤት አደረገች፣ ሥጋዬ ደግሞ በተስፋ ታድራለች፣ነፍሴን በሲኦል አተዋትምናፅ፣ቅዱስ ህንም መበስበስን ያይ ዘንድ አትተወውም።

3. (77:65-67) እግዚአብሔር ከእንቅልፍ እንደሚነቃ ተነሣ፣የወይን ስ ካር እንደተወው እንደ ኀያልም ሰው፣ጠላቶቹንም በኋላቸው መታ፣የዘ ለዓለምን ነውር ሰጣቸው።

4. እሱ ራሱም (ማቴ.16:21፤20:19) ከዚያን ቀን ጀምሮ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ይሄድ ከሽማግሌችና ከካህናት አለቆች ከጻሐፊዎችም ብዙ መከራ ይቀበልና ይገደል ዘንድ በሦስተኛውም ቀን ይነሣ ዘንድ እንዲገባው ለደቀ መዛሙርቱ ይገልጥላቸው ጀመር። ይህን ሰምቶ ጴጥሮስ አይድርስብህ ቢለው፣ወግድ ከፊቴ ዕንቅፋት አትሁንብኝ ብሎ ገሠጸው።

5. (ማቴ.26:30-32)በዚያን ጊዜ ኢየሱስ በዚች ሌሊት ሁላችሁም በእኔ ትሰናከላላችሁ፣እረኛውን እመታለሁ የመንጋውም በጎች ይበተናሉ የሚል ተጽፏልና፤ከተነሣሁ በኋላ ግን ወደ ገሊላ እቀድማችኋለሁ አላቸው።

6. (ማር.9:9፤14:25)ከተራራውም ሲወርዱ የሰው ልጅ ከሙታን እስኪነሣ ድረስ ያዩትን ለማንም እንዳይነግሩ አዘዛቸው።

7. (ዮሐ.2:19)ኢየሱስም መልሶ፣ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት በሦስት ቀንም አነሣዋለሁ አላቸው።

8. ከዚህ በላይ የክርስቶስ ሕማም፣ሞት፣ትንሣኤ ርግጥ መሆናቸውን ለመረዳት የሚከተሉትን የዐይን ምስክሮች የጻፏቸውን የወንጌል ጥቅሶች ለማንበብ እንጠቁማለን፤
(ማቴ.26:30-75፤27:1-66፤28:1-20፤ ማር.14:1-72፤15:1-47፤16:1 20፤ሉቃ.22:1-71፤23:1-56፤24:1-53፤ዮሐ.18:1-40፤19:142፤20:1-31፤21:1 21)

9. ( ዮሐ.20:16)ሙቶ ከተነሣም በኋላ ለማርያም መግደላዊት ገና ወደ አባቴ አላረግሁምና አትንኪኝ፣ነገር ግን ወደ ወንድሞቼ ሂደሽ ወደ አባቴና አባታችሁ__________፣አርጋለሁ ብለሽ ንገሪያቸው አላት። ክርስቶስ የመጣው የሥላሴን ሦስትነት አንድነት ለሰው ልጅ ለመግለ ጥ ዓለምን ለማዳን፣በአርአያው ለማስተማር ስለሆነ፣ጌሊ፣ጌሊውን

ጠቀስን እንጂ፣በሞላ አራቱ ወንጌሎች የሚያሳዩት የክርስቶስን የአምላክ ልጅነት፣ዓለምን ለማዳን በፈቃዱ ከአባቱ እግዚአብሔር አብ ተልኮ መምጣቱን በዝርዝር ይናገራሉ።
እንዲሀ እንዲሀ ያለ ምስክር እያለ ነው፣መሐመዳውያን የኀሊና ዐይናቸውን ጨፍነው፣ክርስቶስ አልተሰቀለም፣ሙቶ አልተነሣም፣የአምላክ ልጅ ነኝ ብሎ አላስተማረም የሚሉ፣ በድንግልና የተወለደ ነቢይ ነው ይላሉ። ነቢይነቱን ግን አይቀበሉም።

<u>ሐዋርያት፣</u>

ቅዱስ ጴጥሮስ፣(ግብሐ.2:23-24)እሱንም በእግዚአብሔር በተወሰነው ሐሳቡና በቀደመው ዕውቀቱ ተሰጥቶት በዐመፀኞች እጅ ሰቅላችሁ ገደላችሁት። እግዚአብሔር ግን የሞትን ጣር አጥፍቶ አስነሣው፣ሞት ይይዘው ዘንድ አይችልምና።
10. (3:14-15)እናንተ ግን ቅዱሱን ጻድቁን ክዳችሁ ነፍስ ገዳዩን ሰው ይሰጣችሁ ዘንድ ለመናችሁ የሕይወትን ፈጣሪ ግን ገደላችሁት። እርሱ ግን እግዚአብሔር ከሙታን አስነሣው፣ለዚህም ነገር እኛ ምስክሮች ነን።
11. (10:39-40)እኛም በአይሁድ አገርና በኢየሩሳሌም ባደረገው ነገር ሁሉ ምስክሮች ነን፤እርሱንም በዕንጨት ላይ ሰቅለው ገደሉት። እርሱን እግዚአብሔር በሦስተኛው ቀን አስነሣው።

<u>ቅዱስ ጳውሎስ ፣</u>

12. (ግብሐ.17:2-3)ጳውሎስም እንደ ልማዱ ወደ እነሱ ምኵራብ ገባ፣ሦስት ሰንበትም ያህል ከእነሱ ጋራ ከመጻሕፍት እየጠቀሰ ያነጋገር (ይከራከር) ነበር፣ሲተረጕምም ክርስቶስ መከራ እንዲቀበልና ከሙታን እንዲነሣ ይገባው ዘንድ እያስረዳ፣ይህ እኔ የምሰብክላችሁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ይል ነበር።
13. (26:22-23)ከእግዚአብሔርም ዘንድ ረድኤት ተቀብዬ ለታናሹም ለታላቁም ስመሰክር እስከዚች ቀን ድረስ አለሁ። ነቢያትና ሙሴ ይሆን ዘንድ ያለውን፣ክርስቶስ መከራን እንዲቀበል፣በሙታንም ትንሣኤ ለሕዝብና ለአሕዛብ ብርሃን በመጀመሪያ ሊሰብክ እንዳለው፣ከተናገሩት በቀር፣አንድም እንኳ የተናገርሁት የለም።
14. (ሮሜ.1:3-4) ይህም ወንጌል በሥጋ ከዳዊት ዘር ስለተወለደ እንደ ቅድስና መንፈስ ግን ከሙታን መነሣት የተነሣ በኀይል የእግዚአብሔር ልጅ ሆና ስለተገለጠ ስለልጁ ነው፣እሱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።
ይህን ለምስክር ያህል፤ስላሞች በቁርአን የተነገረውን የመሐመድ ሐሰት ይዘው ክርስቶስ አልሞተም ስለሚሉ ጠቀስን እንጂ በመላ ሐዲሳት የሚያስተምሩት የኢየሱስን አምላክነት ለእኛ ሲል ሥጋ ለብሶ መሠቃየት፣መሞት፣መነሣት፣በሞተ በአርባ ቀኑ ወደ ሰማይ ዐርጎ በአባቱ ቀኝ በክብር መቀመጥን ነው።

## ምዕራፍ:9

## መንፈስ ቅዱስ እንጂ መሐመድ አይደለም።

አያ አሕመድ ዲዳትና መሰሎቹ ስለመንፈስ ቅዱስ የተነገረውን
ትንቢተ ክርስቶስ መሐመድ ነው እያሉ ያወራሉ፤ይህ ግን ልክ
አለመሆኑን በአለፉት ምዕራፎች አይተናል። በእርግጥ በግልጥ
ክርስቶስ ከእሱ በኋላ ደግ ነቢይ እንደማይመጣ ተናግሯል፣ይመጣል፣
ይላል ያለውም ከሦስቱ ሥላሴ አንዱ አካል መንፈስ ቅዱስን ነው
እንጂ ነቢይ አይደለም።

ምክንያቱስ ቢሉ? አንደኛ በኢየሩሳሌም ሁነው የአብን ተስፋ እንዲጠ
ብቁ አዝዟቸው ከአንድ አደራሽ ተሰብስበው ሲጠባበቁ ጌታ ባረገ
በዐሥረኛው ቀን መንፈስ ቅዱስ ወርዶ ደካሞችን፡ኀያላን፣ዲዳዎቹን
ርቱዓን፣ፈሪዎቹን ጥቡዓን አድርጎ ለስብከተ ወንጌል አዘጋጅቷቸዋል።
ሁለተኛ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ትጠመቃላችሁ ስላላቸው ባሥረኛው
ቀን ካልተጠመቁ፣መሐመድ የመጣው ከ600 ዘመን በኋላ ስለሆነ
ሐዋርያት ሳይጠመቁ የሞቱ አረማውያን ናቸው ማለት ይሆናል።
ሦስተኛ ደግሞ አሁን ሳስተምራችሁ ያልገባችሁን መንፈስ ቅዱስ
መጥቶ ያብራራላችኋል ስላለ፣ከ600 ዘመን በኋላ መሐመድ መጥቶ
አስተማራቸው ማለት ቀልድ ነው።
አራተኛ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ መጥቶ እኔ ሳስተምራችሁ ያልገባችሁን
ያብራሩላችኋል ስለኔም ይመሰክራል ነው ያለው ጌታ፣መሐመድ ግን
የሠራው የዚህን ተቃራኒ ነው፤ጌታን ከዷል፣ተከታዮቹን አርዷል።
(ዮሐ.14:16-17፤24-27)
ከዚህ ቀጥለን ትንቢቶቹን ከእነ ምዕራፋቸው ለአንባቢ እናቀርባለን፤
(ሉቃ.24:48-49) እናንተም የዚህ ሁሉ ነገር ምስክሮች ናችሁ። እነሆ
እኔ የአባቴን ተስፋ እልክላችኋለሁ፤እናንተም ኀይል ከላይ እስክትለብ
ሱ ድረስ በእየሩሳሌም ከተማ ቆዩ (ተቀመጡ)። ኀይል ለመልበስ 600
ዘመን መኖር የለባቸውም ምክንያቱም አሁኑኑ ዓለምን ዙራችሁ
ዓለምን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁ ብሎ አዝዘዋል
ና፣(ማር.16:15-18)።
(ግብሐ.1:3-5)ብዙ መከራ ተቀብሎ ከሞተ በኋላ በብዙ ግልጽ ማስረጃ
ሕያው ሁኖ ታያቸው፤አርባ ቀን ሙሉ እየተገለጠላቸውም ስለ እግዚ
አብሔር መንግሥት አስተማራቸው። አብሯቸውም በነበረ ጊዜ እንዲ
ህ ሲል አዘዛቸው። እኔ የነገርኳችሁን የአብን ተስፋ ጠብቁ እንጂ
ከኢየሩሳሌም አትውጡ፤ዮሐንስ በውኃ አጠመቀ፣እናንተ ግን ከጥቂ
ት ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ ብሏቸው ዐረገ፤በዐረገ
በዐሥረኛው ቀን የተሰጠው ተስፋ መንፈስ ቅዱስ፣አንድነት ተቀምጠው
ሲጠብቁ፣በእያንዳንዳቸው ላይ ወርዶ በልዩ ልዩ ቋንቋ አናግሮአቸዋል

ኀይል፣ጥብዓት ሰጥቷቸዋል። ለዚህም ግብረ ሐዋርያት ምዕራፍ ሁለትን ያነቧል። ለምሳሌም የአይሁድ ፋሲካ ባለፈ በኀምሳኛው ቀን በሚከበረው በጴንጤ ቆስጤ በዓል ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ በአንድነት፣በአንድ ቦታ ተሰብስበው ነበር፤በድንገት ብርቱ ዐውሎ ነፋስ የመሰለ ድምፅ ከሰማይ መጣ፤የነበሩበትንም ቤት ሞላው። የእሳት ነበልባሎች የሚመስሉ ምላሶች ታዩአቸው፤ተከፋፍለውም በእይንዳንዳቸው ላይ ዐረፉባቸው። ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ፣መንፈስ ቅዱስ እንዲናገሩ በሰጣቸው ችሎታ መጠን በሌሎች ቋንቋዎች መናገር ጀመሩ።

በዓለም ካሉት ሀገሮች ሁሉ የመጡ መንፈሳውያን አይሁድ በኢየሩሳሌም ይኖሩ ነበር። ይህንም ድምፅ በሰሙ ጊዜ ብዙ ሰዎች ተሰበሰቡ፤ በኢየቋንቋቸውም ሲናገሩ ስለሰሟቸው ተደነቁ። በመገረምና በመደነቅም እንዲህ አሉ፣እነዚህ እንዲህ የሚናገሩት ሁሉ የገሊላ ሰዎች አይደሉምን? ታዲያ በእየትውልድ ሀገራችን ቋንቋ ሲናገሩ፣እኛ የምሰማቸው እንዴት ነው?――――――――።

እነሆ! እነዚህ ሁሉ የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ በቋንቋችን ሲናገሩ እንሰማለን" ስለዚህ ሁሉም ተገረሙና የሚሉትን አጥተው "ይህ ነገር ምን ይሆን" ተባባሉ። (በሞላ ምዕራፍን ያነቧል።)

የዚህ ምዕራፍና ጥቀስ ከምኑ ላይ ነው ለመሐመድ የሚስማማ መሐመድ ክርስቶስን አልተሰቀለም፣አልሞተም፣አልተነሣም የሚል፤እነዚህ ሁለቱ ምዕራፎች ግን ጌታ ለሐዋርያት (ዮሐ.14:26)ያላቸውን መንፈስ ቅዱሳን ነው። አብ በእኔ ስም የሚልከው አጽናኙ መንፈስ ቅዱስ ግን ሁሉን ነገር ያስተምራችኋል፤እኔ የነገርሃችሁንም ሁሉ እንድታስተውሉ ያደርጋችኋል። (15:26)።

እንደዚህ ያለውን፣ወዲያው ከ10ቀን በኋላ በጰራቅሊጦስ የተፈጸመውን፣መፈጸምም የነበረበትን ጥቅስ ነው፣ እነ አሕመድ ዲዳት ለመሪአቸው ለመሐመድ የሚሰጡት፣የኢየሱስን ነቢይነት ያምናሉ፤ሥራውን ትንቢቱን ግን ለራሳቸው ቅጥፈት እንዲመች ያጣምማሉ።

## ምዕራፍ: 10፣

## የሙሴና የኢየሱስ፣መመሳሰል፣

እንደ ዲዳት ያሉ እነደርሶ ሊቅ እስላሞች ሙሴ እንደኔ ያለ ነቢይ ከወንድሞቻችሁ መካከል (ዘጸ.18:18-19)ያስነሣላችኋል ያለውን ጥቅስ አጣመው፣ሙሴና ኢየሱስ አይመሳሰሉም ይላሉ። በቦታው እንደምናየው የማይመሳሰሉ ሙሴና መሐመድ እንጂ ኢየሱስና ሙሴማ በባሕርይ ከመለያየት በቀር በግብር በዘር አንድ ናቸው። መሐመድና ሙሴ ግን በተፈጥሮ ሥጋ አንድ ሲሆኑ በግብርና በአምልኮ ይለያያሉ። ለምሳሌ ባጭሩ ሙሴ ጣዖት ማምለክን ይከለክላል፤መሐመድ ግን ከዕባ ለምትባል ጣዖት ጥቁር ደንጊያ ይሰግዳል፣ያመልካል፣ ያስመልካል። ክርስቶስ ምንም ዓለምን ለማዳንና ለማስተማር በለበሰው ሥጋ ከኀጢአት በቀር ፍጹም ሰው ቢሆንም ሰው የሆነ ፍጹም አምላክ ስለሆነ ከፍጡራኑ ጋራ ባይመሳሰልም እነ አያ ዲዳት ይመሳሰላል ካሉ በትስብእቱ በሠራው ሥራ እያነጻጸር እናሳያለን።

ከሁሉ አስቀድሞ መመሳሰል፣ሰዎች ይመሳሰላሉ ሲባል ምን ማለት እንደሆነ ለአያ ዲዳት ልንገልጥ እንወዳለን። ይመሳሰላሉ ሲባል በመልክ በጠባይ፣በሚዛን፣በቆዳ ቀለም፣በቁመት በጸታ ወዘተ አይደለም መመሳሰል በአንድ ወይም በሁለት ነገር ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ እኔ የአባቴን እኅት አክስቴን እመስል ነበር፣ግን ከሷ ጋራ በጾታና በጥርስ እንለያይ ነበር፣ጥርስ የእናቴን ጾታ ያባቴን ይዤ ነው የተወለድሁ፣የወጣሁ። አባቴን ደግሞ በአፍንጫና በጠጉር ስለምመስል ብዙ ሰው አባትህን ነው የምትመስል ይለኛል። ሌላው ደግሞ ከአክስቴ ዝምድና የሌላት እናቴ ልክ እንዳክስቴ ቀይ ስለነበረች እናቱን ነው የሚመስል እያለ ይከራከር ነበር። አባቴም በእኛ መልክ ክርክር ሲነሣ ምንትዋብና ዓለማየሁ ከዘመዶቻቸው መልክ ጥሩ ጥሩውን ነው ለቅመው የተወለዱ ይል ነበር። እንደዚሁም ክርስቶስ ከነቢያት ትንቢት ከአንዱ አንዱን ከሌላው ደግሞ ሌላውን ይዞ ነው የመጣው፣የእሱ ምሳሌ የሚሆን አንድ ፍጹም ሰው የለምና።

አንዱ ነቢይ እንደ ሙሴ ያለ ነቢይ፣ሌላው ደግሞ በመለኮቱ አምላክ መሆኑን፣ቀጣዩ ደግሞ የመከራ ሰው መሆኑን፣መገረፉን፣መሰቀሉን፣መዋረዱን፣መሞቱን መነሣቱን፣ማረጉን በአባቱ ቀኝ በክብር መቀመጡን፣ሥልጣን ሁሉ ለእሱ መስጠቱን ነግሯል፣ነግረዋል፣ተንቢተዋል አስቀድመውም አስተምረዋል። ስለመሐመድ መስሎቹ ሐሰውተ መሲሕነትም በሰፊው አትተዋል። ሁሉንም በተራ እስክናየው ለዚህ ጽሑፍ ምክንያት የሆነን መመሳሰል ከዚህ እንቀጥላለን። ክርስቶስ ያስተማረው በአምላክነቱና በባሕርዩ ምክንያት ሊሠራው የማይገባውን እያዘዘ፣

የተቀረውን ግን እሠራ ነው ያሳየው፣(ለዚህ ነው ቅዱስ ጳውሎስ እኔ ክርስቶስን እንደ መስልሁ እናንተም እኔንም ስሉ ያለው)። ጾምና ጸሎትን ማብላትና ማጠጣት፣መታገሥን፣መከራ መቀበልን ወዘተ. የመሳሰለውን በመተግበር።

__ሙሴና ክርስቶስ በመነጻጸር፤__

ሙሴ ተወልዶ ከወላጆቹ ቤት መኖር ስለማይችል ከባሕር ከዐባይ ወንዝ ተጥሎ የፈርዖን ልጅ በአጋጣሚ ስትታጠብ አግኝታ አሳደገችው፤ይህም በእግዚአብሔር ጠባቂነት ነው። (ዘፀ.2: 2-10፣)

1. ጌታም እንደ ሀብታሞች ከሞቀ ቤት ሳይሆን ከበረት፣ከግርግም፣ከጋጥ ተወልዶ ብርድ ሲቀፈቅፈው ሰንብቶ ድንነትን ቀምሷል። ጌታ ግን ከከብቶች ርግጫም ከውርጩም ጠብቆታል።

(ሉቃ.2:7)በዚያም ሳሉ የመውለጃዋ ወራት ደረሰ፣ የበኩር ልጇንም ወለደች በመጠቅለያም ጠቀለለችው፣በእንግዶችም ማደሪያ ስፍራ ስለነበራቸው በግርግም አስተኛችው።

2. ሁለቱም በእኩይ መንፈስ ተፈትነዋል፣አርባ አርባ ቀንም ጾመዋል፤(ዘፀ.34:28፤ማቴ.4:1-11)በዚያም አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ከእግዚአብሔር ጋራ ነበረ፤እንጀራም አልበላም ውሃም አልጠጣም፣ በጽላቶቹም ዐሥሩን የቃል ኪዳን ቃላት ጻፈ።

3. ሙሴም ክርስቶስም ከሕዝባቸው ተሰደዋል፣ተባረዋል፤ስለ ሙሴ (ዘኁ. ምዕፍ: 14-16 አንብ) ስለ ክርስቶስ ደግሞ፣(ሉቃ.4:1-28፣) በምኩራብም የነበሩ ሁሉ ይህን ሰምተው ቁጣ ሞላባቸው፣ተነሥተውም ከከተማ ወደ ውጭ አወጡት፣ይጥሉትም ዘንድ ከተማቸው ተሠርታበት ወደ ነበረች ወደ ተራራው አፋፍ ወሰዱት። እሱ ግን በመካከላቸው አልፎ ሄደ። (ዮሐ.1:11፤ማር.63፤ሉቃ 4:29፤23:18፤ ዮሐ.12:46)።

4. ሁለቱም ባሕርን አዝዘዋል፣ማዕበል ገሥጸዋል፤(ዘፀ.14:21)ሙሴም በባሕሩ ላይ እጁን ዘረጋ፤እግዚአብሔርም ሌሊቱን ሙሉ ጽኑ የምሥራቅ ነፋስ አምጥቶ ባሕሩን አስወገደው፣ባሕሩንም አደረቀው ውኃውም ተከፈለ። የእስራኤል ልጆችም በባሕሩ መካከል በየብስ ገቡ። ውኃውም በቀኛቸውና በግራቸው እንደ ግድግዳ ሆነላቸው። (ማቴ.8:26) እሱም እናንተ እምነት የጎደላችሁ፣ስለምን ትፈራላችሁ አላቸው፣ከዚህ በኋላ ተነሥቶ ነፍሱንና ባሕሩን ገሠጸ፣ታላቅ ጸጥታም ሆነ።

5. ሁለቱም ሕዝባቸውን፣ተከታያቸውን መግበዋል፤ (ዘፀ.16:15-23) የእስራኤልም ልጆች ባዩት ጊዜ ያ ምን እንደሆነ አላወቁምና እርስ በርሳቸው ይህ ምንድር ነው ተባባሉ፤ሙሴም ትበሉ ዘንድ

እግዚአብሔር የሰጣችሁ እንጀራ ይህ ነው። እግዚአብሔር ያዘዘው ነገር ይህ ነው። እያንዳንዱ የሚበላውን ያህል ይልቀም፣በድንኳኑ ባሉት ነፍሶች ቁጥር፣ለአንድ ሰው አንድ ጎሞር ውሰዱ አላቸው።——። (ማቴ.14) በመሸም ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ወደ እርሱ ቀርበው፣ ቦታው ምድረ በዳ ነው። ሰዓቱም አሁን አልፏልና ወደ መንደር ሂደው ለራሳቸው ምግብ እንዲገዙ ሕዝቡን አሰናብት አሉት። ኢየሱስም እናንተ የሚበሉትን ስጧቸው እንጂ ሊሄዱ አያስፈልግም አላቸው፣እነ ሱም ከአምስት እንጀራና ከሁለት ዓሣ በቀር በዚህ የለንም አሉት። እሱም እነዚያን ወደዚህ አምጡልኝ አላቸው። ሕዝቡም በሣር ላይ እንዲቀመጡ አዘዘ። አምስቱን እንጀራና ሁለቱን ዓሣ ይዞ ወደ ሰማይ አሻቅቦ አየና ባረከ፣እንጀራውንም ቆራርሶ ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠ። ደቀ መዛሙርቱም ለሕዝቡ። ሁሉም በልተው ጠገቡ። የተረፈውን ቁርስራሽም ዐሥራ ሁለት ምሶብ ሙሉ አነሡ። ከሴቶችና ከልጆችም በቀር አምስት ሽህ ያህል ወንዶች ነበሩ።

6. ሙሴ የሚያበራ ገጽ እንደነበረው ጌታም በደብረ ታቦር ብርሃነ መለኮቱን ሲገልጥ በብርሃን ተጠቅሎ ታይቷል። (ዘፀ.34 35፤ማቴ.17:2-8)

7. ሁለቱም የሕዝባቸውን ማጉረምረም ታግሠዋል፣(ዘፀ.15: 24፤ማር. 7:1-14) ሁለቱም በወገኖቻቸው ተጠልተዋል፣ተሰድበዋል፣ተቃለዋል (ዘኍ.12:1——፤ዮሐ 7:5)

8. ሁለቱም በእግዚአብሔር ስም በለውነት ሠርተዋል። (ዘፀ.19:1-7)— ሙሴም መጣ የሕዝቡንም ሽማግሌዎች ጠርቶ እግዚአብሔር ያዘዘውን ይህን ቃል ሁሉ በፊታቸው ተናገረ። ሕዝቡም ሁሉ አንድ አፍ ሁነው እግዚአብሔር ያለውን ሁሉ እናደርጋለን ብለው መለሱ። ሙሴም የሕዝቡን ቃል ወደ እግዚአብሔር አደረሰ። (ዮሐ.6:38፤)—— ፈቃዴን ለማድረግ አይደለም እንጂ የላከኝን ፈቃድ ለማድረግ ከሰማይ ወርጀለሁና። (8:26) ስለ እናንተ የምናገረው የምፈርደውም ብዙ ነገር አለኝ፤ዳሩ ግን የላከኝ እውነተኛ ነው፣እኔም ከእሱ የሰማሁትን ለዓለም እናገራለሁ አላቸው። (40) ነገር ግን አሁን ከእግዚአብሔር እውነት የነገርኋችሁን ሰው ልትገሉኝ ትፈልጋላችሁ።

9. ሁለቱም 70:70 ረዳቶች ነበሯቸው።

(ዘኍ.11:16-17) እግዚአብሔር ሙሴን አለው ከእስራኤል ሽማግሎች ከሕዝቡ ላይ ሽማግሎችና አለቆች ይሆኑ ዘንድ የምታውቃቸውን 70 ሰዎች ሰብሰብልኝ፣ወደ መገናኛቸውም ድንኳን አምጣላቸው፣በዚያም ካንተ ጋራ አቁማቸው። እኔም እወረዳለሁ በዚያም እነጋግርሃለሁ፣

በአንተ ካለውም መንፈስ ወስጄ በእነሱ ላይ አደርጋለሁ። አንተ ብቻ እንዳትሸከም፣የሕዝቡን ሸክም ከአንተ ጋራ ይሸከማሉ። (ሉቃ.10:1)ከዚያም በኋላ ጌታ ሌሎችን 70 ሾመ፣ሁለት ሁለትም አድርጎ እርሱ ሊሄድበት ወዳለው ከተማ ስፍራ ሁሉ በፊቱ ላካቸው።

10. ሁለቱም ሕግ ሐግገዋል ሠርተዋል መሥርተዋል፤ሥርዓት ሠርተዋል (ዘፀ.12:14)ይህም ቀን መታሰቢያ ይሁናችሁ፣ለእግዚአብሔር በዓል ቀን ታደርጉታላችሁ፣በልጅ ልጃችሁ ሥርዓት ሁኖ ይኖራል። (ሉቃ.22:19) እንጀራውንም አንሥቶ አመስግነ ቆርሶም ሰጣቸውና ስለ እናንተ የሚሰጠው ሥጋዬ ይህ ነው፤ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ።

11. ከሞት በኋላ ሁለቱም ከሙታን ተነሥተው ታይተዋል፤(ማቴ.17:3-8፤ግብሐ. 1:3)

12. በሕገ ጋብቻ ሥርዓት በሥርዓተ አውስቦም የሙሴና ክርስቶስ ሕግ አንድ ነው፤ሙሴ ያገባው እንዲት ነው፤ያችንም ትልቅ እኅቱና ወንድሙ ነገዷ ከኛ፣ተለየ፣ቆዳዋ የጠቆረ ነው ብለው ቢያጉረመርሙበት፣ወደ እግዚአብሔር አመልክቶ የሚከተለውን መልስ አግኝቷል። ለዚህም ማስረጃ ሊንባቢ እንዲቀና ዘኍ.12 ምዕራፍ በጠቅላላ ከዚህ ቀጥሎ ተጽፏል።

ሙሴም ኢትዮጵያዊቱን አግብቷልና ባገባት በኢትዮጵያዊቱ ምክንያት ማርያምና አሮን በእሱ ላይ ተናገሩ። እነርሱም በውኑ እግዚአብሔር በሙሴ ብቻ ተናግሯልን? በእኛስ ደግሞ የተናገረ አይደለምን? አሉ እግዚአብሔርም ሰማ። ሙሴም በምድር ላይ ካሉት ሰዎች ሁሉ ይልቅ እጅግ ትሑት ሰው ነበር። እግዚአብሔርም ወዲያው ሙሴንና አሮንን ማርያምንም፤ሦስታችሁ ወደ መገናኛው ድንኳን ውጡ ብሎ ተናገረ፣ሦስቱም ወጡ። እግዚአብሔር በደመና ዐምድ ወረደ፣በድንኳኑም ደጃፍ ቆመ፤አሮርንና ማርያምን ጠራ፤ሁለቱም ወጡ። እሱም ቃሌን ስሙ በመካከላችሁ ነቢይ ቢኖር እኔ እግዚአብሔር በራእይ እገለጥለታለሁ ወይም በሕልም እናገረዋለሁ። ባሪያዬ ሙሴን ግን እንዲህ አይደለም፣እርሱ በቤቴ ሁሉ የታመነ ነው። እኔ አፍ ለአፍ በግልጥ እናገረዋለሁ። በምሳሌ አይደለም የእግዚአብሔርን ም መልክ ያያል፣በባሪዬ በሙሴ ላይ ትናገሩ ዘንድ ለምን አላፈራችሁም? አለ።

እግዚአብሔርም ተቆጥቶባቸው ሄደ። ደመናውም ከድንኳኑ ተነሣ። እነሆም ማርያም ለምጻም ሆነች። እንደ አመዳይም ነጭ ሆነች። አሮንም ማርያምን ተመለከተ እነሆም ለምጻም ሁና ነበር። አሮንም ሙሴን ጌታዬ ሆይ! ስንፍና አድርገናልና በድለንማልና እባክህ

ኀጢአት አታድርግብን። ከእናቱ ሆድ በወጣ ጊዜ ግማሽ ሥጋው ተበልቶ እንደ ሞተ፣እርሷ አትሁን። ሙሴም ወደ እግዚአብሔርም እየጮሀ አቤቱ እባክህ አድናት አለው። እግዚአብሔርም ሙሴን፣አባ ትዋ ምራቁን በፊቷ ቢተፋበት እንኳ ሰባት ቀን ታፍር ዘንድ ይገባት ነበር። ሰባት ቀን ከሰፈር ውጭ ተዘግቶ ተቀመጠች፣ማርያምም እስክትመለስ ድረስ ሕዝቡ አልተጓዙም።

ሙሴ፣እግዚአብሔር በጥንተ ተፈጥሮ አዳምና ሔዋንን ሲፈጠር አንድ ወንድ ላንድ ሴት፣(አንድላንድ)መፍጠሩን በማወቁ አንድ ጊዜ ባጋጣሚ ያገባኋትን ምድያማዊት (ኢትዮጵያዊት)አልፈታም በማለቱ ትልቅ ወንድሙና እኅቱ ቢጣሉት፣እምቢ ስላለ፣ፍጥረቱን ሁሉ እኩል የሚያይ አምላኩ፣ኹል አፍ ማርያምን በለምጽ ቀጣ፣መሃል ሰፋሪ አሮንን ገሠጸ። ጋብቻን በጥንተ ተፈጥሮ አንድ ወንድ ላንድ ሴት ብሎ በእኩልነት የፈጠረው እግዚአብሔር አብ ሲሆን ያጸደቀው ደግሞ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ የለበሰ ወልደ እግዚአብሔር ሲሆን የሚቀድሰው ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ነው። ይህን የሚቃወም የእግዚአብሔርን ሕግና ሥርዓት ይቃወማል።

(ዘፍ.2:21-24) እግዚአብሔር አምላክም ለአዳም ከባድ እንቅልፍን ጣለበት፣አንቀላፋም፣ከጎድኑም አንዲት ዐጥንትን ወስዶ ስፍራውን በሥጋ ዘጋው። እግዚአብሔር አምላክም ከአዳም የወሰዳትን ዐጥንት ሴት አድርጎ ሠራት። ወደ አዳምም አመጣት። አዳምም አለ፣ይህች ዐጥንት ከዐጥንቴ ናት፣ሥጋም ከሥጋዬ ናት፣እርሷ ከወንድ ተገኝታለ ችና ሴት ትባል። ስለዚህ ሰው አባትና እናቱን ይተዋል፤ከምሽቱም ይጠበቃል። ሁለቱም አንድ አካል ይሆናሉ።

ይህን ደግሞ ጌታ በወንጌል እንደ ሚከተለው አድርጎ አጽድቆታል (ማቴ.19:3)ፈሪሳውያንም ወደ እሱ ቀረቡና ሊፈትኑት ሰው በሆነው ምክንያት ሁሉ ምሽቱን ሊፈታ ተፈቅዶለታልን? አሉት። እርሱ ግን መልሶ እንዲህ አለ፣ፈጣሪ በመጀመሪያ ወንድና ሴት አደረጋቸው፣አለ ም፣ስለዚህ ሰው አባትና እናቱን ይተዋል ከምሽቱም ጋራ ይጣበቃል፣ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ የሚለውን አላነበባችሁምን? ስለዚህ አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ ወደፊት ሁለት አይደሉም። እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየውም። እነሱም እንግዲያ ሙሴ የፍችዋን ጽሕፈት ሰጥቶ እንዲፈታት ለምን አዘዘ? አሉት። እርሱም፣ ሙሴስ ስለልባችሁ ድንዳኔ ምሽቶቻችሁን ትፈቱ ዘንድ ፈቀደላችሁ፣ከ ጥንት ግን እንዲህ አልነበረም። እኔ ግን እላችኋለሁ፣ያለ ዝሙት ምክንያት ምሽቱን ፈቶ ሌላይቱን የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል፣የተፈታ ችውንም የሚያገባ ያመነዝራል።

የጋብቻን ክቡርነትና የሴትና ወንድን እኩልነት ደቀ መዛሙርቱም አጥብቀውታል፡(ገላ.3:26-29) በእምነት በኩል ሁላችሁም በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና፤ከክርስቶስ ጋራ አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋልና፤አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፤ባሪያ ወይም ጭዋ ሰው የለም፤ወንድም ሴትም የለም፤ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና፤እናንተም የክርስቶስ ከሆናችሁ፤እንኪያስ የአብርሃም ዘር እንደ ተስፋውም ቃል ወራሾች ናችሁ።

(1ቆሮ.7:1-5)ስለ ጻፋችሁልን ነገርስ ለሰው ከሴት ጋራ አለመገናኘት መልካም ነው። ነገር ግን ስለዝሙት ጠንቅ ለእያንዳንዱ ለራሱ ምሽት ትኑረው፤ለእያንዳንዷ ደግሞ ለራስዋ ባል ያኑራት። ባል ለምሽቱ የሚገባትን ያደርግላት፤እንደዚሁም ደግሞ ምሽቲቱ ለባልዋ። ምሽት በገዛ ሥጋዋ ላይ ሥልጣን የላትም፤ሥልጣን ለባሏ ነው እንጂ፤እንዲ ሁም ደግሞ ባል በገዛ ሥጋው ላይ ሥልጣን የለውም፤ሥልጣን ለምሽቱ ነው እንጂ። ለጸሎት ትተጉ ዘንድ ተስማምታችሁ ለጊዜው ካልሆነ በቀር፤እርስ በርሳችሁ አትከላከሉ (አትለያዩ) ራሳችሁን ስላለመ ግዛት ሰይጣን እንዳይፈታተናችሁ፤ደግሞ አብራችሁ ሁኑ (እስከ መጨረሻው አንብ)የሙሴና የክርስቶስ የጋብቻ ሕግ ይህን ነው። እንደ መሐመድ እንስሳ ይምሰል በሚዳ ተገናኝቶ መለያየት ሳይሆን፤አውስቦ ከወሲብ በኋላ ተቃቅፎ ማደርንም ያጠቀልላልና። ይህንስ በስፊው በሙሴና በመሐመድ ልዩነት ዝቅ ብለን እናየዋለን።

ማናቸውም ባለሀገር ስለግብረ አውስቦ ሲጠይቁት በመካከለኛ ሦስት ጊዜ ያስፈልጋል፤እሱም ማታ እንዴት ዋልሽ? እንዴት ዋልህ? በመንፈቀ ሌሊት ለተባይ መከላከያ፤ባጠባብ ደኅና ዋል፤ደኅና ዋይ መበባያ ይላል።

(ዕብ.13:4-5)መጋባት (አወሰቦ) በሁሉ ዘንድ ክቡር ነው፤ምኝታውም ንጹሕ ነው፤ሴሰኞችንና አመንዝሮችን ግን እግዚአብሔር ይፈርድባቸ ዋል። በዚህ ጥቅስ መሠረት ከሙሴና ከክርስቶስ ሕግ የወጣ ከአንድ ላንድ የተላለፈ ወሲብ ማመንዘር ነው። (1ጴጥ.3:7)እንዲሁም እናንተ ባሎች ሆይ! ደካማ ፍጥረት ስለሆኑ ከምሽቶቻችሁ ጋራ በማስተዋል አብራችሁ ኑሩ። ጸሎታችሁ እንዳይደናቀፍ፤አብረው ደግሞ የሕይወት ን ጸጋ እንደ ሚወርሱ አድርጋችሁ አክብሯቸው። እንዲህ ያለውን የሙሴንና የክርስቶስን የአውስቦ ሥርዓት ነው መሐመድ በአከባቢው ያሉትን አረማውያን አሕዛብ ተከትሎ ከ4-13 ወሰነ የለሽ አድርጎ የለቀቀው። እንዲህ ያለ ሰው ቅዱሳት መጻሕፍትን ይከተላል ለማለት ያስቸግራል።

14. ሙሴና ክርስቶስ ስለ ተጨቆነችው ሴት ተከራክረው መብቷን አስከብረዋል፤የሙሴው በሰለጳአድ ሴቶች ልጆች ይታወቃል፤(ዘኁ.27 28)የሰለጳድም ሴት ልጆች በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ አጠገብ በሙሴና በካህኑ በአልአዛር በአለቆችም በማኅበሩም ሁሉ ፊት ቁመው አባታችን በምድረ በዳ ሞተ፣በራሱ ኃጢአት ሞተ እንጂ ከቆሬ ጋራ በእግዚአብሔር ላይ በተሰበሰቡ ወገን መካከል አልነበረም ወንዶችም ልጆች አልነበሩትም። ወንድ ልጅስ ባይኖረው የአባታችን ስም ከወገኑ መሃል ለምን ይጠፋል? በአባታችን ወንድሞች መካከል ርስት ስጠን አሉ። ሙሴም ነገራቸውን ለእግዚአብሔር ዐቀረበ። እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው የሰለአድ ልጆች እውነት ተናግረዋል፤በአባታቸው ወንድሞች መካከል የርስት ድርሻ ስጣቸው፤የአባታቸውን ርስት ለእነሱ አሳልፈህ ስጥ።——። ክርስቶስ እንዲያውም ከመሰበኩም በላይ ስለሴት መብት ብዙ ጊዜ በመከራከሩ ምክንያት አይሁድ የመሰናከል ጥያቄ ይጠይቁት ነበር። (ዮሐ.8 1-11)ኢየሱስ ግን ወደ ደብረ ዘይት ሄደ። ማለዳም ደግሞ ወደ መቅደስ ደረሰ። ሕዝቡም ሁሉ ወደ እርሱ መጡ። ተቀምጦም ያስተማራቸው ጀመረ። ጻሐፎችና ፈሪሳውያንም በምንዝር የተያዘች ሴት ወደሱ አመጡ። በመካከልም እርሷን አቁመው፣መምህር ሆይ! ይህች ሴት ስታመነዝር ተገኝታ ተያዘች፣ሙሴም እንደነዚህ ያሉት እንዲወገሩ በሕግ አዘዘን። አንተስ ስለ እርስዋ ምን ትላለህ? አሉት። የሚከሱበትንም እንዲያገኙ፣ሊፈታተኑት እንዲህ አሉ። ኢየሱስ ግን ጎንበስ ብሎ በጣቱ በምድር ላይ ጻፈ፤መላልሰው ሲጠይቁት ጊዜ ግን ቀና ብሎ ከእናንተ ኀጢአት የሌለበት አስቀድሞ በደንጊያ ይውገራት አላቸው። ደግሞም ጎንበስ ብሎ በጣቱ በምድር ላይ ጻፈ። እነርሱም ይህን ሲሰሙ ኅሊናቸው ወቀሳቸውና ከሽማግሎች ጀምረው እስከ ኋለኞች አንድ አንድ እያሉ ወጡ። ኢየሱስም ብቻውን ቀረ፤ሴቲቱም በመካከል ቆማ ነበረች። ኢየሱስም ቀና ብሎ ከሴቲቱ በቀር ማንንም ባላየ ጊዜ፣ አንቺ ሴት፣እነዚያ ከሳሾችሽ ወዴት አሉ? የፈረደብሽ የለምን? አላት። እስዋም "ጌታ ሆይ! አንድስ እንኳ"አለች። "ኢየሱስም እኔም አልፈርድብሽም፣ሂጂ፤ከእንግዲህ ደግመሽ ኀጢአት አትሥሪ" አላት።

ከሙሴ እስከ ክርስቶስ ባለው ዘመን ሴትና ወንድ ሲያመነዝሩ የተያዙ እንደሆነ ወንዱን ለቀው ሴቷን ይቀጣሉ። ይህ ልምድ በእንግሊዝ እስከ ሲልቢያ ፓንከርኸት ዘመን ነበር።

15. ከዚህ ሁሉም በላይ ሙሴ እንደኔ ያለ ነቢይ አለ እንጂ ጦረኛ ወይም ጀኔራል አላለም። ሙሴና ክርስቶስ የሚመሳሰሉት በነቢይነት

እንጂ በጀኔራልነት ወይም በጦር መሪነት አይደለምና። ብዙዎች
ነቢያትም ጀነራሎች አልነበሩም።

16. መጨረሻው ደግሞ ክርስቶስና ሙሴ፣ሁለቱም የያዕቆብ የሕግ
ምሽቱ የልጅ፣ ልጆች፣ እስራኤላውያን ሲሆኑ፣መሐመድ ግን
የዲቃላውና የገረዷ የእስማኤል ልጅ ዐረብ ነው። እያ መሐመድ ዲዳት
እስራኤል ዐረብ ወንድማማች መሆናቸውን ለማስረዳት የጠቀሰው
ዘፀ.16:12፣የሚለው እሱ እንደ ጠቀሰው ሳይሆን "ከወንድሞቹ መካከ
ል በጠብ(በአምባጓሮ) ወንድሞቹን ለማሳፈር ይኖራል ነው፤በዕብራይ
ስጥ በግሪክ በዐረብ ትርጉም ተመልከት። ከእስማኤል ዘር ጦርነትና
አምባጓሮ እንጂ ሰላም አልተነገረም። ወንድሞቹ የተባሉትም እንደሱ
ከገረድ የተወለዱ ዲቃሎች በለሆኑ ለመቋቋሚያ ትንንሽ ነገር
እየተሰጡ ከይሥሐቅ ጋራ እንዳይወረሱ የተባረሩ ናቸው። እነሱ
ከተባረሩ በኋላ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚወለድበት ይሥሐቅ ተመርጧል።
(ዘፀ.25:5)አብርሃምም የነበረውን ሁሉ ለይሥሐቅ ሰጠው፤የአብርሃም
ም ለነበሩ ለዕቁባቶቹ ልጆች አብርሃም ስጦታን ሰጣቸው፤እርሱም ገና
በሕይወቱ ሳለ ከልጁ ከይሥሐቅ ለይቶ ወደ ፀሐይ መውጫ ወደ
ምሥራቅ ሀገር ሰደዳቸው። ይኸውም ሣራ እንደጠየቀችው ከረድኤቱ
ተስፋ እንዳይካፈሉ ነው። ስለዚህ ባልንጀሮቹ ዲቃሎቹ የኬጡራ ልጆች
እንጂ ያዕቆባውያን እስራኤል አይደሉም።

17. ቃሌንም በአፉ አደርጋለሁ፣
ይህግ እንዲያውም ከሙሴ ይልቅ ለክርስቶስ ይስማማል። አያ ዲዳት
ለምን ብትል? ሙሴ ነቢይ ሲሆን፣ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ራሱ ቃለ
እግዚአብሔር ነው። እሱም ራሱ አባቴ ያዘዘኝን፣አባቴ የነገረኝን፣እን
ደ አባቴ ፈቃድ እያለ ሲያስተምር ኑሯል፤በዚህም ሥጋ የለበሰ
የመለኮት ልጅ መሆኑን አስተምሯል።

(ዮሐ.7:17)አሁንም በበዓሉ እኩሌታ ኢየሱስ ወደ መቅደስ ወጥቶ
ያስተምር ነበር። አይሁድም፣ይህ ሰው ሳይማር፣መጻሕፍትን እንዴት
ያውቃል? ብለው ይደነቁ ነበር። ስለዚህ ኢየሱስ መለሰ እንዲህም
አላቸው፣ትምህርቴስ ከላከኝ ነው እንጂ ከኔ አይደለም፣ፈቃዱን ሊያደ
ርግ የሚወድ ቢኖር እርሱ ይህ ትምህርት ከኔ ወይም ከእግዚአብሔ
ለይቶ ያውቃል። (8:26)የላከኝ እውነተኛ ነው፤እኔም ከእሱ የሰማሁትን
ይህን ለዓለም እናገራለሁ አላቸው።

(12:49-50)እኔ ከራሴ አልተናገርሁምና ነገር ግን የላከኝ አብ እርሱ
የምለውን የምናገረውንም ትእዛዝ ሰጠኝ። ትእዛዙም የዘለዓም ሕይወት
እንደሆነች አውቃለሁ። ስለዚህ እኔ የምናገረውን አብ እንደነገረኝ
እንዲሁ እናገራለሁ።

እነዚህን የመሳሰሉ ብዙ ጥቅሶች አሉ። ክርስቶስ ሊቀ ነቢያትና ሊቀ ሐዋርያት የሚባለውም በዚህ ምክንያት ነው። ሙሴም ለክርስቶስ ንኡስ ምሳሌ እንጂ ዕሩይ (አቻ) ምሳሌ አይደለም።

18. ሙሴ ከሰው ተለይቶ አርባ ቀን ጾሞ ዐሥርቱን ቃላት (ትእዛዛት) በጽላት አጽፎ እንደ ተቀበለ ቃለ እግዚአብሔር ወልድም ከአባቱ ጋራ በመለኮት እምቅድመ ዓለም ሲኖር ኑሮ አሁን ድኅረ ዓለም በእኛ ጊዜ ሥጋ ለብሶ፣በትስብእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ተብሎ ተሰይሞ ስድስቱን ቃላተ ወንጌል (ትእዛዛት) አስተምሯል።

ይህ ሁሉ መመሳሰል እያለ፣እያ አሕመድ ዲዳት ግን ቴሉን ጭጭ አደረግሁት እያለ ይደነፋል። በዚህ ጊዜ፣ከዚህ ላይ አስተዋይ አንባቢ ሁሉ፣አሕመድ ዲዳት እንደ ልማዱ ዋሽቷል፣ወይም ቴሉ ያልተገረ ነው ይላል።

ስለሙሴና ክርስቶስ መመሳሰል እስከዚህ ያየነው ያብቃንና መመሳሰል ለመመሳሰል እንዲዛመድ ከሌላው የስልምና ሐተታ በፊት ስለ ሙሴና መሐመድ አለመመሳሰል ደግሞ ከዚህ አያይዘን እንቀጥላለን።